በኢጣልያ ፡ አገር ፡ በናፖሊ ፡ ከተማ ፡ የተቋቋመ ፡ የምሥራቃዊ ፡ ቋንቋ ፡ ዩኒበርሲቲ

ስሙ ፡ ከማይታወቅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የተጻፈ ፡ ሉዊጂ ፡ ፉሴላ ፡ ያሳተመው ፡

# ያጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታሪክ ።

ሮማ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓመት ፡ እ·ኤ·አ·

36169 20
Dozent
DDr. Ernst Hammersd

history / biography of King Tewodros – of Ethiopia.

በኢጣልያ ፡ አገር ፡ በናፖሊ ፡ ከተማ ፡ የተቋቋመ ፡ የምሥረቃዊ ፡ ቋንቋ ፡ ዩኒበርሲቲ

Founded in the City of Napoli, Italy, the Eastern Lan University

Written by an Ethiopian whose name is not known; Printed by Luu

[ ስሙ ፡ ከማይታወቅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የተጻፈ ፡ ሉዊጂ ፡ ፋሴላ ፡ ያሳተመው ፡

Semu kämaytawäq Ityopyawi yätätsäfa Luwij fasela

(Title) => 

# ያጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታሪክ ።

Yatie Tewodros Tarik

übe.– [ The Biography / histoy of Emperor Tewodros.

26345 / ML: Lu:
UNIVERSITÄT HAMBURG
Seminar für Afrikanische Sprachen
und Kulturen

Roma 1959 A.D
[ሮማ] ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓመት ፡ እ·ኤ·አ·
[በሴናቶ ፡ ማተምያ ፡ ቤት] ፡ ታተመ ፡
Verl. bäsenato matämya bet tatämä

pages: 52

አሰባሰቤት ፡ ፈቃድ ፡ መልሶ ፡ ማሳተም ፡ ወይም ፡
መቅዳት ፡ ክልክል ፡ ነው ።

# መ ቅ ድ ም

ይህ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሳተምሁት ፡ ያጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታሪክ ፡ ከስመ ፡ ጥሩ ፡ ከሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ካርሎ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ተሰጠኝ ። ካርሎ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ታሪኩን ፡ ሲያስረክቡኝ ፡ ወደኢጣልያ ፡ ቋን ቋ ፡ ተርጉመህ ፡ አሳትመው ፡ ብለው ፡ ስለመከሩኝ ፡ ይህንኑ ፡ ምክራቸውን ፡ ተከትዬ ፡ በጣም ፡ የወደድኋቸውንና ፡ የወደዱኝን ፡ ሚቴን ፡ ወዳጄ ፡ ሳስብ ፡ ብርቱ ፡ ኀዘን ፡ ይሰማኛል ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በኤሮጳ ፡ አገር ፡ ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉት ፡ ሁለት ፡ ያጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታሪኮች ፡ ታትመው ፡ ነበር ፤ አንደኛው ፡ ካለቃ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ተጽፎ ፡ ከሻርል ፡ ሞንዶን ፡ ቢዳይሌት ፡ ወደፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ ከተ ተረጐመ ፡ በኋላ ፡ በፓሪስ ፡ ከተማ ፡ ታተመ ። ሁለተኛውም ፡ ከደብተራ ፡ ዘ ነብ ፡ ተጽፎ ፡ ኤኖ ፡ ሊትማን ፡ ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ አሳትመውት ፡ ፕሮፌሶር ፡ ማርቲኖ ፡ ማርዮ ፡ ሞረኖ ፡ ወደኢጣልያ ፡ ቋንቋ ፡ ተረጐሙት ። ትርጐሙ ፡ በ ፲፱፻፵፪ ፡ ዓመት ፡ በሮማ ፡ ከተማ ፡ ታተመ ።

እነዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀስኋቸው ፡ ሁለት ፡ ታሪኮች ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከን ግሊዝ ፡ ሠራዊት ፡ ጋራ ፡ የተዋጉትን ፡ ጦርነት ፡ አይተርኩትም ፤ ቢተርኩት ም ፡ በጥቅሻ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህ ፡ አሁን ፡ የማሳትመው ፡ ታሪክ ፡ የንግሊዝን ፡ ጦርነት ፡ በሰፊው ፡ ስለሚተርክ ፡ ከሁለቱ ፡ ሌላ ፡ ታሪኮች ፡ በፍጹም ፡ ይለያል ።

ለኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ስለንግሊዝ ፡ ጦርነት ፡ ከኢትዮ ጵያዊ ፡ ደራሲ ፡ የተጻፈ ፡ ታሪክ ፡ ታትሞ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። እንደዚህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ ሳሳትም ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ሁሉ ፡ የሚያ ስደስታቸውን ፡ ሥራ ፡ እንደምሠራ ፡ ባለሙሉ ፡ ተስፋ ፡ ነኝ ።

በታሪኩ ፡ ውስጥ ፡ የደራሲው ፡ ስም ፡ አልተገለጸም ። እርሱ ፡ የተወለደ በት ፡ አገር ፡ የኖረበትም ፡ ዘመን ፡ ምንም ፡ ባይታወቅ ፡ ታሪኩን ፡ ጽፎ ፡ ሲ ጨርስ ፡ ያጤ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስንና ፡ ያጤ ፡ ዮሐንስን ፡ ታሪክ ፡ ብጽፍ ፡ አን ድ ፡ ትልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ያስፈልገኛል ፡ ብሎ ፡ ስለጻፈ ፡ እስካጤ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘ መነ ፡ መንግሥት ፡ መኖሩ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ደራሲው ፡ ያጤ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ታሪክ ፡ ሲተርክ ፡ በጆሮው ፡ የሰማውን ፡ ወሬ ፡ ቸል ፡ ብሎ ፡ ባይኑ ፡ ያየውን ፡ ነገር ፡ ስለሚተርክ ፡ ካጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ መለማመዱ ፡ ከዚህ ፡ ይታወቃል ። ይህን ፡ አመዛዝኜ ፡ ታሪኩ ፡ ባይኑ ፡ ካየው ፡ መስካሪ ፡ ስለተጻፈ ፡ መታተሙ ፡ ጠቃሚ ፡ መስሎ ፡ ይታየኛል ።

ከካርሎ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ያገኘሁት ፡ ጽሑፍ ፡ ብዙ ፡ የጽሕፈት ፡ ስሕተት ፡ ነበረበት ። ጽሑፉን ፡ ሳሳትም ፡ ይህን ፡ ስሕተት ፡ ሳላርም ፡ ስለቀረሁ ፡ ጽሑፉ ፡ ከደራሲው ፡ እንደተጻፈ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ እንኳ ፡ ሳይለወጥ ፡ ታትሞአል ። እንደዚህ ፡ ያደረግሁት ፡ ላንባቢው ፡ የደራሲውን ፡ አጻጻፍ ፡ እንዳሳየው ፡ ነው ።

ይህን ፡ ያጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታሪክ ፡ ከሁን ፡ ቀደም ፡ ወደኢጣልያ ፡ ቋንቋ ፡ ተርጕሜው ፡ በናፖሊ ፡ በምሥረቃዊ ፡ ቋንቋ ፡ ዩኒበርሲቲ ፡ ባመታዊ ፡ ታሪክ ፡ መጽሔት ፡ አሳተምሁት ። ቅጁ ፡ በ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓመት ፡ በታተመው ፡ ክፍል ፡ ይገኛል ።

ይህን ፡ ታሪክ ፡ ለማሳተም ፡ የምሥረቃዊ ፡ ቋንቋ ፡ ዩኒበርሲቲ ፡ የሚበቃውን ፡ ገንዘብ ፡ ስለከፈለ ፡ ለምሥረቃዊ ፡ ቋንቋ ፡ ዩኒበርሲቲ ፡ የልብ ፡ ምስጋናን ፡ ሳቀርብ ፡ ከኢትዮጵያና ፡ ከኢጣልያ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የትምህርት ፡ ግንኙነት ፡ እየዋለ ፡ እያደረ ፡ እንዲስፋፋና ፡ እንዲጠና ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

በናፖሊ ፡ ከተማ ፡ ግንቦት ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ እ·ኤ·አ· ተጻፈ ።

ሉዊጂ ፡ ፉሴላ

በናፖሊ ፡ ከተማ ፡ በምሥረቃዊ ፡ ቋንቋ ፡ ዩኒበርሲቲ
ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ አስተማሪ ።

# ቴዎድሮስ

## ፩

ያጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ትውልዳቸው ። ያአባታቸው ፡ አገር ፡ ቋራም ፡ ደምብያም ፡ ነው ። የባታቸው ፡ ስም ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኀይሉ ፡ ይባላሉ ። የደጃች ፡ ክንፉ ፡ ወንድም ፡ ናቸው ። የቋራ ፡ ባለ ፡ አባት ፡ ናቸው ።

የእናታቸው ፡ ስምም ። ወይዘሮ ፡ አትጠገብ ፡ ይባላሉ ፡ ከጐንደርም ፡ ከእንፍራዝም ፡ ከቤጌምድርም ፡ ይወለዳሉ ። ከነገሥታት ፡ ወገንም ፡ ትውልድ ፡ አላቸው ፡ ይላሉ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኀይሉ ፡ ከደጃች ፡ ማሩ ፡ ወይም ፡ ከወንድማቸው ፡ ከደጃች ፡ ክንፉ ፡ ተጣልተው ፡ ጐንደር ፡ ከገዳም ፡ አስደውለው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ወይዘሮ ፡ አትጠገብን ፡ በጐንደር ፡ አገቡዋቸውና ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስን ፡ አረገዙ ፡ ገና ፡ ተረግዘው ፡ ሳሉ ፡ አንድ ፡ መለኵሴ ፡ ለወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ፡ ይህ ፡ ተረግዞ ፡ ያለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ሰውና ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይጠፋል ፡ ብሎ ፡ ነግሮአቸው ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በጐንደር ፡ ተወለዱ ፡

ስማቸውም ፡ ካሳ ፡ ተባሉ ። የክርስትና ፡ ስማቸው ፡ ገብረ ፡ ኪዳን ፡ ነው ። በጐንደርም ፡ አደጉ ፡ ጥቂት ፡ ከፍ ፡ ታሉ ፡ ወድያ ። ወደ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ወደአጎታቸው ፡ ሔዱ ፡ ከርሳቸውም ፡ ሎሌ ፡ ሁነው ፡ ተቀመጡ ።

ደጃች ፡ ክንፉም ፡ ታላቅ ፡ ጌታ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ፡ የባታቸው ፡ ቤት ፡ ፈንጃ ፡ ነበረ ፡ እርሳቸውም ፡ በዝያው ፡ ቦታ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። ግዛታቸው ፡ ግን ፡ ቋራ ፡ ደምብያ ፡ ጭልጋ ፡ እስከ ፡ መተማ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ፡ ከቱርክ ፡ ጋርም ፡ ሁለጊዜ ፡ ይዋጉና ፡ ድል ፡ ያረጉ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡

ቤታቸውም ፡ የጥጋብና ፡ የዘፈን ፡ ቤት ፡ ነበረ ።

እንዲህም ፡ እየተባለ ፡ ይዘፈናል ፡ የክንፉ ፡ ጎራዴ ፡ ጥቁር ፡ የነበረ ። እየቀላ ፡ ሔደ ፡ ቱርክ ፡ እየመሰለ ። ደግሞ ፡ አሽከራቸው ፡ ሁሉ ፡ ገዳይ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።

ሁሉም ፡ ባለ ፡ አሜዋች ፡ አዶ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡ አደራሽ ፡ በተገኙ ፡ ቀን ፡ አሳላፊው ፡ አዶ ፡ አሜዋች ፡ አስሮ ፡ ብርሌ ፡ ከሰጠ ፡ ወድያ ፡ አሸሸ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዘፈን ፡ ይደባለቃል ።

ያልገደለም ፡ ወደ ፡ በረሀ ፡ ይሔዳል ፡ መቸም ፡ አርማጭሆ ፡ ቋራ ፡ ጭልጋ ፡ የዝሆን ፡ አገር ፡ ነውና ፡ እየሔደ ፡ ገድሎ ፡ ይመጣል ።

እንግዴህ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ቴድሮስ ፡ እንመለስ ፡ የመጀርያ ፡ ስማቸው ፡ ካሳ ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ካሳ ፡ ከወንድማቸው ፡ ከደጃች ፡ ክንፉ ፡ ጋር ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ይወድዋቸው ፡ ነበር ።

በኋላ ፡ ፩መለዙሴ ፡ መጥቶ ፡ ለደጃች ፡ ክንፉ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ሊገዛ ፡ ነው ፡ የርሰዎ ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ አይረቡም ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ እንደ ፡ ቅናት ፡ አርገው ፡ ልጅ ፡ ካሳን ፡ ጠሉዋቸው ፡ በመልካም ፡ ዓይን ፡ ትተው ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ አይዋቸው ፡ የደደጃች ፡ ክንፉ ፡ ልጆች ፡ ልጅ ፡ መኰንን ፡ እና ፡ ክንፉ ፡ ጋረድ ፡ ይባሉ ፡ ነበርና ፡ ግዛት ፡ ለልጆቻው ፡ ስለ ፡ ፈለጉ ፡ ነው ።

ልጅ ፡ ካሳ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አያውቁም ፡ ወንድሜ ፡ ይወዱኛል ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡

አንድ ፡ ቀን ፡ ደጅያች ፡ ክንፉ ፡ አዳራሽ ፡ በተገኙ ፡ ቀን ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ሥጋ ፡ ሊያስቈርጡ ፡ እንደ ፡ የቤት ፡ አሽከር ፡ ሁነው ፡ ከደጃች ፡ ክንፉ ፡ ቀረቡ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ቈረጡ ፡ እና ፡ ይበሉ ፡ ጀመሩ ። ዘፈን ፡ ጨወታ ፡ ሲጀመር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ የሚጫወቱትን ፡ ስለ ፡ ማየት ፡ ፊታቸው ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ሳለ ። ደጃች ፡ ክንፉ ፡ የቈረጡት ፡ ጨርሰው ፡ መልሰው ፡ ለመቁረጥ ፡ አቅርብ ፡ ቢልዋቸው ፡ ሳይሰሙ ፡ ቀርተው ፡ ዘገዩ ፡ በኋላ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ሆዳቸውን ፡ በካራ ፡ ሊቀዱዋቸው ፡ ሲቃጡ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ ሸሹ ፡ ሌላ ፡ አስቈራጭ ፡ አሽከር ፡ መጥቶ ፡ ቆመ ።

ልጅ ፡ ካሳም ፡ ከደጀ ፡ ሰላም ፡ መተላለፍያ ፡ ሒደው ፡ ከዝያው ፡ ተኙ ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ከደጀ ፡ ሰላም ፡ ተተከናንበው ፡ ተኝተው ፡ ሳሉ ፡ መኳንንቶች ፡ ሲወጡ ። እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ዛሬ ፡ የወንድማቸውን ፡ ልጅ ፡ በካራ ፡ ሆዱን ፡ ቀደውት ፡ ነበሩ ፡ ተባባሉ ፡ አንዱ ፡ ይገዛል ፡ እያልዋቸው ፡ ቀንተው ፡ ነው ፡ አለ ። አንዱ ፡ ደግሞ ፡ እውነት ፡ ይገዛ ፡ ይሆን ፡ አለ ። ሌሎችም ፡ ርግጥ ፡ ነው ፡ ከብዙ ፡ ሰምተናል ፡ አሉ ፡ ይህነን ፡ ሲናገሩ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ የተኙ ፡ መስለው ፡ ሰሙ ፡ እና ፡ ሌሊቱን ፡ ከድተው ፡ አደሩ ።

ልጅ ፡ ካሳን ፡ ፈልጉ ፡ ቢባል ፡ ታጡ ፡ ጐጃም ፡ ሒደው ፡ የጌታ ፡ አደሩ ፡ መልካም ፡ ጎበዝ ፡ ነበሩና ፡ ጐጃሞች ፡ ወደዱዋቸው ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ጐጃም ፡ አለ ፡ ቢሰሙ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ስደዱልኝ ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ የጐጃም ፡ ገዥም ፡ እ



ርሳቸውም ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ ልጅ ፡ ካሳም ፡ ከዝያው ፡ ተቀመጡ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ጐጃም ፡ ሳሉ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ሞቱ ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ የደጃች ፡ ክንፉ ፡ ሞት ፡ እንደሰሙ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመለሱ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ሞት ፡ አለቀሱ ፡

ጥቂት ፡ ሰንብተው ፡ ሸፍተው ፡ በረሀ ፡ ገቡ ፡ በቋራ ፡ ባገራቸው ፡ በረሀ ፡ ሁነው ፡ በረቱ ። የቋራ ፡ ባላገርም ፡ ወደዳቸው ፡ ጎበዝ ፡ የሆነም ፡ ተከተላቸው ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ግባ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ፡ እምቢ ፡ ሲልዋቸው ፡ ጊዜ ፡ አገሩን ፡ ቋራ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ዘረፉት ። ከተዘረፈ ፡ በኋላ ፡ የቋራ ፡ ባለ ፡ ገር ፡ ሁሉ ፡ ከልጅ ፡ ካሳ ፡ ሸፍታ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ደምያ ፡ እስከ ፡ ጭልጋ ፡ ጎበዝ ፡ መጣላቸው ፡ ከትሁሪር ፡ ሻንቅላም ፡ ወዳጅ ፡ አበጁና ፡ በጣም ፡ በረቱ ፡ ሲበረቱ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጎበዝ ፡ ሹመት ፡ ሰጥቶ ፡ ልጅ ፡ ሰጥቶ ፡ ማኖር ፡ ነው ፡ የሚገባ ፡ ብለው ፡ የራስ ፡ አሊ ፡ መኳንንት ፡ መከሩና ፡ የራስ ፡ አሊ ፡ እት ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ እናታቸው ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ አጋቧቸው ፡ ቋራም ፡ ሹመት ፡ ሊቀበሉ ፡ አምለው ፡ ገቡ ፡ ምሽትም ፡ ሹመት ፡ ሊቀበሉ ፡ አምለው ፡ ካበቁ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ሲገቡ ፡ ወርቅም ፡ ባርያም ፡ ይዘው ፡ ለራስ ፡ አሊና ፡ ለእቴጌ ፡ መነን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ሰጡ ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ምሽታቸውን ፡ አግብተው ፡ አገርም ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ወረዱ ፡ ባገራቸው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተቀምጠው ፡ የቋራ ፡ ግብር ፡ አውጥተው ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ መጡ ፡ ለእቴጌ ፡ መነን ፡ ግብር ፡ ሰጡ ፡ ለመኳንንትም ፡ ብዙ ፡ መቆላመጫ ፡ ሰጡ ፡ በሰፈሩ ፡ ሁሉ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ እያለ ፡ ሁሉ ፡ ወደዳቸው ።

እቴጌ ፡ መነን ፡ ግን ፡ አይወዱዋቸውም ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡ ክፉ ፡ ቆለኛ ፡ ይሉዋቸው ፡ ነበር ።

ከዝያ ፡ በጐንደር ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ሰንብተው ፡ ያሰናብቱኝ ፡ አገሬን ፡ ልወርድ ፡ ብለው ፡ ለእቴጌ ፡ መነን ፡ ተናገሩ ። እቴጌም ፡ እሽ ፡ ቢሆን ፡ ቋራ ፡ የደጃዝማች ፡ አገር ፡ ነውና ፡ በላይህ ፡ የሚሾም ፡ አንድ ፡ ባለነጋሪት ፡ ይዘህ ፡ ሒድ ፡ በሉት ፡ ብለው ፡ ከሹማምቶቸው ፡ ላኩላቸው ። ሹማምቶቹም ፡ እንደእቴጌ ፡ ቃል ፡ ለልጅ ፡ ካሳ ፡ ተናገሩ ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ እንዳይታሰሩ ፡ ፈርተው ፡ ፊታቸው ፡ ሳይቋጥሩ ፡ እሽ ፡ ብለው ፡ እጅ ፡ ነሱ ፡ እና ፡ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ ለኔም ፡ አንድ ፡ በላየ ፡ የሚሆን ፡ ስለ ፡ ሰጡኝ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አሉ ፡ ምነው ፡ ያገሩ ፡ ጥፋት ፡ ያይልኛል ፡ እያሉ ፡ አውቀው ፡ እየተናገሩ ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሔዱ ፡ በነገታው ፡ እንግዳ ፡ ይገፔ ፡ ስሄድ ፡ በድንገት ፡ እንዳይሆንብኝ ፡ መጥን ፡ የሚያዝ ፡ ሰው ፡ ልስደድ ፡ ብለው ፡ ለእቴጌ ፡ ነገሩ ፡ እቴጌም ፡

እሽ ፡ አሉ ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ ባገሩ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳይቆይ ፡ ከብትህ ፡ ፍየልህ ፡ ወደ ፡ ማይገኝ ፡ ስፍራ ፡ አሽሽ ። እህልህም ፡ በጕድጓድ ፡ ክተት ፡ እኔ ፡ ጋላ ፡ ይዤ ፡ ልመጣ ፡ ነኝና ፡ ከተራራው ፡ ስንዘልቅ ፡ በየቤትህ ፡ እሳት ፡ ልቀቅበት ፡ ቡታም ፡ ልቀቅ ፡ ብለው ፡ ለብቻው ፡ ላኩትና ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ የእቴጌ ፡ ደጃዝማች ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ሊመጡ ፡ ናቸውና ፡ እንጀራው ፡ ቅጠል ፡ ጠላው ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ሁኖ ፡ ይቆይ ፡ ፍሪዳም ፡ ማርም ፡ በብዙ ፡ ይዛችሁ ፡ ዳስ ፡ ሰርታቹሁ ፡ ቈዩ ፡ በምን ፡ ጠፋን ፡ እንዳትሉ ፡ በላቸው ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ እና ፡ በነገታው ፡ ወደ ፡ እቴጌ ፡ ሔደው ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ የሚሔደው ፡ ማነው ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ፡ እቴጌም ፡ ደጃች ፡ በለው ፡ ነው ፡ አሉ ። ልጅ ፡ ካሳም ፡ ታጥቀው ፡ ሒደው ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ተሰናበቱ ።

ደጃችም ፡ በለውም ፡ ተነሳ ፡ ወደቋራ ፡ ከርሱ ፡ ጋርም ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ተነሳ ፡ ኃይለኛ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ነፍጥ ፡ ብዙ ፡ ፈረስ ፡ ሰጡት ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ በፊት ፡ መሪ ፡ ሁነው ፡ ቅን ፡ መንገድ ፡ ትተው ፡ ሣር ፡ ውሃ ፡ በማይገኝበት ፡ ዱር ፡ ይዘውት ፡ ቅርቡን ፡ ትተው ፡ በሩቅ ፡ ለፈረስና ፡ ለበቅሎ ፡ የማይመች ፡ ስፍራ ፡ ወሰዱት ፡ ገረድና ፡ አሽከር ፡ በየዱሩ ፡ ተበትኖ ፡ እስኪጠፋ ፡ አደረጉት ። ምነው ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የለም ፡ ቢላቸው ፡ አይዞአቹህ ፡ ቀርበናል ፡ ወደ ፡ አገር ፡ እያሉ ፡ ተስፋ ፡ እየሰጡት ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ትይዩ ፡ ሲዘልቁ ፡ ባላገሩ ፡ በየመንደሩ ፡ እሳት ፡ ለቀቀበትና ፡ ቡታና ፡ እሪታ ፡ ለቀቀው ። ያንጊዜ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ከጋላ ፡ ወታደር ፡ ሁነው ፡ ወደ ፡ ባላገሩ ፡ ይተኰሱ ፡ ነበር ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ የሚያባርሩ ፡ መስለው ፡ ለባላገሩ ፡ ሽሽ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ በለው ፡ ተመለሱ ፡ ይህ ፡ ርጉም ፡ አገር ፡ እንኳ ፡ አይሉኝ ፡ ብለው ፡ ነገሩትና ፡ የዘመዳቸውና ፡ የሳቸው ፡ እህል ፡ ከጕድጓድ ፡ አውጥተው ፡ ሰጡት ፡ ጋላ ፡ እንዳይወርም ፡ ፈራ ።

በነገታው ፡ በመጣነው ፡ መንገድ ፡ መልሱን ፡ ብሎ ፡ የጋላ ፡ ወታደር ፡ ልጅ ፡ ካሳን ፡ ለመነ ፡ ልጅ ፡ ካሳም ፡ ፭ሳምንት ፡ ይቀመጡልኝ ፡ እና ፡ ባላገር ፡ በግድ ፡ አመጣዋለሁ ፡ ብለው ፡ ለመኑት ፡ አውቀው ፡ ጋላም ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ፡ ተነሳ ፡ በመጣው ፡ መንገድ ፡ ይዘውት ፡ ተነሱ ፡ በስከ ፡ ኋላው ፡ ባላገር ፡ እየተከተለ ፡ ፈረስ ፡ በቅሎ ፡ እየገፈፈ ፡ የልጅ ፡ ካሳ ፡ ወታደርም ፡ እኩሉ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ ሁኖ ፡ እኩሉ ፡ ከባላገር ፡ እየሆነ ፡ ጋላ ፡ እስኪጨነቅ ፡ ድረስ ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ ደምብያ ፡ አደረሱትና ፡ የኔ ፡ መከራ ፡ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ ያገኘሁት ፡ ለእቴጌ ፡ ይንገሩ ፡ ብለው ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ተመለሱ ፡ ለበለውም ፡ እ



ንዲህ ፡ አሉት ፡ የሚሆንልኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባላገሩን ፡ በሰርቅ ፡ ላገባው ፡ ነኝ ፡ አገሩ ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ አዩት ፡ ወትሮ ፡ በልመና ፡ ነው ፡ የሚገዛ ፡ ብለው ፡ አሞኙትና ፡ ተመለሱ ፡

በለውም ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ ወደ ፡ እቴጌ ፡ ጐንደር ፡ ገባ ። ነገሩም ፡ መከራውም ፡ ነገረ ፡ እቴጌ ፡ ካሳእሳ ፡ ወዴት ፡ ቀረ ፡ አሉ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ፡ አለ ፡ ምነው ፡ ይዘኸው ፡ ያልመጣህ ፡ ብለው ፡ እቴጌ ፡ ተቈጡ ፡ ልጅ ፡ ካሳም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሸፈቱ ፡ ብርቱም ፡ ሆኑ ፡ በደምብያም ፡ በጭልጋም ፡ እየወጡ ፡ ይዘርፉ ፡ ነበር ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ አስታራቆች ፡ ሰደዱ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ አይዞህ ፡ አገርህን ፡ ጠቅልየ ፡ እሰጥሀ ፡ አለሁ ፡ እቴጌ ፡ እንደ ፡ በደሉህም ፡ ሰምቸ ፡ አለሁ ፡ ብለው ፡ ላኩላቸው ፡ እርሳቸውም ፡ እሽ ፡ ይማሉልኝ ፡ ብለው ፡ አምለው ፡ ገቡ ፡ በኋላ ፡ አገራቸውን ፡ ጠቅልለው ፡ ሰጡዋቸው ፡ ልጅ ፡ ካሳም ፡ በራስ ፡ አሊ ፡ ሰፈር ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ፡ ከዝያው ፡ ሁነው ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ሲያባብሉ ፡ ነበር ፡ ደግሞ ፡ ለመኳንንቶች ፡ ገንዘብ ፡ እየሰጡ ፡ አገራችን ፡ በጋሎች ፡ እየተገዛ ፡ እያሉ ፡ ይማማሉ ፡ ነበር ። ሰው ፡ ደግሞ ፡ እጅግ ፡ ይወዳቸው ፡ ነበር ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ባገሩ ፡ ሁሉ ፡ የእህል ፡ ግብር ፡ ፈሰስ ፡ ጣሉበት ፡ ራስ ፡ አሊ ። ያንጊዜ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ቀለበኛ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ወረዱ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋር ፡ የራስ ፡ አሊ ፡ ቀለበኛ ፡ ብዙ ፡ መኳንንትና ፡ ወታደር ፡ ወረደ ፡ ደግሞ ፡ ቀለብ ፡ የሌላቸው ፡ መኳንንት ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ከርሳቸው ፡ ወረዱ ፡ የአገር ፡ መጥን ፡ ከቤታቸውም ፡ አሰናድተው ፡ ሙሉ ፡ ክረምት ፡ በሲሳይ ፡ አከረሙት ፡ ከወረደው ፡ ሁሉ ፡ ታላላቅ ፡ ሰውም ፡ መሐላ ፡ አደረጉ ፡ እንዲህም ፡ ይላሉ ፡ ለመኳንንቱ ፡ ጥንት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የእስራኤል ፡ መንግሥት ፡ ናት ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞን ፡ ትውልድ ፡ ነው ፡ የሚገዛት ፡ እንዴት ፡ እኛ ፡ ለጋሎች ፡ እንገዛለን ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አባብለው ፡ ከረሙ ፡ በሲሳይም ፡ በገንዘብም ፡ ወታደሩ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከረመ ።

መስቀል ፡ ሲሆን ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ብዙ ፡ ብር ፡ ወርቅም ፡ ባርያም ፡ አስይዘው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ሔዱ ፡ አብሮ ፡ የከረመ ፡ ቀለበኛም ፡ አብሮአቸው ። ራስ ፡ አሊም ፡ ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ ተቀበሉ ።

ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ሰነበቱ ፡ መስቀል ፡ ካለፈ ፡ ወድያ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ጐንደር ፡ ወረዱ ፡ ወደ ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ወደ ፡ አማታቸው ፡ ምሽታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበችም ፡ ከዝያው ፡ ነበሩ ፡ ልጅ ፡ ካሳም ፡ ታጥቀው ፡ ለእቴጌ ፡ እጅ ፡ ነሱ ፡ በክፉ ፡ ዓይን ፡ እንዴት ፡ ነህ ፡ ካሳ ፡ አልዋቸው ። እርሳቸ

ውም ፡ ልባቸው ፡ እየፈራ ፡ በጐንደር ፡ ጥቂት ፡ ሰነበቱ ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ መ
ስለው ፡ እየተዛኑ ፡ ከዝያውም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ የከፋው ፡ አቧበሉ ። ከጥቂት ፡
ቀን ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ኮሶ ፡ ሊጠጡ ፡ ኮሶ ፡ ልጠጣ ፡ ነኝ ፡ ብለው ፡ አስፈ
ቅደው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሒደው ፡ ኮሶ ፡ ጠጡ ። ወደ ፡ አጤ ፡ ዮሐንስ ፡ የ
እቴጌ ፡ ባልም ፡ ኮሶ ፡ ጠጥቸ ፡ ብለው ፡ አሽከር ፡ ላኩ ። ከዝያ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡
ዮሐንስ ፡ ፩ፍሪዳ ፡ ብዙ ፡ እንጀራና ፡ ጠጅ ፡ ሰደዱ ።

እቴጌ ፡ መነን ፡ ግን ፡ ታላቅ ፡ ሥጋና ፡ ፩ገምቦ ፡ ጠጅ ፡ ፴እንጀራ ፡ ሰደዱ ፡
የእቴጌ ፡ ፩መኰንን ፡ ምነው ፡ ፍሪዳ ፡ መስደድ ፡ በተገባ ፡ ነበር ፡ ያለዝያ ፡ በ
ግ ፡ አለ ፡ እቴጌም ፡ ለቈለኛ ፡ ይህ ፡ አነሰው ፡ አሉ ፡ ለልጅ ፡ ካሳም ፡ ፩ወዳጅ ፡
እቴጌ ፡ እንዴህ ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ። የአጤ ፡ ዮሐንስ ፡ የመጣም ፡ የእ
ቴጌ ፡ የመጣም ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ ብለው ፡ ተቀብለው ። የአጤ ፡ ዮሐንስ ፡
ላም ፡ እረዱ ፡ ታላቁ ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ከአገልግል ፡ አግባ ፡ አሉና ፡ የላሚቱ ፡ ሥ
ጋ ፡ ከነ ፡ ሰዋቸው ፡ በልተው ፡ የእቴጌ ፡ ታላቅ ፡ ሥጋ ፡ አሳድርልኝ ፡ አሉ ፤
ልጅ ፡ ካሳ ፡ ግን ፡ ሌሊት ፡ ሳይተኙ ፡ አደሩ ፡ ሰዋቸው ፡ ሁሉ ፡ ሳይተኛ ፡ አደ
ረ ። ለሽዋቸውም ፡ ሁሉ ፡ ከእንዲህ ፡ ያለ ፡ ስፍራ ፡ እንገናኝ ፡ እያሉ ፡ ሰደዱ
ት ፡ ኮሶ ፡ በጠጡ ፡ በ፪ቀን ፡ ምሽታቸውን ፡ ይዘው ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ አ
ገራቸው ፡ በደምብያ ፡ ደረሱ ፡ የተቋጠሩትም ፡ ወታደር ፡ ከዝያው ፡ ተሰበሰበ ፡
ብዙ ፡ ጦርም ፡ ተሰበሰላቸው ።

ያንጊዜ ፡ ካሳ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ የእቴጌ ፡ መነን ፡ ታላቅ ፡ ሥጋ ፡ አምጣ ፡
አሉ ፡ እስቲ ፡ የኔ ፡ አሽከሮች ፡ ይህን ፡ መነን ፡ የሰጠችን ፡ ሥጋ ፡ እንብላውን ፡
አሉ ፡ ሥጋው ፡ ሽቶ ፡ ነበረ ። ያንጊዜ ፡ ፈከሩ ፡ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ፩የናቱ ፡ እ
ኔ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ለጋላ ፡ አልታጠቅም ፡ ብለው ፡ ሽጉጥ ፡ ተኵሰው ፡ ጎራ
ዴ ፡ የመዘዙ ፡ ጊዜ ፡ የርሳቸው ፡ ወታደሮች ፡ ደግሞ ፡ እየፈከሩ ፡ በጎራዴም ፡
በሾተልም ፡ ያችን ፡ ሥጋ ፡ እየቆረጡ ፡ ወደ ፡ በረሀ ፡ እየጣሉ ፡ እንግዲህ ፡
ሥጋይቱ ፡ እንደ ፡ ቈረጥናት ፡ ልባችን ፡ ይቍረጥ ፡ አሉ ።

ከዝያ ፡ ወድያ ፡ በደምብያ ፡ የነበረ ፡ የእቴጌ ፡ መነን ፡ ወታደር ፡ ገፈፉት ፡
በውድ ፡ የሔደ ፡ ሁሉ ፡ አብሮአቸው ፡ ተጓዘ ፡ ፈንጂ ፡ ከደጃች ፡ ክንፉ ፡ ቤት ፡
ሁነው ፡ የወደድኸኝ ፡ ተከተለኝ ፡ የጠላኸኝ ፡ ልቀቅ ፡ የአገሬ ፡ ሰው ፡ ወጥቸ
ልህ ፡ አለሁ ፡ በክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ አይዞህ ፡ ለጋላ ፡ አትታጠቅ ፡ ብለው ፡ አ
ዋጅ ፡ አስነግረው ፡ በፊታቸው ፡ የተገኘ ፡ የእ ፡ መነን ፡ ወታደር ፡ ነፍጡና ፡
መሳርያው ፡ እያስገፈፉ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ወረዱ ።



ወይዘሮ ፡ መነንም ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ እንዲህ ፡ እንዳደረጉ ፡ ሰሙና ፡ ይህ ፡ ፋ
ለኛ ፡ የፍየል ፡ እረኛ ፡ ምንኛ ፡ ጠገበ ፡ ወዴት ፡ አባቱ ፡ ሊገባ ፡ ነው ፡ አሉና
፬የተመረጡ ፡ ደጃዝማቾች ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ለመሔድ ፡ ታዘዙ
ልጅ ፡ ካሳን ፡ ለመውጋት ፡ ተጓዙ ፡ በጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እየተጓዙ ፡ ሰው ፡ እየ
ጨመረ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ዘለቁ ። የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ከቁብታ ፡ ላይ ፡ ሰፍረው
ሲመለከቱ ፡ የጋላ ፡ ወታደር ፡ ዚልቅ ፡ አዩት ። ለወታደራቸው ፡ እንዲህ ፡
ለው ፡ አስለፈፉ ፡ እኔ ፡ መለኸት ፡ እስካስነፋልህ ፡ ድረስ ፡ አትንቀሳቀስ ፡
ለኸት ፡ የተነፋ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የዘገየህ ፡ ለራስህ ፡ እወቅ ፡ ብለው ፡ ነግረው
የጋላ ፡ ወታደር ፡ ሰው ፡ ለመሰብሰብ ፡ ሲዘገይ ፡ ጊዜ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ወደ
ድንኳን ፡ ምሽታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ገብተው ፡ ት
ሽ ፡ እንቅልፍ ፡ ተኝተው ፡ ሳሉ ፡ የጋላው ፡ ጦር ፡ ፊተውራሪው ፡ ሲዘልቅ
ወይዘሮ ፡ ተዋበች ፡ አዩትና ፡ ለባላቸው ፡ ለልጅ ፡ ካሳ ፡ መጡብህ ፡ ታጠቅ
አልዋቸው ፡ ያንጊዜ ፡ አባ ፡ ታጠቅ ፡ ብለው ፡ ፈከሩና ፡ ወደ ፡ ሰልፋቸው
ሔዱ ፡ መልሰው ፡ ደግሞ ፡ መለኸት ፡ ሳይነፋ ፡ የተነሳህ ፡ ለራስህ ፡ ዕወቅ ፡
ም ፡ ብለህ ፡ ተቀመጥ ፡ ብለው ። እርሳቸው ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ገብተወ ፡ ጸሎት
ሲያደርጉ ፡ በጒልበታቸው ፡ ተምበርክከው ፡ ከዛፉ ፡ ወርዳ ፡ ርግብ ፡ ተቀ
ጠችባቸው ፡ ይባላል ፡ እርሳቸውም ፡ ተነስተው ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለአብና
ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ ፊታቸውን ፡ ፫ጊዜ ፡ አማትበው ፡ ወደ
ምድር ፡ ፫ጊዜ ፡ ሰገዱ ፡ እና ። እንግዲህ ፡ ንግርቴ ፡ ደረሰ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡
ልፋቸው ፡ ተመለሱ ። የጋላ ፡ ወታደርም ፡ አሻግሮ ፡ አያቸውና ፡ ጥቂት ፡
ስለው ፡ ታዩት ፡ ሰዋቸውም ፡ ጥቂት ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ይህ
ነው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ የሚገጥም ፡ እያለ ፡ ወረደባቸው ፡ በጣም ፡ እስኪቀርባቸው
ድረስ ፡ የልጅ ፡ ካሳ ፡ ወታደር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ፡ የጋላው ፡ ወታደር
ሲተኵስባቸው ፡ እነዝያ ፡ አልቆሙም ፡ የጋላው ፡ ጦር ፡ ለመወርወር ፡ ሲደርስ
የመይሳ ፡ ልጅ ፡ መለኸት ፡ አስነፋና ፡ በለው ፡ ያሉት ፡ ጊዜ ፡ በጎራዴ ፡ በ
ተል ፡ ቢያያዘው ፡ ነፍጣቸው ፡ ሁሉ ፡ ቋድእና ፡ ጥቂት ፡ ባለ ፡ ቡላድ ፡ ነበረ
የልጅ ፡ ካሳ ፡ የእጃቸው ፡ ከብሱል ፡ ፪አፍ ፡ ነበረ ፡ ሽጉጣቸው ፡ በደንጊያ ፡
ሚተኰስ ፡ ባለ ፡ ቡላድ ፡ ነበረ ፡ ፪ሽጉጥ ፡ ታጥቀው ፡ ነበር ፡ ማኸል ፡ ገብ
ው ፡ ሁለት ፡ አይነተኞች ፡ ጣሉና ፡ ተማረክ ፡ በለው ፡ ያሉት ፡ ጊዜ ፡ የርሳ
ው ፡ ወታደር ፡ በጎራዴ ፡ በጦር ፡ በሾተል ፡ ተሻማው ። የጋላ ፡ ወታደርም
የሚሞትም ፡ የሚማረክም ፡ ሆነ ፡ ሸሽተኛም ፡ ወደ ፡ ደምብያ ፡ አድርጎ ፡ ሸሽ
ልጅ ፡ ካሳም ፡ እስከ ፡ ደምብያ ፡ ወጡ ፡ ከዝያም ፡ ከዝያውም ፡ ሰፈሩ ። እቴ

ም ፡ መልሰው ፡ ክተት ፡ አሉ ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ አሊም ፡ ጦር ፡ ስደድልኝ ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ ራስ ፡ ዓሊም ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ ጦር ፡ ስደዱ ፡ ብለው ፡ ላኩ ። ደጃች ፡ ውቤም ፡ ፊተውራሪ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፡ ሹም ፡ ተምቤን ፡ ወለጊርጊስ ፡ የሚባሉ ፡ አዘው ፡ ሰደዱ ፡ የእቴጌም ፡ ጦር ፡ ሁነው ፡ ደምብያ ፡ ላይ ፡ ገጠሙ ። የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ድል ፡ አደረጋቸው ፡ የሚሞት ፡ ሞተ ፡ የሚማረክም ፡ ተማረከ ፡ ምርኮኛውም ፡ የወደድኸኝ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ተቀመጥ ፡ ያልወደድህ ፡ አገርህ ፡ ሒድ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ነግረው ፡ ምርኮኛ ፡ አሰናብተው ፡ ሰደዱትና ፡ የደጃች ፡ ውቤም ፡ ቁስለኛ ፡ ሁሉ ፡ ምርኮኛውም ፡ ሰሜን ፡ ገባ ።

የወይዘሮ ፡ መነንም ፡ ምርኮኛና ፡ ቁስለኛ ፡ ጐንደር ፡ ገባ ።

ወደ ፡ ትግሬም ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ወሬ ፡ ተወራ ። እንዲህ ፡ እየተባለ ። ካሳ ፡ ቋራ ፡ የሚባል ፡ ኀይለኛ ፡ ሽፍታ ፡ ወጥቶ ፡ የራስ ፡ አሊም ፡ የእቴጌ ፡ መነንም ፡ የደጃች ፡ ውቤም ፡ ጦር ፡ ሒዶበት ፡ ተዋግቶ ፡ ሁሉን ፡ ድል ፡ አረጋቸው ፡ እየተባለ ፡ ተወራ ።

በዝያው ፡ ጊዜ ፡ በትግሬ ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ ተለቀሰ ።

ራእሲ ፡ ዃሊ ፡ ልቓቑ ፡ በለሳ ።

ፍሩይ ፡ ሰብአይ ፡ እንካብ ፡ ተወልደ ፡ ካሳ ።

ደጅያት ፡ ውበውን ፡ ልቓቑ ፡ የፀገዱ ፡

ፍሩይ ፡ ሰብአይ ፡ ካሳ ፡ እንካብ ፡ ተወልደ ። መልሶም ፡ ሲመክር ፡ አለቀሰ ፡ ካሳ ፡ ወደይውን ፡ አይትበል ፡ ምልስ ፡ ምልስ ። ሹሉ ፡ ሻኧ ፡ ዐይርከብን ፡ ሰኑይ ፡ ሠሉስ ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ ።

ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡

ክልተ ፡ ተስቶት ፡ ሳልሣዮም ፡ መብረ ። አንታ ፡ እዙ ፡ ዝራብኧ ፡ እዙይኸ ፡ አበይ ፡ ነበረ ፡

ከምዚ ፡ ሔዚ ፡ ግዳ ፡ ከምተሶረ ፡ አበይሞ ፡ እንተ ፡ ገበረ ።

የአቢ ፡ ደአ ፡ የሎን ፡ አና ፡ ፈንደረ ። አለ ።

ይህን ፡ ያለቀሰ ፡ የናዕዱር ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ሕዝቅያስ ፡ ይባላል ።

ሌላም ፡ ብዙ ፡ ልቅሶ ፡ ለደጃች ፡ ውቤ ፡ አልቅሶ ፡ ነበርና ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ሊቀጡት ፡ አምጡት ፡ ቢባል ፡ አኩሱም ፡ አስደውሎ ፡ አመለጣቸው ።

ከዝያ ፡ በኋላ ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ጐንደር ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ ክተት ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ አስነግረው ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ተነሡ ።

ሠራዊታቸውም ፡ ብዙ ፡ ነበረ ። ይላሉ ፡ ደጃች ፡ ካሳም ፡ የእቴጌ ፡ መነን ፡



ከጐንደር ፡ መነሳት ፡ ሰላይ ፡ መጥቶ ፡ ነገራቸውና ፡ ደጃች ፡ ካሳም ፡ ጦራቸውን ፡ ሰበሰቡ ፡ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ፈከሩ ።

ይች ፡ ቆፍጣጣ ፡ ጋላ ፡ እኔ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ከጦር ፡ ወግቸ ፡ ባቄላ ፡ ያልስፈጩኋት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ታዘቡኝ ፡ አሽሮቸ ፡ ብለው ፡ ፈከሩ ።

ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ይህ ፡ ቆለኛ ፡ ወዴት ፡ አባቱ ፡ ሊገባ ፡ ነው ፡ ይሆን ፡ እያሉ ፡ በንቀት ፡ ቃል ፡ እየተሳደቡ ፡ ወደ ፡ ቋራ ፡ ዘለቁ ።

ከደጃች ፡ ካሳ ፡ ሰልፍም ፡ ተያዩ ። እቴጌም ፡ ሰልፉን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ፍየል ፡ እረኛ ፡ እንጅ ፡ አይፍርም ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ሊዋጋ ፡ ቁመዋል ፡ ብለው ። ሰልፈኛውን ፡ በየሰልፍህ ፡ እለፍ ፡ በለው ፡ አሉና ፡ እቴጌ ፡ መነን ፡ ጦራቸውን ፡ አሳለፉት ፡

የመይሳ ፡ ልጅም ፡ የኔ ፡ ሰልፍ ፡ የሆንህ ፡ መለኸት ፡ ሳትሰማ ፡ አትነሳ ፡ አሉት ።

መለኸት ፡ ሲነፋ ፡ ግን ፡ ፊትከን ፡ ሳታዞር ፡ ግባበት ፡ ብለው ፡ አስለፈፉና ፡ የእቴጌ ፡ መነን ፡ ጦር ፡ እስቲቀርብ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆይተው ፡ በጣም ፡ ሲቀርብ ፡ አይተው ፡ መለኸት ፡ ንፉ ፡ ያሉ ፡ ጊዜ ፡ የደጃች ፡ ካሳ ፡ ወታደር ፡ እየሰልፉ ፡ ተነሥቶ ፡ ይተኩስ ፡ ጀመረ ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ እየገባ ፡ በጎራዴም ፡ በሾተልም ፡ ተያያዘው ፡ የመይሳ ፡ ልጅም ፡ የሚያምኑዋቸው ፡ የተመረጡ ፡ ጅግኖች ፡ ይዘው ፡ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ እቴጌ ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ቢሄዱ ፡ አንድ ፡ ጅግና ፡ ጎበዝ ፡ እቴጌ ፡ መነንን ፡ ከጭናቸው ፡ ላይ ፡ ወግቶ ፡ ማርኮ ፡ ሲመጣ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ አገኙትና ፡ እንኳ ፡ ቀናህ ፡ ብለው ፡ እቴጌን ፡ የሚጠብቅ ፡ ብዙ ፡ ዘበኛ ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ሽሽተኛው ፡ ተማረከ ፡ በለው ፡ እያሉ ፡ ተከሉ ። በዝያው ፡ ጊዜ ፡ የሚማረክም ፡ ተማረከ ፡ የሚሞትም ፡ ሞተ ። ወይዘሮ ፡ መነንም ፡ የፍየል ፡ እረኛ ፡ እያሉ ፡ ስለ ፡ ተሳደቡ ፡ በዋሻ ፡ ገብተው ፡ ታስረው ፡ ባቄላ ፡ ፈጭ ፡ ኋላም ፡ መቅደላ ፡ ታስረው ፡ ሞቱ ፡ ባፍ ፡ ይጠፉ ፡ በለፈለፉ ፡ የሚሉት ፡ ነውና ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ አግኝተው ፡ ሞቱ ።

ይህን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ጐጃም ፡ ሒደው ፡ ከደጃች ፡ ጎሹ ፡ ጋር ፡ ተዋጉ ፡ የጐጃም ፡ ሰውም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሞተ ፡ ደጃች ፡ ጎሹም ፡ ተማረኩና ፡ ታሰሩ ። ኋላም ፡ መቅደላ ፡ ታስረው ፡ ነበር ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጦርነት ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ ሲዋጉ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ እየሰሙ ፡ ለካሳ ፡ አልጭንለትም ፡ ብለው ፡ በንቀት ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ካሳ ፡ መልክተኛ ፡ ሰደ

ዱ ፡ እቴጌ ፡ መነንን ፡ ፈትተህ ፡ ስደድልኝ ፡ አንተም ፡ ግባ ፡ በቀረው ፡ እኔ ፡ ል
መጣብህ ፡ ነኝ ፡ ብለው ።

ልጅ ፡ ካሳም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፈከሩና ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ም
ላሽ ፡ ሰደዱ ። ለእቴጌ ፡ የምታስብ ፡ ላንተ ፡ ምን ፡ ይዘህለት ፡ ነው ፡ እለቃለሁ ፡
ብትል ፡ አልጋየን ፡ ልቀቅ ፡ አለቅም ፡ ያልህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሰፌ ፡ ሜዳ ፡ ይዘ
ህ ፡ ቆየኝ ፡ ብለው ፡ ላኩና ። በስተ ፡ ወድያው ፡ ጦራቸውን ፡ ሰበሰቡና ፡ ወደ ፡
ደብረ ፡ ታቦር ፡ ተነሱ ። ራስ ፡ አሊም ፡ የልጅ ፡ ካሳን ፡ መነሳት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡
ሠራዊታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ አስከትተው ፡ ተሰልፈው ፡ ተ
ቀመጡ ፡ መቸም ፡ ሠራዊታቸው ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ ንቀው ፡ ነበር ። የመይሳ ፡
ልጅም ፡ በአሞራ ፡ ገደል ፡ አድርገው ፡ ጠጉር ፡ ወደ ፡ ሚባል ፡ ገስግሰው ፡ ብ
ቅ ፡ አሉና ፡ ሰፈሩ ። በነጌታው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ኢየሱስ ፡ ጥግ ፡ ይዘ
ው ፡ ትብልብል ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ ንብ ፡ ወደ ፡ ጃንሜዳ ፡ ዘለቁ ። ሰዋቸው ፡ ጥቂ
ት ፡ ሁኖ ፡ በርሳቸው ፡ ጦር ፡ ብዛት ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ አሻግረው ፡ አዩና ፡ ራስ ፡ አሊ ፡
እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ሠርገኛ ፡ እንዳንለው ፡ በዛ ፡ ጦረኛ ፡ እንዳንለውም ፡
አነሰ ፡ ብለው ፡ በንቀት ፡ ተናገሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ጦራቸውን ፡
በሥርዓት ፡ አሰለፉና ፡ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ ገቡና ፡ ይራኰቱ ፡ ጀመር ፡ በስከ ፡ ወ
ድያው ፡ የራስ ፡ ዓሊ ፡ ጦር ፡ ድል ፡ ሆነ ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ ራስ ፡ አሊ ፡ በፈረስ ፡
ሁነው ፡ ሸሹና ፡ የጁ ፡ ገቡ ። የቀረው ፡ ሠራዊታቸውም ፡ የሚሞትና ፡ የሚማ
ረክ ፡ ሆነ ። በዝያን ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ እንግሊዞች ፡ ከራስ ፡ አሊ ፡ ጋር ፡ ተጌን
ተው ፡ ተማረኩ ፡ ስማቸውም ፡ ባሻ ፡ ብላውደንና ፡ ምስተር ፡ ቤል ፡ ናቸው ፡
ቤል ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ የተባሉ ፡ ናቸው ። ራስ ፡ አሊን ፡ ድል ፡ አደ
ረጉና ። አዋጅ ፡ አስነገሩ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ርስት ፡ አለኝ ፡ ጉልት ፡ አለኝ ፡
የምትል ፡ የሴት ፡ ወይዘሮ ፡ የወንድ ፡ መኰነን ፡ በምን ፡ ተነቀልሁ ፡ እንዳት
ል ፡ ግባ ፡ በየአባትህ ፡ ሰጥቸሀለሁ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ነግረው ፡ ከዝያው ፡ በ
ደብረ ፡ ታቦር ፡ ሰፍረው ፡ ከረሙ ። ከዝያው ፡ ሁነው ፡ የቤጌምድርና ፡ የዋድ
ላ ፡ የደላንታ ፡ ሰው ፡ ገባላቸው ፡ የራስ ፡ ዓሊ ፡ ሸሽቶ ፡ የነበረም ፡ ገባ ፡ ከዝ
ያው ፡ ሁነውም ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ላኩ ። ይግቡ ፡ በቀረው ፡ በጎ ፡ ነገር ፡
አይሆንም ፡ ብለው ፤ ደጃች ፡ ውቤም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ አንተ ፡
አያ ፡ ምንኛ ፡ የጠገበ ፡ ነው ፡ ሳልዋጋ ፡ ይገባል ፡ ብሎኝ ፡ ነው ፡ አልገባም ፡ በ
ለው ፡ ብለው ፡ ምላሽ ፡ ሰደዱ ።

ከዚህ ፡ ወድያ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ መስቀልን ፡ ውለው ፡ በየ
አገሩ ፡ ሁሉ ፡ ክተት ፡ አሉትና ፡ ላስታም ፡ ቀኝ ፡ መጨት ፡ ግራ ፡ መጨት ፡



ዋድላ ፡ ደላንታ ፡ ከጨጬሆ ፡ በታች ፡ ከተተ ፡ የጁና ፡ ወሎ ፡ ሸዋ ፡ ሲቀር ፡
አስከተቱና ። አዋጅ ፡ አስነገሩ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ከኔ ፡ የተለየህ ፡ ለራስህ ፡ እ
ወቅ ፡ በምን ፡ ጠፋሁ ፡ እንዳትል ፡ አይዞህ ፡ ወታደር ፡ እኔ ፡ ደስ ፡ ከሚልህ ፡ አ
ገባህ ፡ አለሁ ፡ እኔ ፡ በመራሁህ ፡ ተጓዝ ፡ ስሜን ፡ ስሜን ፡ እነግርህ ፡ አለሁ ፡
ብለው ፡ ወደ ፡ አምባጫራ ፡ ተጓዙ ፤ ደጃች ፡ ውቤም ፡ ግዛታቸው ፡ ሁሉ ፡ ክ
ተት ፡ ብለው ፡ አስከተቱ ፡ ግዛታቸውም ፡ ባምብሎ ፡ ምላሽ ፡ ወገራ ፡ ስሜን ፡
ወልቃይት ፡ ጠለምት ፡ ትግሬ ፡ ሁሉን ፡ አስከተቱና ። እቃቸውም ፡ ሁሉ ፡ ወ
ደ ፡ ጠዘን ፡ አምባ ፡ አገቡ ። ወርቅና ፡ ብር ፡ እህል ፡ ሸማ ፡ ማርም ፡ ቅቤም ፡
ምንጣፍ ፡ መከዳ ፡ ዋንጫ ፡ ብርሌ ፡ ብርጭቆ ፡ ካራ ፡ አቆማዳ ፡ ማጭድ ፡ ገጀ
ሞ ፡ ወረንጦ ፡ እሾህ ፡ አጋም ፡ ቅባኑግ ፡ ከሰል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ በጠዘን ፡ አ
ምባ ፡ አገቡ ፡ የመይሳ ፡ ልጅም ፡ ከአምባ ፡ ጫራ ፡ ተጉዘው ፡ ወገራ ፡ ሰፈሩ ።
ከዝያው ፡ ሁነውም ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ በፍቅር ፡ ይግቡ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ፡
ደጃች ፡ ውቤም ፡ አልገባም ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ላኩ ። ከዝያ ፡ በ
ኋላ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ከወገራ ፡ ወደ ፡ ስሜን ፡ ተጓዙ ፡ አባ ፡ ማሬ ፡ ውቤም ፡ በ
ስሜን ፡ ደብረ ፡ ስጌ ፡ ወገን ፡ ተሰልፈው ፡ ቆይተው ፡ ተታኰሱ ፡ በስከ ፡ ወድያ
ው ፡ ቈሰለው ፡ ተማረኩ ፡ ልጆቻቸውም ፡ ደጃች ፡ ጓንጉልና ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡
ተማረኩ ። ደጃች ፡ ውቤን ፡ የማረከው ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ይዞአቸ
ው ፡ ሔደና ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ እንኳ ፡ ቀናዎ ፡ አልዋቸው ። እሳቱ ፡ የመይሳ ፡
ልጅ ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ወረፍዋቸው ፡ አ
ንት ፡ ቆፍጣጣ ፡ ቊርጥማታም ፡ ሽማግሌ ፡ በክብረት ፡ ግባ ፡ ብየ ፡ ብልክብህ
ምን ፡ ብለህ ፡ ሰደብኸኝ ፡ አሁንም ፡ ቶሎ ፡ ነፍጤና ፡ ገንቤን ፡ አግባ ፡ አልዋ
ቸው ።

ደጃች ፡ ውቤም ፡ እግዜር ፡ ያሳየዎ ፡ የነበረኝ ፡ ነፍጥና ፡ ገንዘብ ፡ አንድ ፡
ሳያመልጥ ፡ ከእጀዎ ፡ ገባ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ አለኝ ፡ አሉና ፡ ተናገሩ ። በስተ ፡ ወ
ድያው ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ የግድ ፡ ትሰጠኛለህ ፡ አሉና ፡ ወስዳችሁ ፡ እሰሩ ፡ ብለ
ው ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ በጭራ ፡ ገመድ ፡ ታሰሩ ፡ እጃቸው ፡ ደም ፡ እስቲወጣ ፡
ድረስ ፡ ከአገር ፡ ከዋሻ ፡ የነበረ ፡ ሰጡ ፡ መልሰው ፡ ደግሞ ፡ ታሰሩ ፡ በጥኑ ፡ ፡፡፡
አምባ ፡ አልሰጥም ፡ ብለው ፡ ነበረ ፡ የሚያልፍላቸው ፡ መስሎአቸው ። እስራ
ቱ ፡ ሲጠናባቸው ፡ ጊዜ ፡ አምባውን ፡ ይቀበሉኝ ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ ደጃች ፡ ካሳ
ም ፡ ወደ ፡ አምባው ፡ ሰው ፡ ሰደው ፡ ቅድም ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ በየአይነ
ቱ ፡ እሾህ ፡ ሳይቀር ፡ አንድ ፡ ጋን ፡ መርፌ ፡ ተገኘ ፡ ይላሉ ፡ በዝያውም ፡ አ
ምባ ፡ ብዙ ፡ የታሰሩ ፡ መኳንንት ፡ እስሮች ፡ ነበሩ ፡ አስፈቱዋቸው ። ደጃች ፡

ውቤ ፡ ማሰርና ፡ መውረስ ፡ መቍረጥ ፡ ይወዱ ፡ ነበርና ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡
አስረው ፡ በስጨነቅዋቸው ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ የልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ገጠ
ሙ ፡ መከራን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ እንደያ ፡ ሳቀልው ፡ እንዲህን ፡ ይከብዳል ፡ ለተ
ሸከመው ፡ አሉ ።

ከአምባ ፡ ጠዝን ፡ የነበረውን ፡ እቃ ፡ ተቀብለው ፡ ታበቁ ፡ ወድያ ፡ ደጃች ፡
ውቤን ፡ ጥራ ፡ ብለው ፡ አመጡዋቸውና ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጠየቅዋቸው ፡ ይህ ፡
ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ይሆነኝ ፡ ብለው ፡ ከአምባ ፡ አኖሩት ፡ አልዋቸው ፡ ደ
ጃች ፡ ውቤም ፡ ለክፉ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ፡ ብየ ፡ አሉ ። አጤ ፡ ቴድሮስም ፡ እን
ኪያው ፡ ከዛሬ ፡ የሚከፋ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ አለ ፡ የማይበሉት ፡ ንፍገት ፡ ነው ፡ እ
ንጅ ፡ ወይ ፡ አስቀድሞ ፡ መብላት ፡ ወይም ፡ ለወታደር ፡ መስጠት ፡ ይሻል ፡ ነ
በር ፡ እንጂ ፡ ያኖሩት ፡ ከበሉ ፡ ምን ፡ ክፉ ፡ ቀን ፡ አለ ፡ አልዋቸው ።

ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ደጃች ፡ ውቤን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ ነ
ገሡ ፡ በስሜን ፡ ደብረ ፡ ስጌ ፡ ድል ፡ ባደረጉ ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ በየካቲት ፡
፫ ፡ አቡነ ፡ ሰላማ ፡ ጳጳሱም ፡ ከደጃች ፡ ውቤ ፡ ተገኙና ፡ ስማቸው ፡ ደጃች ፡
ካሳ ፡ የነበረ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ተባሉ ። አስቀድ
መው ፡ ትንቢት ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ ስሜን ፡ ስሜን ፡ እነግርህ ፡ አለሁ ፡ ብለ
ው ፡ በስሜን ፡ ስማቸው ፡ ተለወጠ ። የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከቀረ ፡ በ
፸ዓመት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በነገሡበት ፡ ደብረ ፡ ስጌ ፡ ሁነው ፡ አዋጅ ፡ አስነገ
ሩ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ አራሽ ፡ እረስ ፡ የወንድ ፡ መኰንን ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ባ
ለ ፡ ጉልት ፡ ባለ ፡ ርስት ፡ እየ ፡ አባትህ ፡ ሰጥቸህ ፡ አለሁ ፡ ነጋዴም ፡ ነግድ ፡
በተቀማህበት ፡ ቦታ ፡ ደንጊያ ፡ ደርድረህ ፡ ወደኔ ፡ ና ። ተወኝ ፡ ሌባ ፡ ተ
ወኝ ፡ ወምበዴ ፡ ግባ ፡ እቀማለሁ ፡ እሰርቃለሁ ፡ ብትል ፡ ለአካልህ ፡
እዘንለት ። አይዞህ ፡ ድኃ ፡ አይዞህ ፡ ወታደር ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ በክርስቶ
ስ ፡ ኀይል ፡ ወጥቸልህ ፡ አለሁ ። የኢያሱ ፡ ይብቃ ፡ ብለው ፡ አስነግረ
ው ፡ ከስሜን ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተጓዙ ፡ ጐንደርም ፡ ከጥንት ፡ ከነገሥታቱ ፡
ግምብ ፡ ገብተው ፡ የጐንደር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በእልልታ ፡ በደስታ ፡ ተቀበለዎ ።
ከዝያው ፡ ከመናገሻው ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ ብዙ ፡ ፍሪዳ ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ታር
ዶ ፡ ጠጅም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ሁኖ ፡ ለድኆችም ፡ ብዙ ፡ ምጽዋት ፡ ሰጥተው ፡
ዘውደዎን ፡ አስመረቁና ። ከጐንደር ፡ ተነስተው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ተጓ
ዙ ፡ ከዝያው ፡ ጥቂት ፡ ሠራዊተዎ ፡ እስኪሰበሰብ ፡ ሰነበቱና ፡ ከዝያው ፡ ሁነ
ው ፡ ወደ ፡ ወሎና ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ወደ ፡ የጁም ፡ ግቡ ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ ሁሉም ፡
አንገባም ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ አሉ ፡ ፫ቱ ፡ አገር ። የቀረው ፡ ግን ፡ ጨርሶ ፡ ገባ ።



ከዝያ ፡ ወድያ ፡ በጨጨሆ ፡ በር ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ የጁ ፡ ወልድያ ፡ ላይ ፡ ሄደ
ው ፡ ሰፈሩና ፡ አልገባም ፡ ብሎ ፡ ያመጠውን ፡ እየዘረፉ ፡ ቤቱንም ፡ እህሉን
ም ፡ ቢቃጥሉት ፡ የግድ ፡ ገባላቸው ፡ ከዝያው ፡ የየጁ ፡ ባለ ፡ አባት ፡ ሹመው ፡
ወደ ፡ ወሎ ፡ ሔዱ ፡ የወሎ ፡ ሰው ፡ አንገባም ፡ ብሎ ፡ ሸፍታና ፡ ወያኔ ፡ እየ
ሆነ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አስቸገረዎ ፡ በወራሪ ፡ የሔደውም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እየገደለ ፡
ሲያስቸግራቸው ፡ ጊዜ ። የተማረከውን ፡ የወሎ ፡ ሰው ፡ እያስያዙ ፡ ሁለት ፡
እግሩና ፡ ሁለት ፡ እጁ ፡ እየቆረጡ ፡ በአንገቱ ፡ ላይ ፡ እያሰሩ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሰ
ደዱት ፡ የወሎ ፡ ሰው ፡ እነዝያ ፡ የተቈረጡትን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደነገጠ ፡
አጥብቆ ፡ ተሸበረ ። ደግሞ ፡ የወሎ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ማጉረስስ ፡ ምሽ
ቱ ፡ ታጉርሰው ፡ ቂጡን ፡ በምን ፡ ያብሰው ፡ አለ ። ንጉሡም ፡ አዋጅ ፡ ነገሩ ፡
ግባ ፡ አልገባም ፡ ያልህ ፡ ለወንድ ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ ለሴትም ፡ ጡትዋን ፡ እ
ቆርጣለሁ ፡ ብለው ፡ አስነገሩና ፡ የወሎ ፡ ሰው ፡ በግድ ፡ በጭንቅ ፡ ገባ ። ነፍስ ፡
የገደልህ ፡ ቋንጃ ፡ የቈረጥህ ፡ ሞሬህ ፡ አለሁ ፡ ግባ ፡ አልገባም ፡ ብትል ፡ ለአ
ከላትህ ፡ እዘንለት ፡ ሹም ፡ ሰጥቸህ ፡ አለሁ ፡ በሹምህ ፡ ታዘዝ ፡ ብለው ፡ አዋ
ጅ ፡ አስነግረው ። ወደ ፡ ሸዋ ፡ ተጓዙ ። የሸዋ ፡ ሰውም ፡ አንገባም ፡ ብሎ ፡
ተዋጋቸው ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ድል ፡ አደረጉ ፡ በዝያም ፡ ብዙ ፡ ነፍጥና ፡ ብ
ዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኙ ፡ አጤ ፡ ምንሊክም ፡ ልጅ ፡ ነበሩና ፡ ወደ ፡ አጤ ፡ ቴዎድ
ሮስ ፡ ገቡ ፡ የሸዋ ፡ ሰው ፡ ሁሉም ፡ ገባ ፡ በሸዋም ፡ የሚሾም ፡ ሹመው ፡ ግባ ፡
አይዞህ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ አስነግረው ፡ አጤ ፡ ምንሊክን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡
ይዘው ፡ ወደ ፡ ቤጌምድር ፡ ተመለሱ ። ወሎና ፡ ሸዋ ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ መሬት ፡
ቀጥ ፡ ብላ ፡ ተገዛች ፡ በትግሬም ፡ በአማራም ፡ ዘማቹም ፡ መኳንንቱም ፡ ባ
ላገርም ፡ ገባ ። ንጉሡ ፡ በአማራ ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ የትግሬ ፡ ሰው ፡ ከቤቱ ፡ ሁኖ ፡
ንጉሥን ፡ አትሙ ፡ ይሰሙናል ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፡
ይሰማሉ ፡ መባሉ ፡ አልባሌ ፡ ወታደር ፡ መስለው ፡ ያልረባ ፡ ልብስ ፡ እየለበሱ ፡
ሰው ፡ የሚናገረውን ፡ ንጉሥን ፡ የሚያማውን ፡ የተበደለውንም ፡ በደል ፡ ከ
ባልጀሮቹ ፡ ጋር ፡ ሲያወጋ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ይሰሙና ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ምነው ፡
እንዲህ ፡ ብለህ ፡ አማኸኝ ፡ ብለው ፡ የተናገረውን ፡ ሁሉ ፡ ይነግሩታል ፡ ክፉ ፡
ነገር ፡ የተናገረውን ፡ ወቅሰው ፡ ይጣሉታል ። መልካም ፡ የተናገረውን ፡ ይሾ
ሙት ፡ ይሸልሙታል ፡ ገንዘብም ፡ ይሰጡታል ። በዚህው ፡ ልማደዎ ፡ አጤ ፡
ቴዎድሮስ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጋቢ ፡ መሳይ ፡ ያደፈ ፡ ለብሰው ፡ በትር ፡ መሳይ ፡
በእጀዎ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ መስክ ፡ ወረዱ ፡ ከዝያው ፡ መስክ ፡ ፲፳የሚሆኑ ፡ ወ
ታደሮች ፡ ተሚጫወቱቱ ፡ ሔዱና ፡ እንዴት ፡ ዋላችሁ ፡ ብለው ፡ አብረው ፡

ተቀመጡ ፡ ንጉሡም ፡ የቧልትም ፡ የቂም ፡ ነገርም ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር ፡ እነዝያ ፡ ወታደሮችም ፡ የፈሪም ፡ የጅግናም ፡ የእብድም ፡ የጭምትም ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ፡ አጤም ፡ አብረው ፡ ይስቃሉ ። ሁሉን ፡ ተጫውተው ፡ አብቅተው ፡ ሊለያዩ ፡ አቅራብያ ፡ አንድ ፡ ድኋ ፡ ወታደር ፡ ከነዝያ ፡ ከተቀመጡት ፡ ለንጉሡ ፡ ሐሜት ፡ ጀመረ ፡ መቸም ፡ ድኋ ፡ ወታደር ፡ ሀሜት ፡ ልማድ ፡ ነውና ፡ ወይም ፡ ላይጠቀም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ እኒህ ፡ ንጉሥ ፡ የሚመስል ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ ለጋስ ፡ ይመስላሉ ፡ ንፉግ ፡ ናቸው ፡ ይሄው ፡ እኔ ፡ አስር ፡ አመት ፡ ሙሉ ፡ አገልግየ ፡ እኒህ ፡ ርጉም ፡ ንጉሥ ፡ ምንምን ፡ አልሰጡኝም ፡ በእላቂ ፡ ጨርቅ ፡ ታንቄ ፡ እኖራለሁ ፡ እንጀራ ፡ እንኳ ፡ እየራበኝ ፡ እቀመጣለሁ ፡ አለና ፡ ተናገረ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁሉም ፡ እየጉዳታቸው ፡ ተጫውተው ፡ ሲያበቁ ፡ ደህና ፡ ሁኑ ፡ ተቧብለው ፡ እየሰፈራቸው ፡ ሔዱ ።

አጤ ፡ ቴድሮስም ፡ ያያማቸው ፡ ወታደር ፡ እንዳያውቃቸው ፡ በሩቅ ፡ ሁነው ፡ ተመልክተው ፡ ቤቱን ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አደራሽዎ ፡ ገቡ ።

ከዚህ ፡ ወድያ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፪ደቧይ ፡ አገልግል ፡ መልኩ ፡ መጠኑ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ አሰፍተው ። በየባሕር ፡ አረብ ፡ አስከፍፈው ። በአንዱ ፡ ሙሉ ፡ ብር ፡ አደረጉበት ፡ አንዱ ፡ ግን ፡ ባዶውን ። ሁለቱን ፡ ቈለፉና ፡ የ፪ቱም ፡ አገልግል ፡ አንድ ፡ መልክ ፡ አደረጉና ፡ አንዱ ፡ በቀኝ ፡ አንዱ ፡ በግራ ፡ ከአልጋው ፡ አጠገብ ፡ አስቀመጡና ፡ ያነን ፡ ወታደር ፡ ቤቱን ፡ በሩቅ ፡ ላሽከር ፡ አመልክተው ፡ ወደርሳቸው ፡ አስመጡት ፡ እርሱም ፡ ምን ፡ ተሰምቶብኝ ፡ ይሆን ፡ መጠራቴ ፡ እያለ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ቀረበ ። ንጉሡም ፡ ገና ፡ እንዳዩት ፡ አንተ ፡ ፲አመት ፡ አገልግየ ፡ ከድኅነቴ ፡ አላወጡኝም ፡ የእለት ፡ እራት ፡ አጥቸ ፡ እህል ፡ አፌ ፡ እያማረው ፡ ርቦኝ ፡ አድራለሁ ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ ባንገቴ ፡ ጠምጥሜ ፡ እኖራለሁ ፡ እያልህ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ታሳጣኝ ፡ አለህ ። እግዜር ፡ ባይሰጥህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንጅ ፡ እንዴት ፡ ፲ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ታገለገልኸኝ ፡ እንጀራ ፡ ሳላሳልፍልህ ፡ በቀረሁ ። አሁንም ፡ እስቲ ፡ እግዜር ፡ ታለልህ ፡ ሃብትህን ፡ ሞክረው ፡ አሉና ፡ ይህው ፡ ፪አገልግል ፡ ቀርቦልሃል ። ባንዱ ፡ ብር ፡ ሞልቶዋል ። አንዱ ፡ ግን ፡ ባዶ ፡ ነው ። አሁንም ፡ በእጅህ ፡ ሳትመዝን ፡ አይንህ ፡ የመረጠውን ፡ አንሳ ። ብር ፡ ያለውን ፡ ያነሳህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እውነት ፡ እኔ ፡ የበደልሁህ ፡ ነኝና ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ፲እጅ ፡ እክስሕ ፡ አለሁ ። ፲አመት ፡ ሙሉ ፡ ስለ ፡ በደልሁህ ። ባዶውን ፡ የመረጥህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ በሃብትህ ፡ እዘን ፡ አምላክ ፡ ባይሰጥህ ፡ ነውና ፡ በኔ ፡ አትዘን ፡ አትማኝም ፡ አሉት ፡ ያድኋ ፡ ወታደርም ፡ አገኝን ፡ አላገኝም ፡ እያለ ፡ ጉልበቱ ፡ እየ



ተንቀጠቀጠ ፡ ቀረበና ፡ ባይኑ ፡ የገባለትን ፡ ቢያነሳ ፡ ያን ፡ ባዶ ፡ አገልግል ፡ ሆነና ፡ አረፈ ። አጤ ፡ ቴዎድሮስም ፡ አሰት ፡ እንዳይመስለው ፡ አፍ ፡ እስተአፍ ፡ ብር ፡ የሞላውን ፡ ደባይ ፡ አገልግል ፡ ከፍተው ፡ አሳዩት ፡ እና ፡ እንግዴህ ፡ አትማኝ ፡ አምላክ ፡ ባያከፍልህ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አሰናበቱት ፡ ለጋስ ፡ ነበሩና ፡ ፲ብር ፡ ሳይሰጡት ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ክፉ ፡ አደረጉ ፡ ደግሞ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ፩ቀን ፡ አንድ ፡ የሚያምኑት ፡ ዘበኛ ፡ ይዘው ፡ አልባሴ ፡ መስለው ፡ አዳፋ ፡ ጋቢ ፡ መሳይ ፡ ለበሱና ፡ ከጨለመ ፡ በኋላ ፡ በሰፈሩ ፡ ይዞሩ ፡ ጀመር ፡ በየጎጆውም ፡ እየተጠጉ ፡ ያደምጡ ፡ ነበር ፡ እኩሉ ፡ ያልተኛ ፡ እኩሉም ፡ ተኝቶ ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ካንድ ፡ ወታደር ፡ ጎጆ ፡ ተጠግተው ፡ ቢያደምጡ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ሲጣሉ ፡ ሰሙ ፡ ወንዱ ፡ ይለምናል ፡ ሴቲቱም ፡ አይሆንም ፡ ትላለች ።

ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ወንድየው ፡ በማርያም ፡ በሥላሴ ፡ እያለ ፡ ቢለምን ፡ በጻድቃን ፡ በቅዱሳን ፡ እያለ ፡ ቢቀባጥር ፡ እምቢ ፡ አለችውና ፡ በይ ፡ በቴዎድሮስ ፡ ሞት ፡ እንድትሰጭኝ ፡ አላት ፡ እሷዋም ፡ ቴዎድሮስማ ፡ ከሚሞት ፡ ጐንደር ፡ አይታረስም ፡ አለችና ፡ ሰጠችው ፡ ንጉሡ ፡ ይህን ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ እየሳቁ ፡ ወደ ፡ አዳራሽዎ ፡ ገቡና ፡ ያን ፡ አብሮአቸው ፡ የነበረ ፡ ዘበኛ ፡ ያችን ፡ ጎጆ ፡ እንዳትሳሳትህ ፡ ብለውት ፡ ነበርና ፡ በነጌታው ፡ ያነን ፡ ዘበኛ ፡ ባልና ፡ ምሽቱን ፡ ጠርተህ ፡ አምጣቸው ፡ ብለው ፡ ሰደዱት ፡ እነዝያም ፡ ምን ፡ ተገኘብን ፡ ይሆን ፡ ንጉሥ ፡ ወደኛ ፡ የሚልኩ ፡ ብለው ፡ እያንዘፈዘፉ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ መጡና ፡ ከጃንሆይ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ፡ ንጉሡም ፡ እንዴት ፡ አደራችሁ ፡ አልዋቸው ፡ እነዝያም ፡ እየተብረጀረጁ ፡ ሳይሰሙ ፡ ባጠገባቸው ፡ የቆመ ፡ ቢነግራቸው ፡ በግምባራቸው ፡ ተደፍተው ፡ እጅ ፡ ነሲተው ፡ ቆሙ ፡ ቀጥለው ፡ ንጉሡ ፡ ትላንትና ፡ ማታ ፡ በምኝታ ፡ ጊዜ ፡ ከቤታችሁ ፡ ሁናችሁ ፡ ምንና ፡ ምን ፡ ብላችሁ ፡ ተናገራችሁ ፡ ብለው ፡ ጠየቁዋቸው ። ወንድየው ፡ ጃንሆየ ፡ የተናገርነው ፡ የለም ፡ ጠላት ፡ ነገር ፡ ሰርቶብን ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ ያጋጥሙኝ ፡ ድኋ ፡ ወታደር ፡ ባርያዎ ፡ ነኝ ፡ እያለ ፡ ይወላፍጥ ፡ ጀመር ፡ ሴቲቱም ፡ አፍዋ ፡ ጠፍቷት ፡ ትንቀጠቀጣለች ፡ ንጉሡም ፡ ከምኝታችሁ ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ የተናገራችሁት ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ አስበህ ፡ ንገረኝ ፡ አይዞህ ፡ አሉት ፡ እሱም ፡ ሰውነቱን ፡ አጠናከረና ፡ አስቦ ። ያነን ፡ ምሽቱ ፡ ያደረገችውን ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ፡ ንጉሡም ፡ ሳቁ ፡ ሴቲቱም ፡ አፈረች ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ለሴቲቱ ፡ ባለ ፡ መርገፍ ፡ ኮርቻ ፡ በቅሎ ፡ ፭ደንገጥር ፡ ባርያ ፡ በርኖስ ፡ መርገፍ ፡ ሸማ ፡ አርገው ፡ ሸለሙና ፡ ለወንድየው ፡ የሸህ ፡ አምበል ፡ ሽሕ ፡ ብር ፡ ደሞዙ ፡ ድንኳን ፡ ከነአጋ

ሰሱ ፡ ማር ፡ ከነባሮች ፡ ገምቦኞች ፡ አርገው ፡ ሸለሙዋቸው ፡ ሰው ፡ በምላሱ ፡
ይጠፋል ፡ በምላሱም ፡ ይጠቀማል ፡ ለጉዳያቸው ፡ ብለው ፡ ያሰቡት ፡ ነገር ።
ንጉሥን ፡ ከዙፋኑዎ ፡ ወርደው ፡ ወደ ፡ ድኃው ፡ ጎጆ ፡ ተጠግተው ፡ በሴቲቱ ፡
መልካም ፡ መናገር ፡ ተሸለሙ ፡ በመልካም ፡ ምላስዋ ፡ የባልዋን ፡ ፈቃድ ፡ ፈ
ጽማ ፡ ንጉሥንም ፡ ደስ ፡ አሰኝታ ፡ ባልዋም ፡ እሷዋም ፡ ተሸለመች ።

## የሽፍቶች ፡

በአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጊዜ ፡ የነበሩ ፡ ሽፍቶች ፡ በጐጃም ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ።
በደምብያ ፡ እስከ ፡ ወልቃይት ፡ ክንፉ ፡ ጋረድ ፡ በትግሬ ፡ አገው ፡ ንጉሤ ፡
እኒህ ፡ ፫ቱ ፡ በርትተው ፡ ነበር ፡ በየስፍራቸው ፡ ሁነው ፡ የጐጃም ፡ የተላ ፡
ጓሉ ፡ ጥፋት ፡ ተድላ ፡ ጓሉ ፡ ሙተራ ፡ ጅበላ ፡ ከሚባል ፡ አምባ ፡ እየገባ ፡
ብዙ ፡ ቀን ፡ አስቸግሮ ፡ ነበር ፡ ንጉሡ ፡ ሲመጡበት ፡ ወደ ፡ አምባ ፡ ይገባል ፡
ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ አገር ፡ ያጠፋል ፡ ሁለ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ
ን ፡ ያስነድዳቸው ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መከሩና ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ክተት ፡ ብለው ፡
አዋጅ ፡ አስነገሩ ፡ ጠንክራ ፡ በቅሎ ፡ ጠንክራ ፡ ፈረስ ፡ ጠንክራ ፡ እግረኛ ፡ ተ
ከተለኝ ፡ ብለው ፡ አስለፍፈው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ መንገድ ፡ አቀኑና ፡ ባማራ ፡ ሳይ
ንት ፡ የሚያልፉ ፡ መስለው ፡ በሌሊት ፡ ቈልሻ ፡ ወደ ፡ ጐዠም ፡ ዘለቁ ፡ ሲነጋ ፡
ሠራዊቱን ፡ ደበቁና ፡ እሳት ፡ አታንድድ ፡ በየዱርህ ፡ ተሸጐጥ ፡ ብለው ፡ አስ
ለፍፈው ፡ በቀን ፡ ተደብቆ ፡ ዋለ ፡ መልሰው ፡ ሌት ፡ ሲገሰግሱ ፡ አደሩና ፡ የ
ጐጃም ፡ ሰው ፡ ሰይሰማ ፡ ሽፍታው ፡ ወደ ፡ አምባው ፡ እንዳይገባ ፡ መግብያ
ውን ፡ በየበሩ ፡ አስጠብቀው ፡ እንደ ፡ ልማድህ ፡ በዱር ፡ ተሸጐጥ ፡ ብለው ፡
አስለፈፉና ፡ ወታደራቸውን ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ ትተው ።

አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ብቻቸው ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ መስለው ፡ አዳፋ ፡ ልብ
ስ ፡ ለብሰው ፡ ጠጕራቸው ፡ ሹሩቤው ፡ እንደ ፡ ተንጨበረረ ፡ ጨሬያቸው ፡
በትክሻቸው ፡ እንዳደረጉ ፡ ከአንዲት ፡ የባላገር ፡ ሴት ፡ ገቡና ፡ እንዴት ፡ ዋ
ልሽ ፡ አልዋት ፡ እሷም ፡ እግዜር ፡ ይመስገን ፡ እንዴት ፡ ውልሃል ፡ አለቻቸው ፡
መልሰው ፡ እባክሽ ፡ ርቦኛልና ፡ እንጀራ ፡ ስጭኝ ፡ አልዋት ። እሷም ፡ የማን
ህ ፡ ወታደር ፡ አለቻቸው ፡ የተድላ ፡ ጓሉ ፡ ነኝ ፡ እንጅ ፡ የማን ፡ ብለሽኝ ፡ አ
ልዋት ፡ ይህን ፡ ተናጋገሩና ፡ እንጀራ ፡ በርጎ ፡ አቀረበችላቸው ፡ ውሃም ፡ አስ
ታጠበችና ፡ መብላት ፡ ሲጀምሩ ፡ ተቀመጠች ። ከዝያ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡ ቴዎድ



ሮስ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጠየቁዋት ፡ ያ ፡ እብድ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ ደረሰ ፡ ይ
ባላል ፡ ወሬው ፡ አልሰማችሁም ፡ አልዋት ፡ እርስዋም ፡ መለሰችና ፡ እብዶች
ስ ፡ የተድላ ፡ ጓሉ ፡ ወታደሮች ፡ ናችሁ ፡ እንጅ ፡ የተቀባ ፡ ንጉሥ ፡ እብድ ፡
አይባልም ፡ አለችና ፡ መልሳም ፡ አሁን ፡ ሸዋ ፡ ሔዶ ፡ ብትሰሙ ፡ አገር ፡ ስለ ፡
ማጥፋት ፡ ደስ ፡ ብሏቹሀል ፡ ያእብድ ፡ የምትሉት ፡ ንጉሥ ፡ ቢዘልቅባችሁ ፡
ደግሞ ፡ ድምጣችሁ ፡ አጥፍታችሁ ፡ ከአምባ ፡ ለመሸጐጥ ፡ ነው ፡ አለቻቸ
ው ፡ እና ። ንጉሡም ፡ ምነው ፡ ትሰድቢነ ፡ አለሽ ፡ እንጀራሽን ፡ አንሽ ፡ አሉ
ዋት ፡ ምነው ፡ አትጐርስም ፡ ብትላቸው ፡ ይበቃኛል ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡ ብለው ፡
ወጡ ፡ ራሳቸውን ፡ ተከናንበው ፡ በመጡበት ፡ መንገድ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ድ
ብቁ ፡ ጦራቸው ፡ ተጨመሩ ፡ በነገታው ፡ በማለዳ ፡ ፀሐይ ፡ ሳትወጣ ፡ ጐዠ
ምን ፡ ጽልመት ፡ አለበሱዋት ፡ የፈረስ ፡ መዓትና ፡ የእግር ፡ አጐዳ ፡ ምድር ፡
የፈረሰ ፡ እስኪመስል ፡ ሆነና ፡ የማረክህ ፡ ለራስህ ፡ እወቅ ፡ አሉትና ፡ የሞተ ፡
ሞተ ፡ የተረፈም ፡ እጅ ፡ እና ፡ እግሩ ፡ እየቆመጡ ፡ ከአንድ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ አረገ
ፉት ፡ ተድላ ፡ ጓሉም ፡ ከዝያው ፡ ሞተ ። ተልባ ፡ ጓሉ ፡ በሉት ፡ አሉ ። አንድ ፡
ወታደር ፡ በቀረርቱ ፡ በበና ፡ ሲገጥም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ተልባ ፡ በባ
ሩድ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ ይታሻል ። እንኳን ፡ ሰውውና ፡ መሬት ፡ ይሸሻል ፡

ጐጃም ፡ ሲዘረፍ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እንጀራ ፡ ወደ ፡ አበላቻቸውና ፡ እ
ብዶችስ ፡ የተድላ ፡ ጓሉ ፡ ወታደሮች ፡ ወደ ፡ አለችው ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡
በሩቅ ፡ ሁነው ፡ አሳይተው ፡ ዘበኞች ፡ ጠባቆች ፡ ሰደዱላት ፡ እሷም ፡ አጥብ
ቃ ፡ ፈራች ፡ እና ፤ ለጠባቆች ፡ ምግብ ፡ ሰጥታ ፡ እየፈራች ፡ ተቀምጣ ፡ ሳለ
ች ፡ ይዘህ ፡ አምጣት ፡ የሚል ፡ መልክተኛ ፡ መጣ ፡ የንጉሥ ፡ ድንኳን ፡ ተቤ
ትዋ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፡ እና ፡ እያንቀጠቀጠች ፡ ወዝዋ ፡ እየፈሰሰ ፡ ከጃንሆይ ፡
ፊት ፡ እጅ ፡ ነስታ ፡ ቆመች ።

አጤ ፡ ቴዎድሮስም ፡ የቁጣ ፡ አስመስለው ፡ በዪ ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ ትላንትና ፡
የተላ ፡ ጓሉ ፡ ወታደሮች ፡ ከቤትሽ ፡ ገብተው ፡ ነበር ፡ ሰምቸ ፡ አለሁና ፡ እው
ነቱን ፡ ንገሪኝ ፡ በቀረ ፡ ከሳሽ ፡ ሊመጣብሽ ፡ ነው ፡ አሉና ፡ ነገርዋት ። እሷም ፡
እግዜር ፡ ያሳየዎ ፡ ጃንሆይ ፡ ከንጉሥና ፡ ከእግዜር ፡ ፊት ፡ እውነት ፡ መናገር
ነው ፡ መልካም ። ትላንት ፡ እውነት ፡ በሐሰት ፡ አለውጥም ፡ አንድ ፡ ጎበዝ ፡
ከቤቴ ፡ መጥቶ ፡ እባክሽ ፡ ርቦኛልና ፡ እንጀራ ፡ ስጭኝ ፡ አለኝ ፡ የማን ፡ ወታ
ደር ፡ ነህ ፡ ብየ ፡ ብጠይቀው ፡ የተድላ ፡ ጓሉ ፡ ነኝ ፡ እንጅ ፡ የማን ፡ ልታደር
ጊኝ ፡ ነው ፡ አለኝ ፡ እኔም ፡ ፈርቸ ፡ እንጀራ ፡ በርጎ ፡ አቀረብሁለትና ፡ አል
ላውም ፡ እንኳ ፡ ተልሞጽምጾ ፡ ጥሎልኝ ፡ ሔደ ፡ የተናገረውስ ፡ ለራሱ ፡ ያ

ጥቀመው ፡ እኔ ፡ አልናገረውም ፡ እኔ ፡ ግን ፡ የተቀበ ፡ ንጉሥ ፡ ሲመጣ ፡ ድምጣችሁ ፡ ሊጠፋ ፡ ዛሬ ፡ ንጉሥ ፡ ሽዋ ፡ ሒደው ፡ ሰምታችሁ ፡ ድኃ ፡ ለማጥፋት ፡ ደስ ፡ ብሎአችኋል ፡ ብየ ፡ ተናገርሁትና ፡ ደህና ፡ ሁኝ ፡ ብሎኝ ፡ ጠሩን ፡ አንስቶ ፡ ወጥቶ ፡ ተጓዘ ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የተናገርሁት ፡ የለኝም ፡ ካለ ፡ ፩ኅበዝም ፡ ሌላ ፡ የገባብኝ ፡ የለም ፡ ከሳሽ ፡ ይቁምብኝ ፡ አለችና ፡ እጅ ፡ ነሳች ፡ ጃንሆይም ፡ በይ ፡ ሒጂ ፡ ብለው ፡ ዘበኞችዋን ፡ ይዛ ፡ እየተንቀጠቀጠች ፡ ቤትዋን ፡ ተመለሰች ፡ ዘበኞች ፡ ከርስዋ ፡ ጋር ፡ ቢመለሱ ፡ ለጥፋት ፡ መስሏት ፡ ነበር ። በነገታው ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተዘርፎ ፡ የሚለብሰው ፡ ልብስ ፡ የሚበላው ፡ እህል ፡ ሲያጣ ፡ የሷ ፡ ቤት ፡ ከነጎረቤትዋ ፡ በጤና ፡ አደሩ ፡ በነገታውም ፡ ተጠርታ ፡ ሔደች ፡ እየፈራች ፡ ሽንትዋ ፡ በጭንዋ ፡ እየወረደ ፡ ሒዳ ፡ እጅ ፡ ነሳችና ፡ ቆመች ፡ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ ፈርታ ፡ ሲያዩዋት ፡ ጊዜ ፡ አይዞሽ ፡ ብለው ፡ ንሳ ፡ ፻ላም ፡ ለርቢ ፡ የሚሆኑዋት ፡ ፻በሬ ፡ ለእርሻ ፡ ከዚህ ፡ ካለው ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ አስመርጠህ ፡ ስጣት ። ደግሞ ፡ እስከ ፡ እልፈቴ ፡ ነጣ ፡ አትከሰስ ፡ አትወቀስ ፡ አሉዋት ፡ እሷ ፡ ግን ፡ እውነት ፡ አልመስላት ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ለመንሳት ፡ ልቧ ፡ ጠፍቶ ፡ አብረዋት ፡ የቆሙ ፡ እጅ ፡ ንሽ ፡ እጅ ፡ ንሽ ፡ ቢልዋት ፡ በግድ ፡ እጅ ፡ ነሳች ። ሰው ፡ በምላሱ ፡ ይጠፋል ፡ በምላሱም ፡ ይድናል ፡ እንኳን ፡ ራስዋን ፡ ለጎረቤቶችዋም ፡ ጠቀመች ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ተናገረች ፡ ምላሳችን ፡ ትንሽ ፡ ናት ፡ ክፉ ፡ ብንናገርባት ፡ ብንዋሽባት ፡ በሰውና ፡ በእግዜር ፡ ታጠፋን ፡ አለች ።

መልካም ፡ ብንናገርባት ፡ እውነት ፡ ብንመሰክርባት ፡ ከሰውና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታፋቅራለች ፡

## ያጤ ፡ ቴድሮስ ፡ የእቶቻቸው ፡ ታሪክ ።

አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በመጀርያ ፡ ሽፍታ ፡ ሳሉ ፡ ፩ቀን ፡ ቢርባቸው ፡ ወደ ፡ እቶቻቸው ፡ ቤት ፡ ተሰርቀው ፡ ገቡ ፡ እቶቻቸውም ፡ ደነገጡና ፡ ምን ፡ ልታረግ ፡ መጣህ ፡ ልታጠፋን ፡ አልዋቸው ፡ ቢርበኝ ፡ እንጀራ ፡ ልታበሉኝ ፡ መጣሁ ፡ አሏቸው ። አንዲቱ ፡ ምን ፡ እንጀራ ፡ አለ ፡ ባንተ ፡ ጠንቅ ፡ ተዘርፈን ፡ የለም ፡ አለች ፡ መቸም ፡ ምላስዋ ፡ ያልተቀበ ፡ ነውና ። አንዲቱ ፡ ግን ፡ አፈ



ር ፡ ያብላኝ ፡ ወንድሜ ፡ እንዴት ፡ እንጀራ ፡ ቸገረህ ፡ ብላ ፡ አልቅሳ ፡ የምታረገው ፡ ጨነቃትና ፡ አስባ ፡ ለዘር ፡ ብሎ ፡ የተቀመጠ ፡ ያልተፈለፈለ ፡ የባሕር ፡ ማሽላ ፡ አገኘችና ፡ ይህን ፡ ፈልፍየ ፡ ፈጭቸ ፡ አበላሀለሁ ፡ ወንድሜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለችዎና ፡ የባሕር ፡ ማሽላውን ፡ ትፈለፍል ፡ ገባች ። መፍጨት ፡ ስትጀምር ፡ ያች ፡ ያልታደለች ፡ አንዲቱ ፡ መጣችና ፡ ምነው ፡ አንቺ ፡ ዘሩን ፡ ልትፈጭ ፡ እነው ፡ ተይ ፡ አለቻት ። ባለ ፡ እድሊቱ ፡ መለሰችና ፡ እቴ ፡ ዘርስ ፡ ካሳ ፡ አለቻት ፡ አጤ ፡ እየሰሙ ፡ ፈጭተው ፡ ጋግረው ፡ ሰጥዋቸውና ፡ በልተው ፡ ደህና ፡ ሁኑ ፡ ብለው ፡ በጨለማ ፡ ወጥተው ፡ ሔዱ ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጠቅልለው ፡ ያዙና ፡ ዘርስ ፡ ካሳ ፡ ላለችው ፡ እታቸው ፡ ቋራ ፡ አገራቸውን ፡ ጠቅልለው ፡ ባልዋን ፡ ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ አፍራሽ ፡ አሰኝተው ፡ ነጋሪት ፡ ከነ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማው ፡ በፊትዋ ፡ አብጅር ፡ እያለ ፡ እስከ ፡ እልፈታታቸው ፡ ገዛች ፡ ስትሞትም ፡ እያለቀሱ ፡ በግምጃ ፡ በተለበጠ ፡ ሳጥን ፡ ጉብታ ፡ ግሽን ፡ አምባ ፡ ተቀበረች ።

ያች ፡ ዘር ፡ አትፍጭ ፡ ያለችው ፡ እታቸው ፡ ግን ፡ በምላስዋ ፡ ቀረባትና ፡ ባላገር ፡ ሁና ፡ ቀረች ፡ በጭቃ ፡ እየታዘዘች ። ሰው ፡ በምላሱ ፡ ይጠፋል ፡ በምላሱ ፡ ይጠቀማል ።

## የክንፉ ፡ ጋረድ ፡ ታሪክ ፡

ክንፉ ፡ ጋረድ ፡ የአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ነው ። አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በአባቱ ፡ በደጃች ፡ ክንፉ ፡ ይምሉ ፡ ነበር ፡ ክንፉ ፡ ይሙት ፡ ይላሉ ። ሲፈክሩም ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ ደጃች ፡ ክንፉ ፡ ስለ ፡ አሳደግዋቸው ።

ክንፉ ፡ ጋረድ ፡ ግን ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ከድቶ ፡ ብርቱ ፡ ሽፍታ ፡ ሁኖ ፡ ነበር ፡ በደምብያም ፡ በጭልጋም ፡ ቆላ ፡ ለቆላ ፡ እየተሰረቀ ፡ መሻዳሪ ፡ ይበላ ፡ ነበር ፡ ንጉሡም ፡ ዘመዳቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቸላ ፡ ብለውት ፡ ነበር ፤ ተው ፡ ግባ ፡ እያሉም ፡ እየላኩ ፡ ይመክሩት ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። እርሱም ፡ አልገባም ፡ አለና ፡ እየበረታ ፡ ሔደ ፡ የንጉሥ ፡ ዘመድ ፡ ነውና ፡ ምን ፡ አልባት ፡ ያገኘን ፡ እያለ ፡ ወታደር ፡ መቸም ፡ እበላለሁ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ እሞታለሁ ፡ አያውቅምና ፡ የደምብያ ፡ የጭልቃ ፡ የወልቃይት ፡ የወገራ ፡ የቈላውም ፡ የደጋውም ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ሰበሰበና ፡ አገር ፡ ያውክ ፡ ጀመረ ፡ ወደ ፡ ጐንደርም ፡ እየገባ ፡ ሃብታሞች ፡ እያሰረ ፡ ገንዘብ ፡ ይገላገል ፡ ያዘ ።

## የበሻ ፡ ብላውደን ፡ ታሪክ ፡

ባሻ ፡ የተባሉ ፡ የምጥዋ ፡ ቄንሱል ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ነው ፡ በቱርክ ፡ ግዛት ፡ የሚገዛ ፡ ባሻ ፡ ይባላል ፡ ከዝያ ፡ በኋላ ፡ ባሻ ፡ ብላውደን ፡ የእንግሊዝ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ፡ በጐንደር ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አግብተው ፡ ነበር ፡ ያችው ፡ ሴት ፡ በዝያው ፡ ጊዜ ፡ ጐንደር ፡ ነበረችና ፡ ባሻ ፡ ብላውደን ፡ ወደ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሒደው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ልወርድ ፡ ፈቃድ ፡ ይስጡኝ ፡ አሉና ፡ ተናገሩ ፡ ንጉሡም ፡ አትሒድ ፡ ክንፉ ፡ ጋረድ ፡ ያገኝሀል ፡ አልዋቸው ፡ ባሻ ፡ ብላውደን ፡ መቸም ፡ ጀግና ፡ ተዋጊ ፡ ነበሩና ፡ እኔ ፡ አባ ፡ ኑብሶ ፡ እንኔን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሽፍታ ፡ ይገድለኛል ፡ አሉና ፡ ከንጉሥ ፡ ፊት ፡ ተናገሩ ፡ ንጉሥ ፡ እሽ ፡ ሒድ ፡ አልዋቸውና ። ተሰናብተው ፤ ወደ ፡ ጐንደር ፤ ተነሱ ፡ ንጉሥ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ነው ፡ የነበሩ ።

ባሻ ፡ ብላውደን ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በጐንደር ፡ መንገድ ፡ ሲጓዙ ፡ ዋሉና ፤ በነገታው ፡ ጐንደር ፡ ሊገቡ ፡ ቸኵለው ፡ ነበርና ፡ ከበቅሎ ፡ ወርደው ፡ በፈረስ ፡ ተቀመጡና ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬያቸው ፡ በበቅሎ ፡ ሁኖ ፡ እርሳቸው ፡ ፈረሱን ፡ በርትረታ ፡ ቀስ ፡ ብየ ፡ እሄዳለሁ ፡ እየመሰላቸው ፡ ይጓዙ ፡ ጀመር ፡ ጐንደርን ፡ በቶሎ ፡ ስለ ፡ መግባት ፡ ያስባሉ ፡ እንጅ ፡ የሚቆያቸውን ፡ ነገር ፡ አላሰቡም ፡ ነበር ፡ ሰዎቻቸውም ፡ ደክመው ፡ እንደርሳለን ፡ እያሉ ፡ ቢከተሉ ፡ የማይደርሱ ፡ ሆኑ ፡ ባሻ ፡ ብላውዳንም ፡ ቀሀ ፡ ከጐንደር ፡ አጠገብ ፡ ከዝያ ፡ መልካም ፡ ወንዝ ፡ ከፈረሴ ፡ ወርጀ ፡ ሰዎቸ ፡ ሲመጡ ፡ በአጀብ ፡ ጐንደር ፡ እገባለሁ ፡ እያሉ ፡ እየጋለቡ ፡ ሲሔዱ ፡ ሳሉ ፡ ቀሀ ፡ ከወንዙ ፡ ሊገቡ ፡ ጥቂት ፡ ስትቀራቸው ፡ የጋረድ ፡ ሰዎች ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ፈሰሱባቸው ፡ አባ ፡ ኑብሶ ፡ ብለው ፡ ፈክረው ፡ ወደ ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬ ፡ ጠበንጃ ፡ ሊቀበሉ ፡ ዘወር ፡ ሲሉ ፡ የጋረድ ፡ ሰዎች ፡ በረምታ ፡ ተኰሱባቸው ፡ ጋሻ ፡ ጃግሬውም ፡ በበቅሎ ፡ እየጋለበ ፡ ፉኒጥ ፡ ፉኒጥ ፡ ቢል ፡ ሳይደርስባቸው ፡ ቀረ ፡ የሕልም ፡ ሩጫና ፡ በቅሎ ፡ መጋለብ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ካሳብኸው ፡ አያደርስም ፡ እና ። ባሻ ፡ ቡላውደን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሳይገድሉ ፡ ያንጊዜው ፡ ወደቁና ፡ በስከወድያ ፡ ሞቱ ፡ ሰዎቻቸውም ፡ ተማረኩ ፡ ጠበንጃቸው ፡ ሳይተኰስ ፡ ከጋሻ ፡ ጃግሬው ፡ እጅ ፡ የጋረድ ፡ ወታደሮች ፡ ወሰዱት ፡ ትምክህት ፡ ክፉ ፡ ነውና ፡ ባሻ ፡ ብላውደን ፡ ለ፪የሐበሻ ፡ ወታደር ፡ እኔ ፡ ብቻየ ፡ እበቃለሁ ፡ ብለው ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፡ ይባላል ፡ በአፍ ፡ ትምክሕት ፡ መልካሙ ፡ ጅግና ፡ በከንቱ ፡ ወድቀው ፡



ቀሩ ፤ አባ ፡ ኑብሶ ፡ ነበረ ፡ ፍከራቸው ፡ አባ ፡ ኑብሶ ፡ ያሉበቱ ፡ ከአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በወሎ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ባሻ ፡ ብላውደን ፡ ወራሪ ፡ ብለው ፡ ሔዱ ፡ የወረሒመኖ ፡ ፈረስ ፡ አላጎ (አላጐ?) ፡ መጣባቸውና ፡ በ፪አፍ ፡ ጠበንጃ ፡ ፪ፈረሰኞች ፡ መርጠው ፡ ጣሉ ፡ መልሰው ፡ በሽጉጥ ፡ አንድ ፡ ገድለው ፡ ፫እንደ ፡ ጣሉ ፡ የወርሔመኖ ፡ ፈረሰኞች ፡ ሽሹና ፡ ሩቅ ፡ ለሩቅ ፡ ሁነው ፡ ሲያዩ ፡ የባሻ ፡ ብላውደን ፡ ፫አዳኞች ፡ ውሾች ፡ ነበርዋቸው ፡ ተእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ያመጡዋቸውና ፡ ያነን ፡ ባሻ ፡ ብላውደን ፡ የገደሉት ፡ ሬሳ ፡ እኒያ ፡ ውሾች ፡ ይበላሉ ፡ ውሾቹ ፡ ታላላቆች ፡ ነበርና ፡ የጋላ ፡ ወታደር ፡ በሩቅ ፡ ሁኖ ፡ ቢያቸው ፡ ሌላ ፡ አይነት ፡ መስለው ፡ ታዩት ፡ ባሻ ፡ ብላውደንም ፡ ሌላ ፡ ዓይነት ፡ ነጭ ፡ ሁነው ፡ አሻግሮ ፡ አየና ፡ አንተ ፡ ዛሬስ ፡ ሰው ፡ የሚበላ ፡ መጥቶዋል ፡ ሬሳ ፡ ሲበላ ፡ አይቸ ፡ ሲል ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ሸሸ ፡ ባሻ ፡ ብላውደንም ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ ቢሰሙ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ፡ ብለው ፡ ፎከሩ ። እንዲያ ፡ ያሉትን ፡ ጅግና ፡ ፩ሰው ፡ ሳይገድሉ ፡ በቀሀ ፡ ወንዝ ፡ በሽፍቶች ፡ እጅ ፡ ወደቁ ። ተዝያ ፡ ወድያ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ባሻ ፡ ብላውደንን ፡ ጋረድ ፡ እንደ ፡ ገደላቸው ፡ ሰሙና ፡ አዘኑ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስም ፡ ታረዱና* ፡ የናቴ ፡ ልጅ ፡ ወንድሜ ፡ እያሉ ፡ አለቀሱ ። ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ አብረው ፡ የወጡ ፡ ባልንጀሮች ፡ ነበሩና ። እጅግ ፡ ሀዘን ፡ ጠናባቸው ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የ፩ሳምንት ፡ ስንቅህን ፡ ያዝ ፡ ጠንካራ ፡ በቅሎ ፡ ጠንካራ ፡ አጋሰስ ፡ ጠንከራ ፡ ፈረስ ፡ ይዘህ ፡ እኔ ፡ በመራሁህ ፡ ተጓዝ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ አስነገሩና ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ገሰገሱ ፡ ክንፉ ፡ ጋረድም ፡ የአጤ ፡ ቴዎድሮስን ። መምጣት ፡ ሰማና ፡ ከነበረው ፡ ስፍራ ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ዋልድባ ፡ ወደ ፡ ማይ ፡ ተክሊት ፡ አዲ ፡ አርቃይ ፡ የሚባል ፡ ወገን ፡ ሒዶ ፡ ሰፈረ ፡ ንጉሥም ፡ ተከትለውት ፡ በለማልሞ ፡ ቁልቁለት ፡ ወርደው ፡ ድብ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ፡ የዝያን ፡ ጊዜ ፡ የክንፉ ፡ ጋረድ ፡ መከሮች ፡ እንሽሽ ፡ ብለው ፡ መከሩት ፡ እርሱም ፡ ሳልዋጋ ፡ እንዳልሸሽ ፡ ግዝት ፡ ያርግብኝ ፡ ብሎ ፡ ተገዘተና ፡ ወታደሩ ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ማይ ፡ ተክሊት ፡ ላይ ፡ ተሰልፎ ፡ ዝም ፡ አለ ፡ ብዙ ፡ ጦር ፡ ነበረውና ። አጤ ፡ ቴዎድሮስም ፡ መቸም ፡ የጦር ፡ መላ ፡ ሌላ ፡ የሚያውቃት ፡ አልነበረምና ፡ ጥኑ ፡ ዱር ፡ ነው ፡ የነበረ ፡ ቦታውና ፡ የእግር ፡ ነፍጠኛ ፡ በግራ ፡ በቀኝ ፡ ሰደዱበትና ፡ ተሰጥተህ ፡ ተቀመጥ ፡ ብለው ፡ አዘዙት ፡ እኔ ፡ በማኸል ፡ ስጀምር ፡ ፊትከን ፡ ሳታዞር ፡ ተሻማው ፡ ብለው ፡ አዘውት ፡ አደሩና ፡ በማለዳ ፡ የቀኙም ፡ በቀኝ ፡

* በዚህ ፡ ስፍራ ፡ የደራሺው ፡ ጽሕፈት ፡ አይጉላም ። ምናልባት ፡ በ«ታረዱና» ፡ ስፍራ ፡ «ተረዱና» ፡ ቢነበብ ፡ ይሻላል ።

የግራውም ፡ በግራ ፡ የመይሳ ፡ ልጅም ፡ ማኽል ፡ ለማኽል ፡ ሔዱና ፡ ገጠሙ ። ክንፉ ፡ ጋረድም ፡ ዱሩን ፡ ይዞ ፡ ይለማመጥ ፡ ጀመረ ፡ መልካም ፡ አድርጎ ፡ እስከ ፡ እኩል ፡ ቀን ፡ ተዋጋ ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ የንጉሡ ፡ ሠራዊት ፡ ሲያስጨንቀው ፡ ጊዜ ፡ ክንፉ ፡ ጋረድ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ገድየ ፡ እሞታለሁ ፡ ብሎ ፡ ማኽል ፡ ለማኽል ፡ በፈረስ ፡ ጨሬውን ፡ እየሰበቀ ፡ አንድ ፡ ጅግና ፡ ፈረሰኛ ፡ አስከትሎ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሉበቱ ፡ ደረሰ ፡ እንደ ፡ እብድ ፡ በፊቱ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ እየሸሸ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ጦር ፡ ሊወረውር ፡ ሲቃጣ ፡ ሊቀ ፡ መንኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ የማነን ፡ ጌታ ፡ ብለው ፡ ጋረድን ፡ ደረቱን ፡ በጠበንጃ ፡ ሰነጠቁት ፡ እና ፡ ወደቀ ። ያ ፡ የጋረድ ፡ ጀግና ፡ ደግሞ ፡ የማነን ፡ ጌታ ፡ አለነ ፡ በፈረስ ፡ መጥቶ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስን ፡ በጦር ፡ ካይናቸው ፡ ወግቶ ፡ ገደላቸው ።

አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደግሞ ፡ ያ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስን ፡ የወጋ ፡ ጅግና ፡ የማነን ፡ ሎሌ ፡ ገድለህ ፡ ልትሔድ ፡ ብለው ፡ በጠበንጃ ፡ ገደሉትና ።

በስከ ፡ ወድያው ፡ ንጉሡ ፡ ባለቤታቸው ፡ በፈረስ ፡ ወጡና ፡ ባለ ፡ ቤት ፡ ወድቆልሀል ፡ ተማረክ ፡ በለው ፡ ሲሉት ፡ ጊዜ ፡ የንጉሥ ፡ ሠራዊት ፡ እንደ ፡ ንብ ፡ እያለፈ ፡ . . . . . . ፡ ጀመር ። የጋረድ ፡ ሠራዊት ፡ የሚሞት ፡ ሙቶ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ሳያመልጥ ፡ ተማረከ ፡ ንጉሡም ፡ ምርኮኛ ፡ የሰደድህ ፡ ለአካላትህ ፡ እዘንለት ፡ ብለው ፡ አስለፍፈው ፡ በቶሎ ፡ ደባርቅ ፡ ወጥተው ፡ ሰፈሩ ። በሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስም ፡ ሞት ፡ ሲያለቅሱ ፡ ሰነበቱና ። ከጋረድ ፡ ጋራ ፡ የተገኘ ፡ ምርኮኛ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ማግረው ፡ በጠበንጃ ፡ ፈጁት ፡ ደብድበው ፡ ታበቁ ፡ ወድያ ፡ የሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ ደም ፡ ነው ፡ ጋረድ ፡ ሊገድለኝ ፡ ኑሮ ፡ ስለኔ ፡ ተለውጦ ፡ ዮሐንስ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ ይላሉ ። የእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ በሔደበት ፡ ሁሉ ፡ የተመሰገነ ፡ ነውና ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ ዮሐንስ ፡ በሐበሻ ፡ በጅግንነታቸው ፡ ተመስግነው ፡ የጌታቸውን ፡ ጠላት ፡ ተነጥፈው ፡ ሞቱ ። የጋረድ ፡ ሎሌም ፡ የተመሰገነ ፡ ጅግና ፡ ነው ፡ የጌታውን ፡ ደም ፡ መልሶ ፡ ሞተ ። ቴዎድሮስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያም ፡ የተመሰገኑ ፡ ጅግና ፡ የሎሌያቸውን ፡ ደም ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ገድለው ፡ መልሰው ፡ አልጋዎን ፡ የሚያቆሙ ፡

ክንፉ ፡ ጋረድም ፡ ንጉሡን ፡ እገድላለሁ ፡ ብሎ ፡ ማኽል ፡ ለማኽል ፡ ገብቶ ፡ ፊቱን ፡ ሳያዞር ፡ የወደቀ ፡ የተመሰገነ ፡ ጅግና ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጅግና ፡ ሆነ ፡ ፈሪ ፡ ሆነ ፡ ሁሉ ፡ ለሞት ፡ ነውና ፡ ሁሉም ፡ ሞቱ ።

የጅግኖቹ ፡ ስም ፡ ግን ፡ አልጠፋም ፡ አለ ። ከዝያ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ የጋረድን ፡ ሠራዊት ፡ ደብድበው ፡ ከጨረሱ ፡ ወድያ ፡ ከደባርቅ ፡ ወደ ፡



ጐንደር ፡ በሚነሱበት ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲቀር ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ አስነገሩ ።

አራሽ ፡ እረስ ፡ ነጋዴም ፡ ነግድ ። ሽፍታ ፡ ወምበዴ ፡ ተው ፡ ግባ ፡ ይሻላሀል ፡ ተዚህ ፡ ቀደም ፡ የበደልኸው ፡ ቋንጃ ፡ የቆረጥህ ፡ ነፍስ ፡ የገደልህ ፡ ምሬሀ ፡ አለሁ ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ያለህ ፡ ግባ ፡ አልገባም ፡ ብለህ ፡ አዋጀን ፡ ያለፍህ ፡ ግን ፡ ለአካልትህ ፡ እዘንለት ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ አስነገሩና ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ተጓዙ ። ያንጊዜም ፡ እነ ፡ አገው ፡ ንጉሤም ፡ በትግሬ ፡ ሽፍቶች ፡ ነበሩ ።

በዝያው ፡ ጊዜ ፡ አጤ ፡ በጐንደር ፡ አደራሽ ፡ ተገኙ ፡ እና ፡ የጃንሆይ ፡ አዝማሪ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገጠመ ።

ጋረድ ፡ ሞተ ፡ እንኳ ፡ ተቀበረ ። ያንተ ፡ ዘር ፡ ነውና ፡ ሰግተነው ፡ ነበረ ። አለ ።

መልሶም ፡ ይብላኝ ፡ ለንጉሤ ፡ ጀርባው ፡ ተከፈተ ፡ ይብላኝ ፡ ለተሰማ ፡ ጀርባው ፡ ተከፈተ ። የወንዶቹ ፡ ወንድም ፡ አባ ፡ ገልብጥ ፡ ሞተ ። አለ ፡

የጋረድ ፡ ፍከራ ፡ አባ ፡ ገልብጥ ፡ ነበረ ፡ ማለቱ ፡ የቴድሮስን ፡ አልጋ ፡ ገልብጬ ፡ እኔ ፡ እነግሣለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ። በአፍ ፡ ጡር ፡ መናገር ፡ ክፉ ፡ ነውና ፡ በአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በወንድሙ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይሾምና ፡ እንዳይከብር ፡ ምቀኛ ፡ ሁኖ ፡ ሙቶ ፡ ሳይቀበር ፡ እርሱና ፡ ሠራዊቱ ፡ የአሞራና ፡ የጅብ ፡ ምግብ ፡ ሁነው ፡ ቀሩ ።

በዝያው ፡ ጊዜ ፡ የጐንደር ፡ ሊቅ ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጽፈው ፡ ግጥም ፡ ገጠሙ ። ከዝያም ፡ ነገሠ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ። ቴዎድሮስ ፡ ነገሡና ። እባብ ፡ ጠፉ ፡ በጐደና ። ወምበዴም ፡ ሔደ ፡ ምነና ። ጉብያችንም ፡ አለ ፡ ፈሰስ ። ጋለሞታችንም ፡ አለች ፡ ፈረንስ ። አንዳንድ ፡ ወምበዴ ፡ መንኵሶ ፡ በየገዳሙ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ።

አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደብተራና ፡ መለኩሴ ፡ አይወዱም ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ደብተራ ፡ አይወዱም ፡ ነበርና ፡ ደብተራን ፡ ሲሰድቡ ፡ ድጉን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እየታጠቀ ፡ አይዋጋ ፡ አይገብር ፡ ከከተማ ፡ ሁኖ ፡ የሰው ፡ ምሽትና ፡ ጋለሞታ ፡ እየመለመለ ፡ ነው ፡ ኑሮው ፡ ይሉት ፡ ነበር ። ስለ ፡ ዚህ ፡ ሪሙን ፡ ሁሉ ፡ ነቅለው ። በደብር ፡ ፎልዑካን ፡ ይበቃሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደብርም ፡ ፯ቄስ ፡ ይበቃል ፡ ብለው ፡ ሰርተውት ፡ ነበር ፡ ስለዚህ ፡ ካህን ፡ ሁሉ ፡ አይወዳቸውም ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊስሙ ፡ ገቡ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ አዲስ ፡ ተሰርቶ ፡ ማኅደረ ፡ ማርያም ፡ ይመስለኛል ፡ ተ

ጨርሶ ፡ ነበር ፡ ቅኔ ፡ ማኅሌቱ ፡ ጠበብ ፡ ያለ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ዱብተራ ፡ ንጉሥ ፡ ያከበሩት ፡ ተአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራ ፡ ቁሞ ፡ ነበርና ። አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ይህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠበበ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ያ ፡ ያከበሩት ፡ ዱብተራ ፡ ለ፳ልኡካን ፡ አይጠባቸውም ፡ አለና ፡ መለሰላቸው ፡ ካህን ፡ አይወዱም ፡ ብሎ ፡ አምቶ ፡ ነው ፡ ንጉሡም ፡ በሆዳቸው ፡ አዝነውበት ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከሆነ ፡ ወድያ ፡ ያዱብተራ ፡ ከንጉሥ ፡ ጠላቶች ፡ ጋር ፡ አግኝተውት ፡ አብሮ ፡ ተደበደበ ፡ ያንጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ቂማቸውን ፡ ነገሩበት ።

አንድ ፡ ቀን ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዱብረ ፡ ታቦር ፡ ሳሉ ፡ ፪መለኩሶች ፡ ተጣልተው ፡ ተሳድበው ፡ ዳኛ ፡ ይዞዋቸው ፡ ተንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ መጡና ፡ ቆሙ ፡ እየቃላቸውና ፡ እየስድባቸው ፡ ተናገሩ ፡ ነገሩ ፡ ፍሬ ፡ የሌለበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አዩትና ፡ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ መለኩሴ ፡ የታባሽ ፡ አትዋጊ ፡ አታርሽ ፡ ድግሽን ፡ በራስሽ ፡ እየታጠቅሽ ፡ ሰውን ፡ አላሳርፍ ፡ ካልሽ ፡ በሉ ፡ ልብሳችሁን ፡ ጥላችሁ ፡ ታገሉ ፡ አልዋቸውና ፡ ብቻ ፡ ቀሚሳቸውን ፡ ሆኑና ፡ ከንጉሥ ፡ ፊት ፡ ትግል ፡ ገጠሙ ፡ የሁለቱ ፡ መጠምጠምያ ፡ ወደቀና ፡ አንድ ፡ በላይ ፡ አንድ ፡ በታች ፡ ሳይሆን ፡ የግድም ፡ ወደቁና ፡ ሁለቱም ፡ አንድላቸው ፡ ሳይነሱ ፡ ተወደቁቱ ፡ ሁነው ፡ ይጐፋጨሩ ፡ ጀመር ፡ ተዝያ ፡ ወድያ ፡ ንጉሡ ፡ እየሳቁ ። የታባሽ ፡ መለኩሴ ፡ ምላስ ፡ ተሸክመሽ ፡ ብለው ፡ አንስዋቸው ፡ ብለው ፡ እንግዲህ ፡ እርስበርሳችሁ ፡ ብትሳደቡ ፡ እገርፋችሁ ፡ አለሁ ፡ ብለው ፡ ሰደድዋቸው ።

ደግሞ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሰውን ፡ እያስያዙ ፡ ሲደበድቡ ፡ ሳሉ ፡ አንድ ፡ የጭዋ ፡ መለኰሴ ፡ ትምርት ፡ የሌለው ፡ ተማርኮ ፡ መጣ ፡ በል ፡ ያዘው ፡ ሲሉት ፡ ጊዜ ፡ ጃንሆየ ፡ እግዜር ፡ ያሳየዎ ፡ ቄስ ፡ ነኝ ፡ አላቸው ፡ ንጉሡም ፡ ቄስ ፡ ተሆንህ ፡ ዳዊት ፡ ቁጥሩ ፡ ስንት ፡ ነው ፡ አሉት ፡ እርሱም ፡ ጃንሆየ ፡ ይማሩኝ ፡ እንጅ ፡ የሜዳ ፡ ቄስ ፡ ነኝ ፡ አላውቅም ፡ ሲላቸው ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሳቅ ፡ ይዞአቸው ፡ አፈዎን ፡ ይዘው ፡ ዝም ፡ አሉ ፡ የሜዳ ፡ ቄስም ፡ ከመደብደብ ፡ አመለጠ ።

## የአገው ፡ ንጉሤ ፡ ታሪክ ፡

በአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መንግሥት ፡ ደጃች ፡ ንጉሤ ፡ እና ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ የሚባሉ ፡ ፪ወንድማማች ፡ ሸፈቱ ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ የአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሎላት ፡ ነበሩ ፡ በሳህላ ፡ መሬት ፡ ሽፍታ ፡ ሁነው ፡ ተቀመጡ ፡ ንጉሡ ፡ መቸም ፡



እርፈት ፡ አልነበራቸውም ፡ ሁለጊዜ ፡ ወደ ፡ ወሎና ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ነው ፡ ይሔዱ ፡ የነበር ። ደጃች ፡ ንጉሤም ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ሰው ፡ ሰበሰቡና ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ተሻገሩ ፡ የስሜን ፡ የሳህላ ፡ የልዋሬ ፡ የጠለምትም ፡ ወታደር ፡ እበላለሁ ፡ እያለ ፡ ተከተላቸውና ፡ ወታደር ፡ በዛ ፡ ትግሬ ፡ ገብተው ፡ ተቀምጠው ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቆዩ ። ደጃች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ አባ ፡ ጎርፌ ፡ የራስ ፡ አርአያ ፡ ወንድም ፡ የትግሬ ፡ ገዢ ፡ ነበሩና ፡ ከአገው ፡ ንጉሤ ፡ ጋር ፡ በሐውዜን ፡ ወገን ፡ ሀራህር ፡ በሚባል ፡ ስፍራ ፡ ገጠሙ ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ጦርነት ፡ ተዋግተው ፡ በዝያን ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ሞቱ ፡ ደጃች ፡ ኀይለ ፡ ማርያምን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ አገው ፡ ንጉሤ ፡ አገው ፡ ተሰማ ፡ ሲባሉ ፡ የነበሩ ፡ ሁለቱ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ደጃች ፡ ተሰማ ፡ ተባሉ ፡ ጠቅልለው ፡ ትግሬን ፡ ያዙ ፡ የላስታ ፡ ወታደርም ፡ ብዙ ፡ ገባላቸው ፡ የወልቃይት ፡ የጠገዴ ፡ ወታደር ፡ ተሰበሰበ ፡ ወታደራቸውም ፡ የጠገበ ፡ ያጌጠም ፡ ነበረ ፡ ለባላገርም ፡ ለሁሉም ፡ ደጎች ፡ ነበሩ ፡ ጠቅላዩ ፡ ትልቁ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ናቸው ፡ እርሳቸው ፡ ጭራሽ ፡ ርኅሩኅ ፡ ናቸው ፡ የነበሩ ፡ ይላሉ ፡ ይቈረጥ ፡ በቃ ፡ የተፈረደበት ፡ እንደ ፡ ሆነ ። አያ ፡ እግርና ፡ ዕጅ ፡ በውሃ ፡ አይበቅልም ፡ ገርፈህ ፡ ስደደው ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። ይሞት ፡ በቃ ፡ ቢፈረድበትም ፡ ገንዘብ ፡ ይከፍሉ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ። በዚህ ፡ የተነሳ ፡ ወታደራቸው ፡ ቀለጤ ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ ሥራት ፡ አይመለከትም ፡ ነበር ፡ ብቻ ፡ ማጌጥና ፡ መብላት ፡ መጠጣት ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ አሳብ ፡ ያልነበራቸው ፡ ይመስላል ። እንዲህ ፡ ሁነው ፡ ተደላድለው ፡ ትግሬን ፡ ቀጥ ፡ አርገው ፡ ገዝተው ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ። የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ከሸዋ ፡ ገስግሰው ፡ አገዎች ፡ ሳይሰሙ ፡ ወደ ፡ ተምቤን ፡ ብቅ ፡ አሉ ፡ አገዎችም ፡ ወደ ፡ መረብ ፡ እቃቸውና ፡ መሳርያቸው ፡ እያራገፉ ፡ የመረብ ፡ አሸዋ ፡ እየዋጣቸው ፡ የደከመውን ፡ እየጣሉ ፡ ነጋሪታቸው ፡ በየዱሩ ፡ ባላገር ፡ እየለቀመው ፡ አሸዋ ፡ ለአሸዋ ፡ ይዘው ፡ ወልቃይት ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ትተው ፡ በረሀ ፡ ገቡ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ወደ ፡ አድዋ ፡ ገቡ ፡ ያንጊዜ ፡ የጥምቀት ፡ በዓል ፡ የመድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ ታቦት ፡ ሸኝተው ፡ አገቡና ፡ የአገዎች ፡ ጥለውት ፡ የሔዱ ፡ ነፍጥም ፡ እቃም ፡ ሰባሰቡና ፡ ወርደው ፡ አድያቦ ፡ አድአሮ ፡ ከሚባል ፡ ሰፈሩ ፡ ከዝያው ፡ ተነስተው ፡ የተከዜ ፡ የዋልቃይትም ፡ የዋልድባንም ፡ በረሀ ፡ ዳሰሱና ፡ ድብዛቸው ፡ ሲጠፋባቸው ፡ ጊዜ ። ወገራ ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ ሰፈሩ ፡ አገዎችን ፡ አለመገኘታቸው ፡ ተናደው ፡ ከወገራ ፡ ተነስተው ፡ አምባጫራን ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ ዱብረ ፡ ታቦር ፡ በዝያው ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ ጨጨሆ ፡ በርን ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በንዴት ፡ ሔዱ ፡ ንጉሥ ፡ ሸዋ ፡ ሔዱን ፡ በሰሙ ፡ ጊ

ዜ ፡ እነ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ትግሬ ፡ ገቡና ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ ሲበሉ ፡
ከረሙ ።

አጤ ፡ ቴዎድሮስም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ከሸዋ ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ገስግሰው ፡
በ፲፯ቀን ፡ አገዎች ፡ ሳይሰሙ ፡ አሳባቸውን ፡ ጥለው ፡ ንጉሥ ፡ ሸዋ ፡ ናቸው ፡
ብለው ፡ ሳለ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ተምቤን ፡ ዱብ ፡ አልዋቸው ፡ የአገው ፡
ጦርም ፡ አንድ ፡ ጠበንጃ ፡ ሳይተኰስ ፡ ፩ጦር ፡ ሳይወረውር ፡ ሁሉ ፡ ተያዙ ፡ እ
ኩሉም ፡ ጌታውን ፡ እየጣለ ፡ ወደ ፡ አድዋም ፡ ወደ ፡ አኵሱምም ፡ ገዳም ፡ ገ
ባ ፡ ደጃች ፡ ንጉሤና ፡ ደጃች ፡ ተሰማም ፡ ያንጊዜው ፡ ተያዙና ፡ ፪እግራቸው ፡
፪እጃቸው ፡ ጎምደው ፡ አሞራና ፡ ጅብ ፡ በላቸው ፡ አባ ፡ ዲራ ፡ ብሩ ፡ የሚባ
ል ፡ የተምቤን ፡ ሹም ፡ የነበረ ፡ በሸጉጥ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሞተ ፡ አሞራ ፡ በላው ፡
በትግሬ ፡ ይዘፈን ፡ ነበር ፡ አባ ፡ ዲራ ፡ ብሩ ። ሩባ ፡ ሩባ ፡ በልኽዎ ፡ አሟሩ ፡
እየተባለ ፡ ከደጃች ፡ ንጉሤ ፡ ጋር ፡ ተምቤን ፡ ያገኙቱ ፡ አንድ ፡ ሳይተው ፡ ቈ
ራርጠው ፡ ተፈጁ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አድዋ ፡ ወረዱና ፡ ከገዳም ፡ የገባ ፡ ሳይቀር ፡
ሞቻሉ ፡ ከእስላሞች ፡ መቃብር ፡ ሰብስበው ፡ እግርና ፡ እጁ ፡ እየበጠሱ ፡ ፈ
ጁት ፡ የጅብና ፡ ያሞራ ፡ ምግብ ፡ አደረጉት ፡ አድዋ ፡ የነበረ ፡ ጨርሰው ፡ ካ
በቱ ፡ አኩሱም ፡ ሒደው ፡ ከገዳም ፡ እያወጡ ፡ ቈራርጠው ፡ ፈጁት ። ያንጊ
ዜ ፡ ሣህሉ ፡ ተሰማ ፡ የሚባል ፡ ፈካሪ ፡ ጅግና ፡ የደጃች ፡ ንጉሤ ፡ አኰሱም ፡
ተገኘ ፡ አገሩ ፡ ወልቃይት ፡ ነውና ፡ አጤ ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሔደው ፡ ሳለ ፡ እንዲ
ህ ፡ እያለ ፡ ሲፎክር ፡ ኑሮ ፡ ነው ። መገን ፡ ሣህሉ ፡ ተሰማ ፡ አባ ፡ ጀቢራ ፡ ፶በፊ
ት ፡ ፶በኋላ ፡ ፶በቀኝ ፡ ፶በግራ ፡ ክርክር ፡ አይቀርም ፡ ከዝያ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ከ
ፍ ፡ ሲል ፡ ከዝያ ፡ ሰውየ ፡ ዝቅ ፡ ሲል ፡ ከጉብርየ ። አድዋ ፡ የተመዘዘ ፡ ፎንዜ ፡
ሸዋ ፡ ተሰማ ፡ በጊዜ ። እንዲህ ፡ እያለ ፡ ሲፎክርባቸው ፡ የነበረ ፡ በአኩሱም ፡
ተጌንቶ ፡ ተይዞ ፡ መጣ ፡ ንጉሡ ፡ እንዳዩት ፡ ፈታውራሪ ፡ ጉብርየን ፡ ተሎ ፡
ጥራ ፡ ብለው ፡ ተጠርተው ፡ መጡ ፡ ንጉሡም ፡ ጉብርየ ፡ የኔና ፡ ያንተ ፡ ወደ
ረኛ ፡ እየው ፡ አልዋቸውና ፡ ሣህሉ ፡ ተሰማን ፡ ፊክር ፡ አሉት ፡ እርሱም ፡ ሞ
ት ፡ ላይቀርብኝ ፡ አልፈክርም ፡ ብሎ ፡ እምቢ ፡ አለ ፡ ንጉሥም ፡ በአህያ ፡ አስ
ቀምጠው ፡ ሰፈሩን ፡ አዞሩት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያየው ።

ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ፍከራው ፡ አባ ፡ ጀቢራ ፡ ነበረ ፡ ቈራርጠው ፡ የጀቢራ ፡
ምግብ ፡ አደረጉት ፡ አገዎችን ፡ ቈራርጠው ፡ ጨርሰው ፡ ንጉሥ ፡ አገረዎን ፡
ተመልሰው ፡ ገቡ ።



## የንጉሥ ፡ ቴዎድሮስና ፡ የእንግሊዞች ፡

አጤ ፡ ቴዎድሮስና ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ በመጀመርያ ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡
ይላላኩ ፡ ነበር ፡ በምጥዋ ፡ የእንግሊዝ ፡ ቆንሱል ፡ ነበረና ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡
ሁለጊዜ ፡ ወደ ፡ ቈንሱሉ ፡ ይልኩ ፡ ነበር ፡ ልመናቸው ፡ ሰራተኞች ፡ እያሉ ፡
የብረት ፡ የእንጨት ፡ የናስ ፡ የመድፍ ፡ የጠበንጃ ፡ የአረብያ ፡ ብልሃት ፡ ይህ
ን ፡ ታገሬ ፡ አወጣለሁ ፡ ነበር ፡ ምኞታቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቈንሱል ፡ ኬምሮን ፡ የሚባሉ ፡ በንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡
ፈቃድ ፡ ተልከው ፡ ታጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መጡ ፡ ንጉሡም ፡ የቈንሱል ፡ ኬም
ሮንን ፡ ወደርስዎ ፡ መምጣት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከሃማሴን ፡ ጀምረው ፡ እስተ ፡
ጐንደር ፡ ድረስ ፡ ቈንሱሉ ፡ በሰፈሩበት ፡ በሚገባ ፡ መጥን ፡ ታዘዘ ፡ ፍሪዳው ፡
ማሩ ፡ ቅቤው ፡ ዶሮው ፡ እንቁላሉ ፡ እንጀራው ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ጠላው ፡ እ
ንደ ፡ ውሃ ፡ ተባላገር ፡ ተምስሌኔዎችም ፡ በያገሩ ፡ ያሉቱ ፡ ሁሉ ፡ ጠጃቸው ፡
እያሰናዱ ፡ እንዲቀበሉ ፡ ታዘዘ ። ቈንሱል ፡ ኬምሮን ፡ ይህን ፡ መጥናቸውን ፡
እየተቀበሉ ፡ እያመሰገኑ ፡ የተቀበላቸውም ፡ ሹም ፡ ጠበንጃ ፡ መሳይ ፡ ግምጃ
ም ፡ ብርም ፡ እየሸጓጐጡ ። የተቀበሉትንም ፡ መጥን ፡ እየጣፉ ፡ በአድዋ ፡
አርገው ፡ በሽሬ ፡ መንገድ ፡ ወገራን ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ ጐንደር ፡ ንጉሡ ፡ ጐ
ንደር ፡ ላይ ፡ አደራ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተሜዳው ፡ ላይ ፡ ሰፍረው ፡ ነበሩና ። ቈን
ሱል ፡ በሚገቡበት ፡ ቀን ። የንጉሡ ፡ ወታደር ፡ ተሰልፎ ፡ በቀኝ ፡ በግራ ፡
ታጅበው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርሱ ፡ መድፍም ፡ ጠበንጃም ፡ እየ
ተንጧጣ ፡ ጢሱ ፡ እንደ ፡ ጉም ፡ እስኪሆን ፡ ላይን ፡ እስቲጨልም ፡ ባንድ ፡
ወገን ፡ ፈረሰኛ ፡ መሬቱን ፡ አላብሶ ፡ ነጋሪትም ፡ እምቢልታውም ፡ ቀንደ ፡
መልኸት ፡ መሬቱን ፡ የሚፈነቅል ፡ እየመሰለ ፡ ግምጃ ፡ ድንኳን ፡ ተቀጥሎ ፡
ተቀጥሎ ፡ እየገጠመ ፡ ምንጣፍ ፡ ሞልቶ ፡ አደባባዩም ፡ ሁሉ ። በምንጣፍ ፡
ተሸፍኖ ፡ ለትንግርት ። ንጉሡም ፡ ልብሰ ፡ መንግሥተዎ ፡ እንደ ፡ ለበሱ ፡ ዘ
ውደዎን ፡ በራሰዎ ፡ ደፍተው ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ አራቱ ፡ ሊቀ ፡ መንኳሶች ፡ ን
ጉሡ ፡ እንደ ፡ ለበሱት ፡ ያለ ፡ ካባ ፡ ላንቃ ፡ ለብሰው ፡ ለብሰው ፡ የቀረው ፡ ራ
ስም ፡ ደጃዝማችም ፡ እንደ ፡ ተሸለመ ፡ ራሶችም ፡ ራስ ፡ ወርቃቸውን ፡ እያሰ
ሩ ፡ በቀኝና ፡ በግራም ፡ የንጉሡ ፡ ጋሻጀግሮች ፡ ጣፋ ፡ ጣፋ ፡ ጋሻውንና ፡
ጠበንጃውን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ዙርያውን ፡ ከበ ፡ መቸም ፡ ጋ

ሻ ፡ ዤግሮች ፡ የተባሉ ፡ ረጅም ፡ ረጅሞችን ፡ እየመረጡ ፡ ነው ፡ አርገዋቸው ፡ የነበሩ ፡ ሁሉም ፡ ስታያቸው ፡ ያስፈራሉ ፡ ሹርቤአቸው ፡ ጎመድ ፡ ጎመድ ፡ አስመስለው ፡ ግድግዳ ፡ የተማገረ ፡ መስለው ፡ ቆሙ ።

ተዚህ ፡ በኋላ ፡ ቈንሱል ፡ ኬምሮንም ፡ ያገራቸውን ፡ ሽልማት ፡ እንደ ፡ ተሸለሙ ፡ ቀሚሳቸው ፡ የሚጐነተር ፡ የመሰለ ፡ ወርቅ ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ በትከሳቸው ፡ የሚወርድ ፡ ኳስወርቅ ፡ ነበረ ፡ በደረታቸውም ፡ ሀረግ ፡ የመሰለ ፡ ወርቅ ፡ ነበረበት ፡ በሱሪያቸውም ፡ በሁለቱ ፡ አውራጃ ፡ በጭናቸው ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፡ የክንዳቸው ፡ ሽራጥና ፡ የቆባቸው ፡ ላይን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፡ የጎራዴያውም ፡ ኳስ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፡ መቸም ፡ ቁመታቸው ፡ ዘንጠፍ ፡ ያሉ ፡ ነበሩና ፡ ጎራዲያቸው ፡ ምድር ፡ እየነካ ። መጥተው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሱ ፡ ቈንሱል ፡ ሲገባ ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩ ፡ ሁሉ ፡ መኳንንት ፡ ቁመው ፡ ቆዩ ፡ ንጉሡም ፡ እንዲያ ፡ ሳይጨርሱት ፡ እንደ ፡ መቆም ፡ ብለው ፡ አክብረው ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ከሚቀመጡበት ፡ ወምበር ፡ ላይ ፡ እስቀመጥዋቸውና ፡ ባስተርጓሚ ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር ፡ ቈንሱልም ፡ ጥቂት ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፡ የንግሥት ፡ የሰላምታ ፡ ደብዳቤ ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጡ ፡ ንጉሥም ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ በክብረት ፡ ደብዳቤውን ፡ ተቀብለው ፡ አነቡቡና ፡ ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር ። በስከወድያው ፡ ግብር ፡ መጣና ፡ አደራሹ ፡ ግጥም ፡ አለ ፡ ለቈንሱልም ፡ በፈረንጆች ፡ ወጥ ፡ አስርተውላቸው ፡ ነበርና ፡ ማለፍያ ፡ ጥብስም ፡ እየመጣ ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ የማር ፡ ጠጅም ፡ እያማረጡ ፡ ተዝያም ፡ ተዝያም ፡ እየቀማመሱ ፡ አስተርጓሚው ፡ ቀርበ ። ማለፍያ ፡ ማለፍያውን ፡ ጨወታ ፡ ሲጫወቱ  መቸም ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጨወታ ፡ ሲጫወቱ ፡ ደስ ፡ ያሰኛሉ ፡ ሲቆጡ ፡ ቀን ፡ አያድርስ ፡ ይለዋል ፡ እንጅ ።

በዚህ ፡ ነገር ፡ አዝማሪ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገጠማላቸው ። በፊት ፡ ያን ፡ አዝማሪ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አጫውተኝ ፡ እያሉት ፡ ሲስቁለት ፡ እሱም ፡ ሲያስቃቸው ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ አድጦት ፡ መሰለኝ ፡ አጤ ፡ ቴድሮስ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ቡልጭ ፡ ብለውታል ፡ መሰለኝ ፡ ያአዝማሪ ፡ ቶሎ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገጠመ ፡ ፍቅሩን ፡ ጨርሶ ፡ ጠቡን ፡ ሲያመጣው ፡ ሞላጫ ፡ ገደል ፡ ዝንጀሮ ፡ አይወጣው ። አላቸውና ፡ ሳቁለት ፡ ይላሉ ። ወደ ፡ ቈንሱል ፡ እንመለስ ፡ መልካሙን ፡ ጨወታ ፡ እየተጫወቱ ፡ ቆዩ ፡ መቸም ፡ ሙሉግብር ፡ ነው ፡ ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡ አዝማሪዎችም ፡ ሸለሌ ፡ እያሉ ፡ ተጫውተው ፡ ታበቁ ፡ ወድያው ፡ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሆነና ፡ ቆንሱልም ፡ ወደ ፡ ታዘዘላቸው ፡ ስፍራ ፡ ሔዱ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ የዘበኛው ፡ አለቃ ፡ ታዞ ፡ እምቢልታውም ፡ አጀቡም ፡ እየተመመ ፡



ወደ ፡ ታዘዘው ፡ ቤት ፡ ገቡ ፡ ከዝያውም ፡ ቤት ፡ አደራሹ ፡ ምንጣፍ ፡ ሞልቶ ፡ አልጋው ፡ ሰጋጃና ፡ ዋላንሳ ፡ ተነጥፎ ፡ የንጉሡ ፡ ግብርም ፡ አስቀድሞ ፡ አልፎ ፡ ከዝያው ፡ ሞሰቡና ፡ ገምቦው ፡ የተሰጣ ፡ በርበሬ ፡ መስሎ ፡ ቀዋሞችና ፡ ገምቦኞች ፡ ባሮች ፡ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ የተሰበሰበ ፡ ቁራ ፡ መስሎ ፡ ፍሬዳው ፡ እምቧ ፡ እያለ ፡ በጉም ፡ ሟ‍ኧ ፡ እያለ ፡ ቆየና ፡ ወድያው ፡ ቈንሱል ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ የአዛዡ ፡ ተወራጅ ፡ ገብቶ ። እንሆ ፡ ፶ላም ፡ ፻በግ ፡ ፪ሽህ ፡ እንጀራ ፡ ፴ጋን ፡ ጠጅ ፡ ፲ገምቦ ፡ ማለፍያ ፡ ጠጅ ፡ ፲ገምቦ ፡ አዋዜ ፡ ካራውም ፡ እንጨቱም ፡ ሣሩን ፡ አበረከተ ፡ ቈንሱልም ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ አሉና ፡ ቀጥለው ፡ ይሄን ፡ ሁሉ ፡ የሚፈጅ ፡ ሠራዊት ፡ የለኝ ፡ ፫ላም ፡ ፲በግ ፡ ይበቃኛል ፡ አሉና ፡ የተረፈው ፡ ውሰዱት ፡ ብለው ፡ ተናገሩና ፡ በዝያው ፡ ጠነከሩ ፡ ሹሙም ፡ ሒዶ ፡ ለጃንሆይ ፡ ነገረ ፡ ንጉሡም ፡ መልሰው ፡ ለወጉ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ እንኳን ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ በንግሥት ፡ የከበረ ፡ ሹም ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደብዳቤ ፡ ይዞ ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ አክብሮ ፡ መቀበል ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ ላኩና ፡ ቈንሱልም ፡ ተቀብለው ፡ ዝም ፡ አሉ ፡ በበነገታውም ፡ ቈንሱል ፡ ኬምሮን ፡ የንግሥትን ፡ መተያያ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ የሰደዱት ፡ ጠበንጃም ፡ ኩብሱልም ፡ ባሩድም ፡ ፪አፍ ፡ ሽጉጦችም ፡ ሁሉ ፡ ባለ ፡ ድብ ፡ ነው ፡ ምንጣፍም ፡ ግምጃም ፡ ሰርፍም ፡ ግዛምዛም ፡ ሰጡና ። ቀጥለውም ፡ የሳቸው ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሰጡ ፡ ንጉሡም ፡ የንግሥቲቱና ፡ የቈንሱል ፡ መተያያ ፡ በፍቅር ፡ አመስግነው ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ ብለው ፡ ተተቀበሉ ፡ በኋላ ፤ በስከውድያው ፡ ግብር ፡ ገባ ፡ ተበልቶ ፡ ተጠጥቶ ፡ ታበቃ ፡ በኋላ ፡ ምላሽ ፡ አሰኝተው ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ነገር ፡ መልካካሙን ፡ ጨወታና ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር ፡ ንጉሥም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ያገረዎን ፡ የቀድሞውን ፡ የነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ የራሳቸውንም ፡ የተዋጉበትን ፡ የደስታውንም ፡ የመከራውን ፡ የሁሉንም ፡ ይጫወታሉ ። ቆንሱልም ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ የመንግሥቱን ፡ የወታደሩን ፡ ስራት ፡ የባላገሩን ፡ ስራት ፡ አኗኗሩና ፡ አገዛዙ ፡ የምድር ፡ ባቡርና ፡ የባሕር ፡ መርከቡን ፡ ሰራተኞቹም ፡ እደሚሰሩቱ ፡ ስራ ፡ ያገሩም ፡ ልማት ፡ የምድሩም ፡ ስፋት ፡ በየነጋዴው ፡ የሚቀረጠውን ፡ እና ፡ የሚገባው ፡ ወርቅ ፡ ከባላገርም ፡ የሚገባውን ፡ የጅኒ ፡ ወርቅ ፡ የዚህን ፡ ሁሉ ፡ በየአመቱ ፡ እያሰሉ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ደሞ ፡ ንግሥታችን ፡ አይደክሙ ፡ አይዋጉ ፡ በእረፍት ፡ ተቀምጠው ፡ ይኖራሉ ፡ እያሉ ፡ የለት ፡ የለት ፡ የሚገርምና ፡ የሚደነቅ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያልታየና ፡ ያልተሰማ ፡ ነገር ፡ የሎንደራም ፡ የከተማዋ ፡ ስፋት ፡ የሰዎችዋም ፡ ብዛት ፡ የመንገድዋም ፡ አጠራረግ ፡ መግብያና ፡ መውጫዋም ፡ የግምብዋም ፡ ስራ ፡ የመብራትዋም ፡

የጨወታዋም ፡ የሴት ፡ ዘበኛዋም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ኰንሱሉ ፡ ለንጉሥ ፡ ሁለ ፡ ጊዜ ፡ ያጫውቱአቸው ፡ ነበር ፡ ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እየሰሙ ፡ ይቀኑ ፡ ነበር ፡ ደሞም ፡ ያገሬ ፡ ሰው ፡ አይገዛምኝ ፡ እንጅ ፡ እኔም ፡ ተላንተ ፡ ተተፋቀርሁ ፡ እኔም ፡ ባገሬ ፡ እንደ ፡ ዚሁ ፡ ለማድረግ ፡ አስባለሁ ፡ ይላሉ ።

ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ሰነበቱና ፡ ቈንሱል ፡ ኬምሮን ፡ አገሬን ፡ ልሔድ ፡ ፈቃድ ፡ ይስጡኝ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ ንጉሡም ፡ እሺ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ የሚሔድ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ወርቅ ፡ መጣምር ፡ ኮርቻ ፡ ወርቅ ፡ ርባን ፡ ጋሻ ፡ ወርቅ ፡ ጫማ ፡ ሰጡአቸው ። ከነደብዳቤው ፡ ጭምር ።

ለቈንሱል ፡ ኬምሮንም ፡ ማለፍያ ፡ የተንቈጠቈጠ ፡ ወርቅ ፡ ዘቦ ፡ ቀሚስ ፡ ማልፍያ ፡ ድርብ ፡ መርገፍ ። ጣፋ ፡ ጋሻ ፡ ወርቅ ፡ ቅብ ፡ ለምድ ፡ ማልፍያ ፡ በቅሎ ፡ ባለ ፡ ጥልፍ ፡ ማለፍያ ፡ ፈረስ ፡ ተነ ፡ መጣምሩ ፡ ጫሜ ፡ ጎራዴ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ሸለሙና ። መጥን ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ እየታዘዘ ፡ በሽሬ ፡ መንገድ ፡ አርገው ፡ አኵሱም ፡ ገብተው ፡ ከዝያው ፡ ጥቂት ፡ ሰንብተው ፡ ወደ ፡ አድዋ ፡ መጡ ፡ በአድዋም ፡ ጥቂት ፡ ሰነበቱና ፡ መረብ ፡ ተሻግረው ፡ በአዲ ፡ ኋላ ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ አስመራ ፡ ከአስመራ ፡ ወደ ፡ ምጥዋ ፡ ገቡ ፡ የናይብ ፡ ሙሐድ ፡ ሰዎቹም ፡ መንገድ ፡ ይመሩ ፡ ነበር ፡ ተዚህ ፡ በኋላ ፡ ቆንሱል ፡ ኬምሮን ፡ በምጥዋ ፡ ሁነው ፡ ባለቤታቸው ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ሳይሔዱ ፡ ያጤ ፡ ቴዎድሮስን ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በመርከብ ፡ በቡስጣ ፡ ሰደዱ ፡ ይሉናል ።

ንግሥት ፡ ቢክቶርያም ፡ ያን ፡ የአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደብዳቤና ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሰለ ፡ ፍቅር ፡ አመስግነው ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ ብለው ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ስለ ፡ ለመኑት ፡ ነገርና ፡ ስለ ፡ ሰደዱላቸው ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ የዚያነን ፡ ሁሉ ፡ ምላሽ ፡ በደብዳቤ ፡ አጽፈው ፡ መልሰውም ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አስይዘው ። ቈንሱል ፡ ኬምሮንን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ንግሥት ፡ ቤክቶርያ ፡ ወደ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልከው ፡ ሰደድዋቸው ፡ ኰንሱል ፡ ኬምሮንም ፡ መቸም ፡ ፍቅር ፡ አድርጌአለሁና ፡ ብለው ፡ በመተማ ፡ መንገድ ፡ አቅንተው ፡ በትግሬ ፡ እንዳይመጡ ፡ ስለ ፡ መጥኑ ፡ እንዳያስቸግሩ ፡ ይመስላል ፡ በጭልጋ ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ ደምብያ ፡ መጡ ፡ ከንጉሥ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጋራም ፡ በዝያው ፡ በአዘዞ ፡ ወይም ፡ በጀንዳ ፡ ተገናኙ ፡ እና ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስም ፡ አክብረው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ተቀበልዋቸው ፡ የንግሥትም ፡ ደብዳቤ ፡ ተቀበሉና ፡ አዩ ፡ ያየሚፈልጉት ፡ ነገር ፡ ለገና ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አዩት ፡ እና ፡ እየተጫወቱ ፡ መልካም ፡ መልካሙን ፡ እያወጋጉ ፡ ሰነቡቱ ።



ጥቂት ፡ ሰንብተው ፡ የመከሩ ፡ መክረው ፡ ምክሩም ፡ ያየምለምነው ፡ ነገር ፡ ቈንሱልን ፡ ያሰርሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንግሥቲቱ ፡ በግድ ፡ እሱን ፡ ስለ ፡ ማስፈታት ፡ ትሰዳለች ፡ ይህን ፡ በሆዳቸው ፡ መከሩ ፡ እንጅ ፡ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ ጦር ፡ መጥቶ ፡ ይጐዳኛል ፡ ተሆደዎ ፡ አልገባም ።

ደግሞ ፡ መልክተኛውን ፡ ስለ ፡ ማሰር ፡ ምህኛት ፡ ፈለጉና ፡ ቈንሱል ፡ ኬምሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

በፊት ፡ ወደ ፡ ንግሥቲቱ ፡ ጽፌ ፡ የሰጠሁን ፡ ደብዳቤ ፡ ባለ ፡ ቤትህ ፡ በእጅህን ፡ ለንግሥት ፡ ሰጠህ ፡ ወይስ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ሰደድከው ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ።

ቈንሱል ፡ ኬምሮንም ፡ እኔስ ፡ አልሔድሁም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በቶሎ ፡ እንዲደርስ ፡ በባቡር ፡ ሰደድሁትና ፡ ምላሹም ፡ ከንግሥት ፡ በቶሎ ፡ መጣልኝና ፡ ደግሞ ፡ ባለቤትህ ፡ ወደ ፡ ጃንሆይ ፡ ይዘህ ፡ ሂድ ፡ ብለውኝ ፡ ይሄው ፡ ባለ ፡ ቤቴ ፡ ይገኛ ፡ መጣሁ ፡ አሉና ፡ ኮንሱል ፡ ኬምሮን ፡ መለሱ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በፍከራ ፡ አልጋዎ ፡ ሊሰበር ፡ እስቲቀርብ ፡ ይንደቀደቁ ፡ ጀመር ፡ እኔ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ አንት ፡ ነጭ ፡ ሙርጥ ፡ እኔ ፡ አንሽህእነው ፡ የኔን ፡ የኔን ፡ ደብዳቤ ፡ በጅህ ፡ አለመስጠትህ ፡ አሉና ፡ በል ፡ ንሳ ፡ ያዘው ፡ አሉና ፡ በጥፊ ፡ እየመቱ ፡ ወታደሮች ፡ አሰርዋቸው ፡ አብረዋቸው ፡ የነበሩም ፡ የእንግሊዝ ፡ ሰዎችም ፡ ታሰሩ ፡ ገንዘባቸውም ፡ ሁሉ ፡ ተቈጥሮ ፡ ወደ ፡ እቃቤት ፡ ገባ ።

ንጉሡም ፡ እየመለሱ ፡ ይፈክሩ ፡ ጀመር ፡ እንኳን ፡ ይሄ ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ ሙርጥ ፡ ወታደር ፡ እሷዋ ፡ ራስዋ ፡ ብትሆን ፡ ባሕር ፡ ተማምና ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ መጥታ ፡ ተሜዳላይ ፡ አትገጥመኝም ። እኔ ፡ አንድ ፡ የናቱ ፡ እያሉ ፡ ፈከሩ ።

ኰንሱል ፡ ኬምሮንም ፡ ከዝያው ፡ ታደባባይ ፡ ታስረው ፡ ጥቂት ፡ ሰነበቱና ፡ እንደ ፡ ታሰሩ ፡ ወደ ፡ መቅላ ፡ ሰደድዋቸው ፡ አብሮአቸው ፡ የታሰሩትም ፡ ነጮች ፡ አብረው ፡ ሄዱ ፡ አብረው ፡ የታሰሩ ፡ ስማቸው ፡ ኬረንስ ፡ መኬልቢ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሰዎች ፡ ባርደል ፡ የሚባል ፡ ፈረንሳዊ ፡ ይመስለኛል ፡ ማክረር ፡ የሚባል ፡ ወጥቤት ፡ ነበረ ፡ ቴዴስክ ፡ ይመስለኛል ፡ እነዚህ ፡ ተኮንሱል ፡ ጋር ፡ የታሰሩ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ አብረው ፡ ሄዱ ፡ ኰንሱልም ፡ እግር ፡ ተወርች ፡ ታስረው ፡ ረጅም ፡ ናቸው ፡ የነበሩና ፡ ጎብጠው ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ ሰሙና ፡ ወደ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ደብዳቤ ፡ ሰደዱ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ኰንሱል ፡ ኬምሮንን ፡ ፈትተው ፡ እንዲሰዱልኝ ፡ እለምናለሁ ። ለርሰዎ ፡ የበደለዎን ፡ በደልም ፡ በደብዳ

ቤ ፡ ጽፈው ፡ ይስደዱልኝ ፡ እና ፡ ባለ ፡ ቤቴ ፡ እቀጣው ፡ አለሁ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡ ማፋቀር ፡ ነው ፡ የሰደድሁት ፡ እንጅ ፡ ለጠብ ፡ አልሰደድሁትም ፡ ብሎ ፡ ደብዳቤው ፡ ተነበበ ።

የመይሳ ፡ ልጅ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ የናቱ ፡ እች ፡ ነጭ ፡ ሙርጥ ፡ አሁን ፡ ያን ፡ ሎሌዋ ፡ ቄራርጨ ፡ ለውሻ ፡ በሰጠሁት ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የምታረግ ፡ ባሕር ፡ ተማምና ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ከሜዳ ፡ ወጥታ ፡ አትገጥመኝም ፡ የሐበሻ ፡ ባል ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ውሽማ ፡ አሁን ፡ ምጥዋን ፡ አክ ፡ ብየ ፡ እንትፍ ፡ ልበልባት ፡ አሉና ፡ ፈከሩ ። መልክተኛውንም ፡ አዋርደው ፡ አሰሩዋቸው ፡ ባሻ ፡ ፈለቀ ፡ ይመስለኛል ፡ በእንግሊዝ ፡ ስማቸው ፡ እስፒዲ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ አስረው ፡ ባሻ ፡ ፈለቀን ፡ ፈቱዋቸውና ፡ እንዲህም ፡ አልዋቸው ። መድፍ ፡ ጠበንጃ ፡ ባሩድም ፡ ከብሱል ። አስይዘህ ፡ ሰራተኞም ፡ ጨምረህ ፡ ብትመጣ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በተፋቀርን ፡ ኰንሱል ፡ ኬምሮንም ፡ ፈትቸ ፡ በሰደድሁት ፡ አሉና ፡ ተናገሩ ፡ መቸም ፡ ፊት ፡ እንዳሰቡት ፡ ኰንሱል ፡ አስሬ ፡ ሰራተኞችና ፡ መድፍ ፡ እገላገላለሁ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ ጦር ፡ መጥቶ ፡ ይወጋኛል ፡ ተልበዎ ፡ አሳብ ፡ አልነበረም ።

ባሻ ፡ ፈለቀም ፡ እሽ ፡ ጀንሆይ ፡ ይህ ፡ አይቸግረኝም ፡ ባለ ፡ ቤቴ ፡ አደርገዋለሁ ፡ አሉ ፡ ስለ ፡ መውጫ ፡ ብለው ፡ አማርኛ ፡ ቋንቋም ፡ ይናገራሉ ፡ ደሞ ፡ ባሻ ፡ ፈለቀ ፡ ሲናገሩ ፡ አነጋገራቸው ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ከሀበሻ ፡ ወታደሮች ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ይመስላሉ ፡ ንጉሥም ፡ እውነት ፡ መሰለዎና ፡ ባሻ ፡ ፈለቀን ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ሰድዋቸው ።

ተዝያ ፡ ወድያ ፡ ባሻ ፡ ፈለቀ ፡ ሎንደን ፡ ገቡና ፡ ለንግሥት ፡ መከራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ያልዋቸውን ፡ ተናግረው ፡ ታበቁ ፡ ወድያ ፡ ባሻ ፡ ፈለቀ ወደ ፡ ሐበሻ ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ተመልሰው ፡ ለመዋጋት ፡ ከንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ ለመኑ ፡ እንጅ ፡ ስለ ፡ ዕርቅ ፡ አለመኑም ፡ ይላሉ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ መሪ ፡ ሁነው ፡ መጡና ፡ የሚቀበለኝ ፡ ካገኘሁስ ፡ እንደ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ላኩኝ ፡ መድፍና ፡ ጠበንጃ ፡ ይገኛ ፡ መጥቸ ፡ አለሁ ፡ እያሉ ፡ ያቧልቱ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ። መልሰው ፡ መልክተኛ ፡ ሰደዱ ፡ ምስተር ፡ ራሰም ፡ የሚባሉ ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ ንግግርና ፡ ምላሽ ፡ ያወቁ ፡ ከርሻቸውም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሃኪምና ፡ አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ነበሩ ፡ ስማቸውም ፡ ዶክተር ፡ ብላንክ ፡ ምስተር ፡ ጥሪዶ ፡ የሚባሉ ። እነዚህ ፡ ሶስቱ ፡ ንጉሥ ፡ ቄራጣ ፡ በሚባል ፡ ሰፍረው ፡ ሳሉ ፡ ወደ ፡



አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ መጡ ፡ ንጉሡም ፡ በክብረት ፡ እንደ ፡ ሚገባ ፡ አርገው ፡ ተቀበልዋቸውና ። በሰከ ፡ ወድያው ፡ የንግሥት ፡ ደብዳቤና ፡ ያመጡትንም ፡ ግምጃም ፡ ምንጣፍም ፡ መተያያ ፡ ሰጡና ። ንጉሡም ፡ ፊታቸው ፡ ብርሃን ፡ አርገው ፡ ያጫውቱዋቸው ፡ ጀመሩ ።

ምስተር ፡ ራሰምም ፡ እጅግ ፡ አዋቂ ፡ ናቸውና ፡ መልካም ፡ መልካሙን ፡ ጨወታና ፡ ምላሽ ፡ ይመልሱላቸዋል ፡ ሲናገሩም ፡ በዓረብ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር ። ንጉሡም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ አረብኛ ፡ ጥቂት ፡ ይሰማሉና ።

የንግሥቲቱ ፡ ደብዳቤም ፡ ቃሉ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፡ የኔ ፡ ሎሌና ፡ ሹም ፡ ኮንሶል ፡ ኬምሮን ፡ እኔንና ፡ እርሰዎን ፡ ሰለ ፡ ማፋቀር ፡ ነው ፡ የሰደድሁት ። እርሱ ፡ ግን ፡ አላፋቀረነም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እሷን ፡ ስለ ፡ በደለ ፡ ታሰረ ። አሁን ፡ ግን ፡ የኔ ፡ ሹም ፡ ምስተር ፡ ራሰምን ፡ ሃኪም ፡ ብላንክና ፡ ጥሪዶ ፡ ከርሰዎ ፡ ሰድጀ ፡ አለሁ ፡ ራሰም ፡ የነገረዎን ፡ ሁሉ ፡ እንደኔ ፡ ቃል ፡ ነውና ፡ እርሱ ፡ ያለዎን ፡ እንዲያረጉልኝ ፡ እለምናለሁ ። እኔም ፡ እስሮችን ፡ ፈትተው ፡ ራሰምና ፡ ሰዎቹ ፡ ወደኔ ፡ ሲመለሱ ፡ አሳበዎን ፡ አደርጋለሁ ። ከዝያ ፡ ወድያም ፡ የኔና ፡ የርሰዎ ፡ ፍቅር ፡ ይጠናከራል ። አደራ ፡ በሰማይ ፡ አደራ ፡ በምድር ፡ ብየ ፡ አማጥናለሁ ፡ በቶሎ ፡ ሰዎቸን ፡ እንዲሰዱልኝ ፡ ብለው ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥተ ፡ ንግሥት ፡ በደብዳቤ ፡ ላኩና ። አቶ ፡ ራሰምም ፡ መቸም ፡ ሲናገሩ ፡ አሳምረው ፡ ነውና ። በሰከ ፡ ወድያው ፡ በቃል ፡ ተናገሩ ፡ ንጉሡም ፡ እሽ ፡ ያልኸኝ ፡ ሁሉ ፡ አረግልህ ፡ አለሁ ፡ ኬምሮንም ፡ ፈትቸ ፡ እሰጥሀለሁ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ አቶ ፡ ራሰምም ፡ እጅ ፡ ነሱና ። እንዲህም ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ ጃንሆይ ፡ ካረጉት ፡ አይቀር ፡ በመቅደላ ፡ ያሉት ፡ እስሮች ፡ ነጮች ፡ የሆኑ ፡ ይፍቀዱልኝ ፡ እና ፡ ሁሉን ፡ ይፍቱልኝ ፡ ሙሉ ፡ ደስታና ፡ ፍቅር ፡ እንዲሆን ፡ ብለው ፡ ለመኑ ። አጤ ፡ ቴዎድሮስም ፡ እሽ ፡ እንዳልኸው ፡ ይሁንልህ ፡ ይፈቱ ፡ አሉና ። አቶ ፡ ራሰምም ፡ ሃኪም ፡ ብላንክም ፡ ጸሐፊ ፡ ብሪዶም ፡ እየተነሱ ፡ እጅ ፡ ነሱ ፡ የንጉሥ ፡ መኳንንት ፡ ሁሉም ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ፍቅር ፡ ንጉሣችን ፡ ተፋቀሩ ፡ ብሎ ። በስከ ፡ ወድያ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ከእስር ፡ ጠባቆች ፡ ደብዳቤ ፡ አስጻፉና ፡ ሰደዱ ፡ ኮንሱል ፡ ኬምሮንና ፡ ከዝያ ፡ ያሉ ፡ የታሰሩ ፡ ነጮች ፡ ፈትታችሁ ፡ ለሰደድኋቸው ፡ አለቆች ፡ ሰጥታችሁ ፡ ስደዱ ፡ አሉና ። ወደ ፡ መቅደላ ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ ብዙ ፡ ነፍጠኛ ፡ ሔደ ፡ ኰንሱል ፡ ከነ ፡ ሰዎቹ ፡ ይዘው ፡ ለመምጣት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በታንኳ ፡ ሆኑና ፡ ራሰም ፡ ከሰዎቻቸው ፡ ጋር ፡ ይዘው ፡ ሁሉም ፡ በታንኳ ፡ ሆኑና ፡ ከቄራጣ ፡ ወደ ፡ ዘጌ ፡ ባሕር ፡ ለባ

ሕር ፡ አርገው ፡ አሣ ፡ ወጋሮችም ፡ በመቃጥን ፡ ሰው ፡ ሰው ፡ የሚያህል ፡ አሣ ፡ እያወጡ ፡ ወይጦም ፡ ጉማሬ ፡ እየገደለ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ እያመጡ ፡ ለእንግሊዞች ፡ እየሰጡ ፡ ደግሞ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ደሴት ፡ የቆራጣም ፡ ቡፍና ፡ በ'ኹረ ፡ ሎሚው ፡ አደሱም ፡ ገነት ፡ ነው ፡ የሚመስል ፡ ከባሕር ፡ ዳሩም ፡ እየሆኑ ፡ ወደ ፡ ጉማሬ ፡ ይተኰሳሉ ፡ ንጉሡም ፡ እነዝያም ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ በታንኳ ፡ እየሆኑ ፡ ሲናፈሱ ፡ ጊዜ ። እንግሌዞች ፡ ደስ ፡ ብሎአቸው ፡ ነበር ። በወዲህ ፡ የመጣነበት ፡ ነገር ፡ ሰዋችን ፡ አስፈትተን ፡ በወዲህም ፡ ባሕሩንና ፡ ጀልባው ፡ ያገራቸው ፡ እየመሰላቸው ፡ ደሰ ፡ አላቸውና ። ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከዝያው ፡ ከዘጌ ፡ ሳሉ ፡ እስሮቹ ፡ ተፈትተው ፡ ወደ ፡ ቈራጣ ፡ ገቡ ። ብሎ ፡ የንጉሡ ፡ አለቃ ፡ መጥቶ ፡ ለንጉሥ ፡ ነገረ ፡ ንጉሡም ፡ ወድያው ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፡ ራሰምን ፡ ጥራ ፡ አሉና ፡ አቶ ፡ ራሰምን ፡ ከሰፈራቸው ፡ አስጠርተው ፡ አምጥተው ፡ የምሥራች ፡ ኰንሱል ፡ ኬምሮን ፡ ከነሰዎቹ ፡ ተፈትቶ ፡ ቋራጣ ፡ ገባ ፡ አልዋቸው ፡ ምስተር ፡ ራሰምም ፡ የንጉሡ ፡ እጅ ፡ እና ፡ እግር ፡ ሳሙና ፡ እንግዲህ ፡ የጃንሆይና ፡ የንግሥታችን ፡ ፍቅር ፡ እስተ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ያልፋል ፡ አሉና ፡ ብዙ ፡ ፍሥሐ ፡ አደረጉ ። ደግሞም ፡ ለመኳንንትም ፡ ብዙ ፡ መቆላመጫ ፡ ይሰጡ ፡ ነበርና ፡ የንጉሡ ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ጌታ ፡ ራሰምም ፡ ብዙ ፡ መጠጥና ፡ ገንዘብ ፡ አጥፍተው ፡ አደሩ ።

ጌታ ፡ ራሰም ፡ በነገታው ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሔዱና ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ቁመው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ እሥሮቹ ፡ ተዚህ ፡ መጥተው ፡ ከጃንሆይ ፡ እጅ ፡ ቢነሱን ፡ ይሻላል ፡ ወይስ ፡ በዝያው ፡ ይሒዱ ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ፡ ንጉሡም ፡ አንደ ፡ ጊዜ ፡ ላንተ ፡ ስል ፡ ምሬልህ ፡ አለሁ ፡ በወድያ ፡ ይሒዱ ፡ እንጅ ፡ ተኔ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አላቸው ፡ አሉና ፡ መለሱ ።

ጌታ ፡ ራሰምም ፡ የንጉሥ ፡ እጅ ፡ ሳሙና ፡ ወደ ፡ እስሮቹ ፡ መልክተኛ ፡ ሰደዱ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጃንሆይ ፡ ስለ ፡ ንግሥታችን ፡ ፍቅር ፡ ብለው ፡ ምረዋችኋልና ፡ እኔ ፡ ከንጉሥ ፡ ተሰናብቸ ፡ እሰከመጣ ፡ ድረስ ፡ በደምብያ ፡ መንገድ ፡ ተጓዙ ፡ ብለው ፡ የንጉሥ ፡ ሰውም ፡ መሪ ፡ ሰጥተው ፡ ወደ ፡ ቋራጣ ፡ ላኩ ፡ እርሳቸው ፡ ዘጌ ፡ ላይ ፡ ሁነው ።

ለኰንሱል ፡ ኬምሮንም ፡ ተአገራቸው ፡ የመጣላቸውን ፡ ልብስ ፡ ሰደዱላቸውና ። እሰሮች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ የሐበሻ ፡ አሽከርና ፡ ገረዶችም ፡ እልል ፡ አሉና ። ከቈራጣ ፡ ተነስተው ፡ የደምብያን ፡ መንገድ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ጭልጋ ፡ መንገድ ፡ ተጓዙ ፡ የንጉሡ ፡ መሮችም ፡ መቸም ፡ አብረዋቸው ፡ ነበሩ ።



ሁለት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ፫ቀን ፡ እንደ ፡ አደረጉ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ የምን ፡ ሰደድኋቸው ፡ የሚል ፡ ጠጠት ፡ በሆዳቸው ፡ ገባና ፡ የሰይጣን ፡ ምክር ፡ ሲመክሩ ፡ አድረው ፡ በማለዳ ፡ ራሰምን ፡ ጥራ ፡ አሉና ፡ ራሰም ፡ ተጠርተው ፡ መጡ ፡ ሊያሰናብትዋቸው ፡ መስሎዋቸው ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ሒደው ፡ ተንጉሥ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ። ንጉሡም ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ ምነው ፡ እስሮቹ ፡ ከኔ ፡ እጅ ፡ ሳይነሱ ፡ ሰደድኋቸው ፡ አልዋቸው ። አቶ ፡ ራሰምም ፡ አንተ ፡ አንደ ፡ ወደድህ ፡ ስደዳቸው ፡ እንጂ ፡ ከኔ ፡ ምን ፡ ጉዳይ ፡ አላቸው ፡ ብለው ፡ መንገድ ፡ መሪ ፡ ሰጥተው ፡ አልሰደድዋቸውም ፡ ብለው ፡ እንዳይናገሩ ፡ ፈሩና ፡ ሆዳቸው ፡ እያወቀ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ጃንሆየ ፡ ኃጢዓተኛ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አይገባውም ፡ ንጉሥን ፡ የበደለ ፡ ደግሞ ፡ እንዲያ ፡ ነው ፡ ብየ ፡ ደሞ ፡ ጃንሆየን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ከንግሥታችን ፡ ከገቡ ፡ ወድያ ፡ በፍርድ ፡ ቅጣት ፡ አይቀርላቸውምና ፡ ስለ ፡ ዚህ ፡ እኔ ፡ ሒዱ ፡ የንጉሥ ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ አይገባችሁም ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ንግሥታችን ፡ ፍቅር ፡ ምረዋችኋልና ፡ ሒዱ ፡ ብየ ፡ ሰደድኋቸው ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ ራሰም ።

አጤ ፡ ቴድሮስም ፡ እኔ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ አንቺ ፡ አህያ ፡ ኮርተሽ ፡ ያንቺ ፡ ሰዎች ፡ ከኔ ፡ እጅ ፡ እንዳይሱ ፡ ሰደድሁ ፡ ታልሽ ፡ ንሳ ፡ ያዛቸው ፡ አሉና ፡ ፫ቱ ፡ ተያዙ ፡ ራሰምና ፡ ጥሪደ ፡ ብላንክ ። በሰከ ፡ ወድያውም ፡ በደምብያ ፡ የተጓዘውን ፡ እስሮች ፡ ቶሎ ፡ መልሳቸው ፡ አሉና ፡ ጦር ፡ ወደ ፡ ደምብያ ፡ ሰደዱና ፡ አስመጥተው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ኮንሶል ፡ ኬምሮንና ፡ እስሮች ፡ በመቅደላ ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ በሰንሰለት ፡ ታሰሩ ፡ ራሰምና ፡ ሃኪሙ ፡ ጸሐፊውም ፡ በሰንሰለት ፡ ገብተው ፡ በዘበኛ ፡ ይጠበቁ ፡ ጀመሩ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሆነ ፡ በዘጌ ፡ ነው ፡ እነዝያ ፡ በታሰሩ ፡ ወይ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ ወይም ፡ ፲ቀን ፡ እንዳደረጉ ፡ በንጉሡ ፡ ሰፈር ፡ ፈንግል ፡ ኮለራ ፡ በ'ሽታ ፡ ገባ ፡ በዘጌ ፡ ንጉሡ ፡ ከዝያ ፡ ሸሽተው ፡ እስሮቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በቶሎ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ወጡ ፡ ሲጓዙም ፡ በፈንግሉ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ሞተ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ሃኪሙን ፡ አስፈትተው ፡ ወሰዱና ፡ ለታመሙቱ ፡ ብዙ ፡ አዳኑ ፡ ደግሞም ፡ ሁሉን ፡ ፈትተው ፡ በዘበኛ ፡ ይጠበቁ ፡ ነበር ፡ ሃኪሙም ፡ ላይነተኛ ፡ ሰው ፡ አልፎ ፡ ብዙ ፡ አዳነ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በ'ሽታው ፡ ለቀቀና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ራሰምና ፡ ሰዎቻቸው ፡ ኮንሶል ፡ ኬምሮንም ፡ ከቀድሞ ፡ አብረዋቸው ፡ ታስረው ፡ የነበሩ ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ አስረው ፡ ብዙ ፡ ነፍጠኛ ፡ ዘበ ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ሰደድዋቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በ፩አመት ፡ ወይስ ፡ ከዚያው ፡ የሚበልጥ ፡ አጤ ፡ ቴዎድ

ሮስ ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ቢክቶርያ ፡ መልክተኛ ፡ ሰዱዱ ፡ ማርቲን ፡ ፍላድ ፡
የሚባሉ ፡ ቃሉም ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ እኔ ፡ ሰዎችሽን ፡ ፈትቸ ፡ ልሰድ ፡ የለ
መንሁትን ፡ ልመናም ፡ ሰራተኞች ፡ በየአይነቱ ፡ ስራ ፡ የሚያውቁ ፡ ስደጅል
ኝ ፡ ብለው ፡ ላኩ ። ማርቲን ፡ ፍላድም ፡ እንደ ፡ ተላኩት ፡ ቃል ፡ ደብዳቤው
ን ፡ ወስደው ፡ ለእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሰጡ ፡

የእንግሊዝ ፡ ንግሥትም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ምላሽ ፡ መለሱ ፡ እሽ ፡ የሚ
ፈልጉትን ፡ ጉዳይ ፡ ኋላ ፡ ይሆናል ፡ አስቀድመው ፡ የኔን ፡ መልክተኞች ፡ በ
ግፍ ፡ ያሰርዋቸውን ፡ ፈትተው ፡ ምጥዋ ፡ ድረስ ፡ ይስደዱልኝ ። እነዝያ ፡ ም
ጥዋ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ እኔም ፡ ያሉኝን ፡ ነገር ፡ እሰዳለሁ ። ይህነን ፡ ያላደረጉ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ወደርሶ ፡ ጦር ፡ መስደዴን ፡ ይወቁት ፡ ብለው ፡ በማ
ርቲን ፡ ፍላድ ፡ እጅ ፡ ደብዳቤ ፡ ሰደዱ ።

አጤ ፡ ቴድሮስም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተሰሙ ፡ በኋላ ፡ ፈከሩ ። ነገር ፡ ግን ፡
በሆዳቸውም ፡ ፍርሃት ፡ ገባ ። ብስጭትም ፡ አበዙ ፡ ከነጮች ፡ ሰራተኞችም ፡
ጋራ ፡ መጣላት ፡ ጀመሩ ። ጋፋት ፡ የምትባል ፡ ከተማ ፡ የፈረንጆች ፡ ነበረች ፡
እሷን ፡ ለቃችሁ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ውጡ ፡ አልዋቸው ፡ ጋፋትና ፡ ደብ
ረ ፡ ታቦር ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ያንድ ፡ ሰዓት ፡ መንገድ ፡ አይሆንም ። ሁሉ ፡ አን
ድ ፡ አገር ፡ ነው ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ፈረንጆች ፡ ጋፋትን ፡ ሊለቁ ፡ አልወደዱም ፡
መልካካም ፡ ቤት ፡ ባለ ፡ ደርብ ፡ መስኮቱ ፡ መዝጊያው ፡ ባለ ፡ መስዋት ፡ የሆ
ነ ፡ ሠርተውባት ፡ ነበር ።

ደግሞ ፡ ጋፋት ፡ ማለፍያ ፡ ከተማ ፡ ሁና ፡ ነበር ፡ በዙርያዋ ፡ ሁሉ ፡ ፈሳ
ሽ ፡ ወንዝ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ውስጥም ፡ ውሃ ፡ ይገባ ፡ ነበር ፡ ጠንካራ ፡ ቅጥርም ፡
ነበራት ፡ እንደ ፡ ምሽግ ፡ መተኳኰሻ ፡ መስኰት ፡ ነበረ ፡ የመድፍም ፡ የጠበ
ንጃም ፡ መተኰሻ ፡ ፩መድፎች ፡ በ፩መስኰት ፡ ተዘግበ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፡ ስ
ለ ፡ ዚህ ፡ ንጉሡ ፡ ነጮች ፡ በጋፋት ፡ ሊቀመጡ ፡ አልወደዱም ፡ ሽዋ ፡ ሳሉ ፡
ንጉሥ ፡ ነው ፡ ይህው ፡ ምሽግ ፡ የተደረገ ፡ እና ፡ ወይ ፡ አንድ ፡ ሽፍታ ፡ ወይ
ም ፡ ከሚከዱ ፡ መኳንንቶቻቸው ፡ ተዝያው ፡ ገብተው ፡ ያስቸግሩኛል ፡ ብለ
ው ፡ ተጠራጥረው ፡ ነበር ፡ ሰውም ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ክዳት ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ፡
ስለ ፡ ዚህ ፡ ፈረንጆችን ፡ ልቀቁ ፡ በቶሎ ፡ አልዋቸው ። የፈረንጆችም ፡ እሽ ፡
እያሉ ፡ ጓዛችን ፡ መስርያ ፡ እቃችን ፡ እንሰበስባለን ፡ እያሉ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡
ሰነበቱ ፡ ተዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ በቁጣ ፡ ከሰፈራቸው ፡ ተነስተው ፡ ወደ ፡ ጋ
ፋት ፡ ወረዱና ፡ እርሳቸው ፡ ከውሃው ፡ መዘወር ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ ንሳ ፡
ያዛቸው ፡ ብለው ፡ ፈረንጆችን ፡ አስያዙዋቸው ፡ ቤታቸውም ፡ ሁሉ ፡ የነፍጠ



ኛ ፡ ዘበኛ ፡ ከበ ፡ ያዘው ፡ የፈረንጆች ፡ ገረዱ ፡ ሎሌው ፡ ሁሉ ፡ እንዳይወጣ ፡
ተጠበቀ ፡ በጋፋት ፡ ብዙ ፡ ደስታና ፡ ጥጋብ ፡ የነበረባት ፡ ልቅሶና ፡ ዋይታ ፡
ሁኖ ፡ አደረ ፡ ንጉሡ ፡ ፈንጆችን ፡ አስይዘው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ወጥተ
ው ፡ አደሩ ፡ አንድ ፡ የማርቲን ፡ ፍላድ ፡ አሽከር ፡ የተማረ ፡ የደምብያ ፡ ሰው ፡
ከመንገድ ፡ አግኝተውት ፡ ቆራርጠው ፡ ጣሉት ። የፈረንጆች ፡ ምሽቶች ፡ ሁ
ሉ ፡ ጋፋት ፡ ከቤታቸው ፡ በዘበኛ ፡ ተከበው ፡ እያለቀሱ ፡ ተጨንቀው ፡ አደ
ሩ ። በነጌታው ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ድልድይ ፡ ታሰሩት ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተቀምጠው ፡ ፈረንጆችን ፡ ተታሰሩቱ ፡ ስፍራ ፡ አስጠር
ተው ፡ እኔ ፡ ልጆቸን ፡ ወዳጆቸን ፡ አልጠላኋችሁም ፡ ጋፋትን ፡ አንለቅም ፡
ብትሉኝ ፡ ነው ፡ አሁንም ፡ ምሬአችሁ ፡ አለሁ ፡ የዛሬን ፡ ቀን ፡ ጋፋትን ፡ ልቀ
ቁ ፡ ብለው ፡ ፈትተው ። ከደብረ ፡ ታቦር ፡ ወደ ፡ ጋፋት ፡ ንጉሡና ፡ ፈረንጆ
ች ፡ ወርደው ፡ ምሽቶቻቸው ፡ እቃቸው ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ገቡ ።

## የጋፋት ፡ እልፈት ።

ይህን ፡ ታደረጉ ፡ በኋላ ፡ የውሃ ፡ መዘወሩን ፡ አፍርሱት ፡ ብለው ፡ ንጉ
ሡ ፡ አዘዙና ፡ አፈረሱት ፡ የውሃው ፡ መዘወር ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ስራ ፡ ይሰራ
በት ፡ ነበር ፡ እየዞረ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በመጋዝ ፡ ግንድ ፡ ይሰነጥቃል ። ባንድ ፡
ወገን ፡ ባሩድ ፡ ይወቅጣል ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ባሩዱን ፡ ያንኰረኵራል ፡ ባ
ንድ ፡ ወገን ፡ ወናፍ ፡ ያናፋል ። ደሞ ፡ ማንጠሚ ፡ የመድፍም ፡ የእንጨት
ም ፡ ባለ ፡ ቤቱ ፡ ያነጣል ፡ ያረብያ ፡ በማኸሉ ፡ የሚሆን ፡ ይነጠጥበታል ።
ይህን ፡ ብንቅርቅር ፡ አርገው ፡ ታፈረሱ ፡ ወድያ ። ፪ሐጎዶ ፡ መድፍና ፡
ቦምባ ፡ ይፈስበት ፡ የነበረው ፡ አፈረሱና ፡ ቀጥለው ፡ ቤቱንም ፡ ሁሉ ፡
አፈራረሱና ፡ እቃውም ፡ እንጨቱም ፡ አስይዘው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡
ሔዱ ። ስለ ፡ ጋፋት ፡ አስቀድሞ ፡ አዝማሪ ፡ ገጥሞ ፡ ነበር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
እዱኛ ፡ ዘመመች ፡ ወረደች ፡ ወደ ፡ ጋፋት ። እንዳትዘነብልም ፡ እንደግ
ፋት ። እንደ ፡ በሉ ፡ መቅረት ፡ የለም ፡ አለ ፡ መትፋት ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ጋፋ
ትን ፡ ለቀቁና ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ሰፈር ፡ አደረጉ ፡
ፈረንጆችም ፡ ከመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥግ ፡ የግድግዳ ፡ ቤ
ቶች ፡ ሰሩ ፡ የንጉሡም ፡ በግድግዳ ፡ ብዙ ፡ አደራሽ ፡ ተሰራ ። ደግሞ ፡ ለ
ፈረንጆች ፡ ከዝያው ፡ ላይ ፡ አጎዶ ፡ ስሩ ፡ መድፍ ፡ ስሩ ፡ አልዋቸው ፡ ጋፋት ፡
አፍርሰው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ በንጉሡ ፡ የብስጭት ፡ መንፈስ ፡

አደረበዎ ፡ ሰውም ፡ ይከዳ ፡ ጀመረ ፡ ወታርም ፡ መኳንንትም ፡ ባለ ፡ ገርም ፡
አልታዘዝም ፡ አለ ፡ የቤጌምድር ፡ ባላገር ፡ ሁሉ ፡ ወያኔ ፡ ሽፍታ ፡ ሆነ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሜዳው ፡ ሁሉ ፡ ፩ታላቅ ፡ አጥር ፡ አደ
ረጉ ፡ እንደ ፡ ምሽግ ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ የሚከት ፡ መድፉም ፡ ከመድኃኔ ፡ ዓ
ለም ፡ ከድልድዩ ፡ አሰለፉትና ፡ እርሳቸው ፡ ወደ ፡ ወራሪ ፡ ይሔዱ ጀመረ ፡ ከ
ዝያ ፡ ከፊታቸው ፡ የተገኘውን ፡ ሁሉ ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉት ፡ ጀመሩ ፡ ከዝያ ፡
ወድያ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋር ፡ የሐደው ፡ ሰው ፡ ወራሪ ፡ ኑረው ፡ ሲመለሱ ፡ በዋ
ለው ፡ ይከዳ ፡ ጀመር ፡ ባላገሩም ፡ በየዱሩ ፡ በየበረሀው ፡ እየሆነ ፡ ይዋጋም ፡
ይሳደብም ፡ ገባ ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ያገኙትን ፡ ሰው ፡ በጠበንጃም ፡ በእሳትም ፡
ይፈጁት ፡ ጀመሩ ፡ የጐንደር ፡ ፵፬ቤተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አቃጠሉት ፡ ሰው ፡
ሁሉም ፡ ተማረከ ፡ አገሩም ፡ ሁሉ ፡ ዘረፉት ፡ በእሳትም ፡ አቃጠሉት ። የዳ
ራ ፡ የፎገራ ፡ የደምቢያም ፡ ላም ፡ ዘረፉት ፡ ለዘር ፡ ሳይቀር ፡ የደከመውን ፡ በ
መንገድ ፡ እየደበደቡ ፡ ወደ ፡ አጥሩ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ አገቡት ፡ ከሜዳው ፡ ላ
ይ ፡ ሁነው ፡ ለሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አቅሙ ፡ እንደ ፡ ብዛቱ ፡ አካፈሉት ።
እንዴህም ፡ አሉት ፡ የምትበላውን ፡ ያቅመህን ፡ ብላ ፡ ቋንጣም ፡ ዘልዝለ
ህ ፡ አድርቅ ፡ የተረፈው ፡ ላም ፡ ግን ፡ እያረድህ ፡ መሬት ፡ ቆፍረህ ፡ ቅበረ
ው ፡ ብለው ፡ አስለፈፉ ፡ ቁርጥ ፡ ቀንም ፡ አደረጉለት ፡ በዝያችው ፡ በሰጠሁ
ህ ፡ ቀን ፡ ከሰፈሩ ፡ ላም ፡ ቁማ ፡ ያየሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብርቱ ፡ ቅጣት ፡ አለብ
ህ ፡ አሉትና ። ወታደሩም ፡ የበላው ፡ በልቶ ፡ ቋንጣውም ፡ ዘልዝሎ ፡ የተረ
ፈው ፡ ላምና ፡ በሬ ፡ እያረደ ፡ ቀበረው ፡ ወታደሩ ፡ ሣር ፡ ለማጨድ ፡ ባልሆነ
ለት ፡ ጊዜ ፡ ጎጆው ፡ ሁሉ ፡ ቆርበት ፡ ብቻ ፡ አልብሶት ፡ ከረመ ።

የወታደሩ ፡ ሁሉም ፡ ምግቡ ፡ ቋንጣ ፡ ነበረ ፡ ከመስከረም ፡ ወድያ ፡ ግን ፡
የገብስ ፡ ዋሸቃ ፡ ከባለገር ፡ ጋር ፡ እየተዋጋ ፡ እየዘረፈ ፡ መብላት ፡ ጀመረ ።
በዝያው ፡ ክረምት ፡ ባንድ ፡ ብር ፡ አንድ ፡ ቁና ፡ እህል ፡ በ፩ብር ፡ ይሸመት ፡
ነበር ። አንድ ፡ ብር ፡ ላንድ ፡ አሞሌ ፡ ተለወጠ ፡ ያውም ፡ ባላገሩ ፡ እየተሰረ
ቀ ፡ በየዘመዱ ፡ ነው ፡ የሚገኝ ፡ የነበረ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ ለፈረንጆች ፡ ለስራ
ተኞች ፡ እያካፈሉ ፡ ለተራበው ፡ መኳንንትም ፡ ግብር ፡ ሲያበሉ ፡ ከረሙ ፡ ዳ
ሩ ፡ ሰው ፡ በእሳት ፡ ሲቃጠል ፡ በጠበንጃም ፡ ሲደበደብ ፡ እያየ ፡ ሁሉ ፡ በየጎ
ጆው ፡ በየድንኳኑ ፡ ሲያለቅስ ፡ ከረመ ። አንድ ፡ አንድ ፡ ክፎች ፡ ደግሞ ፡ እ
ገሌ ፡ ሊከዳ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ሲከዳም ፡ ያገኘው ፡ እየያዘ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይጣ
ፉ ፡ ነበረ ።

የምጽርሐ ፡ የደሴቱ ፡ ጥፋት ። አንድ ፡ ቀን ፡ አጤ ፡ ቴዎድድሮስ ፡ ወደ ፡



ባሕሩ ፡ ዳር ፡ ስለ ፡ መዝረፍ ፡ ሔዱ ፡ ሲዘርፉ ፡ ውለው ፡ ከምጽርሃ ፡ ደምበ
ር ፡ ሰፈሩና ፡ ወደ ፡ ምጽርሐ ፡ ባታንኳ ፡ ፩ሰው ፡ ሰደው ፡ ቶሎ ፡ ግቡ ፡ ናችሁ ፡ ብ
ለህ ፡ ንገራቸው ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ ከዝያው ፡ ውስጥ ፡ የጐንደር ፡ ሃብታሞችም
ነጋዶች ፡ እነ ፡ ጥርሶ ፡ ኃይሉ ፡ እነ ፡ ልጅ ፡ ብርየ ፡ እነ ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጎበዜ ፡
ከበርቶች ፡ ናቸው ፡ ከዝያው ፡ ውስጥ ፡ ሁነው ፡ ከባላገሮቹና ፡ ከመነኮሳቱ ፡
ጋር ፡ ፩ሁነው ፡ አንመጣም ፡ ብለው ፡ ላኩ ፡ በምጽርሃ ፡ ያለ ፡ ታንኳ ፡ ሁሉ
ም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ አገቡት ፡ አጤ ፡ እንዳያገኙት ፡ ብለው ፡ ንጉሡም ፡ በዋ
ና ፡ እንዳይሻገሩት ፡ የማይሆን ፡ ሆነና ፡ እየተናደዱ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡
ተመለሱ ፡ ከቤታቸው ፡ ገብተው ፡ ፈረንጆች ፡ ጥራ ፡ አሉ ፡ አቶ ፡ ዋልድ ፡ ማ
የር ፡ የእንጨት ፡ ሰራተኛ ፡ ሳልሚለር ፡ የብረት ፡ ናቸውና ፡ መጡ ፡ የምጽር
ሐ ፡ ሰዎች ፡ ያረግዋቸው ፡ ነገር ፡ ነገርዋቸው ፡ እነዝያም ፡ ይህ ፡ አይሸግረነም ፡
አሉ ፡ ንጉሥም ፡ በንዴት ፡ ሳይተኙ ፡ አደሩና ፡ በነጋታው ፡ ፈረንጆች ፡ ሰራ
ተኞች ፡ የሐበሻ ፡ ሰራተኞችም ፡ ይዘው ፡ ሂደው ፡ ከምጽርሐ ፡ የባሕር ፡ ዳር ፡
ሰፍረው ፡ በየአገሩ ፡ ሸምቆ ፡ አሰበሰቡ ፡ ሰራተኞችም ፡ እንጨት ፡ በመጋዝ ፡ እ
የሰነጠቁ ፡ እንደ ፡ ሳንቃ ፡ አርገው ፡ ብዙ ፡ ወታደር ፡ የሚይዝ ፡ ሰሩና ፡ በዝ
ያ ፡ እየሆነ ፡ ነፍጠኛ ፡ ወደ ፡ ምጥርሃ ፡ ገባ ፡ ንጉሡ ፡ ከዳር ፡ ሁነው ፡ በመድ
ፍ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አፈረሱት ፡ ነፍጠኛውም ፡ ገብቶ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ማ
ረከው ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ጎበዜ ፡ በታንኳ ፡ ሁኖ ፡ አመለጠ ፡ ጥርሶ ፡ ኃይሉና ፡
ልጅ ፡ ብርየ ፡ ተያዙ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ በታንኳ ፡ ተሻግረው ፡ የምጥርሃ ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉት ፡ ከዝያውም ፡ ብዙ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ተገኘ ፡ ጥር
ሶ ፡ ኃይሉና ፡ ልጅ ፡ ብርየ ፡ ግን ፡ ታስረው ፡ በጭራ ፡ ገመድ ፡ ብር ፡ ይከፍ
ሉ ፡ ነበር ፡ ልጅ ፡ ብርየ ፡ በእስራቱ ፡ በቶሎ ፡ ሞተ ፡ ተስፋ ፡ ኃይሉ ፡ ግን ፡
በእንግሊዞች ፡ ወጥተው ፡ ጐንደር ፡ ገብተው ፡ ጌታ ፡ ሁነው ፡ ነበር ። ፊት ፡ ሌ
ት ፡ ከውርጭ ፡ ቀን ፡ ከፀሐይ ፡ በጭራ ፡ ታስረው ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ አገኙ ፡
በዝያው ፡ ጊዜ ፡ የዋድላ ፡ የደላንታ ፡ ወታደሮች ፡ ባንድ ፡ ወገንም ፡ የሜጫ
ና ፡ የዳሞት ፡ ወታደሮች ፡ ከነአለቃቸው ፡ ሊከዱ ፡ ተማምለው ፡ ታበቁ ፡ ወ
ድያ ፡ በመንገድ ፡ ከደረሱ ፡ እኩሌቶች ፡ ወይ ፡ የሚበዙ ፡ ተመልሰው ፡ ለ
ንጉሥ ፡ ተናገሩ ፡ ንጉሡም ፡ በቶሎ ፡ እነዝያን ፡ ዋሾች ፡ መሪ ፡ አርገው ፡ ብ
ዙ ፡ ጦር ፡ ሰደዱና ፡ ተይዘው ፡ መጡ ፡ በመንቆር ፡ አግቡዋቸው ፡ ብለው ፡
በመንቆር ፡ አንገታቸው ፡ በርጥብ ፡ ቆርበት ፡ ታሰሩ ፡ እግርና ፡ እጃቸውም ፡
በሰንሰለት ፡ ታሰሩና ፡ ቀን ፡ ተጣይ ፡ ሌት ፡ ተውርጭ ፡ እራቁታቸውን ፡ እህ
ልና ፡ ውሃ ፡ እንዳይቀምሱም ፡ በዘበኛ ፡ አስጠበቁና ፡ አኖሯቸው ። ከዝያ ፡

ወድያ ፡ ውሃ ፡ ሲጠማቸው ፡ ጊዜ ፡ ሽንታቸው ፡ ይጠጡ ፡ ነበር ፡ ይህነን ፡ ጠባቆቹ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከነሽንታቸው ፡ ከለከልዋቸው ፡ ደግሞ ፡ ዝናብ ፡ ሲዘብ ፡ በግድግዳው ፡ እጃቸው ፡ ወደ ፡ ጠፈጠፉ ፡ ቢያዘልቁ ፡ ጠባቆቹ ፡ እጃቸውን ፡ እየመቱ ፡ ከለከልዋቸው ። ከዚህ ፡ ጭንቅ ፡ የተነሳ ፡ እኩሎቹ ፡ በቶሎ ፡ ሞቱ ፡ እኩሎቶቹ ፡ ጸሎት ፡ እያደረጉ ፡ አይናቸው ፡ ቅጠልያ ፡ መልካቸውም ፡ ብጫ ፡ መስሎ ፡ ብቻ ፡ ጅማትና ፡ አጥንት ፡ ቀርተው ፡ ላይን ፡ ያስፈሩ ፡ ነበር ፡ እንዲያ ፡ ሁነው ፡ ሁሉ ፡ ሞቱና ፡ ከነመንቈራቸውና ፡ ተነሰንሰለታቸው ፡ በረሀ ፡ ወደቁ ።

በዝያው ፡ ጊዜ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ስሜን ፡ ሞቱና ፡ ሞታቸው ፡ ግን ፡ በበሽታ ፡ ነው ፡ ንጉሡም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይቅበር ፡ አስለቃሽም ፡ ታልቅስ ፡ አሉ ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ የነዝያ ፡ በውሃና ፡ በራብ ፡ በመንቆር ፡ የሞቱቱ ፡ እህት ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ አለቀሰች ። አውይ ፡ የኔታ ፡ ደጃች ፡ ውቤ ፡ ዘወትር ፡ ደግነት ። ዛሬ ፡ እንኳ ፡ ለድሀም ፡ እንባ ፡ አተረፉለት ። አለችና ፡ መልሳም ፡ አለቁ ፡ ይሉኛል ፡ ይለቅ ፡ አባታቸው ፡ እኔም ፡ አልናገር ፡ እኒያም ፡ ስም ፡ የላቸው ። አለች ፡ እገሌ ፡ እገሌ ፡ እንዳትል ፡ ቅጣት ፡ ስለ ፡ ፈራች ፡ የሚደበደብ ፡ ሰው ፡ አይቶ ፡ እኔን ፡ አዎይ ፡ ብሎ ፡ ያዘነ ፡ ይቀጣ ፡ ነበር ፡ እንኳን ፡ ልቅሶ ። ደግሞ ፡ የጐንደር ፡ አልቃሽ ፡ እንዲህ ፡ አለች ። ጐንደር ፡ ተተኰሶ ፡ ነበርና ፡ አርባ ፡ አራቱ ፡ ደብር ፡ ተጨንቆ ፡ ሲሸበር ፡ ምንኛ ፡ ጠገበ ፡ ተተኰሰ ፡ ጐንደር ፡ አለች ፡ መልሳም ፡ በልጅነታቸው ፡ እህል ፡ ያልቀመሱ ፡ ምንኛ ፡ ጠገቡ ፡ አበ ፡ ተተኮሱ ፡ አለች ፡ ጐንደርን ፡ እሳት ፡ በመተኮሱ ፡ የጥጋብ ፡ ትኩሳት ፡ አስመሰለች ።

አቦም ፡ በልጅነታቸው ፡ የናታቸው ፡ ጡት ፡ ሳይጠቡ ፡ እህል ፡ ሳይቀምሱ ፡ አደጉ ፡ ይባላልና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ በእሳት ፡ መቃጠሉ ፡ የጥጋብ ፡ አስመሰለች ።

ክረምቱ ፡ ሁሉ ፡ ወታደሩ ፡ በመከራ ፡ ከረመ ፡ የሚቃጠልም ፡ ሲያቃጥሉ ፡ የሚደበደብም ፡ ሲደበደብ ፡ ከረመ ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ውሾች ፡ ሰው ፡ አላሳልፍም ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ ፡ የዱር ፡ አውሬ ፡ ሁነው ፡ ነበር ፡ የሰው ፡ ሥጋና ፡ የከብት ፡ ሥጋ ፡ ለምደው ።

ንጉሡም ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ መስቀልን ፡ ውለው ፡ መስከረም ፡ ጨርሰው ፡ በጥቅምት ፡ መባቻ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ተነሱ ፡ መድፋቸውና ፡ ጉዞአቸው ፡ ይዘው ፡ መንገድም ፡ እየተደለደለ ፡ አቀበቱም ፡ ቁልቁለቱም ፡ እያደላደሉ ፡ እየጠረጉ ፡ መድፉን ፡ በሰው ፡ እያስጐተቱ ፡ ከአንድ ፡ ሰፈር ፡ ፩ወር ፡ ፪ወር ፡



፪ሳምንት ፡ ፩ሳምንት ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ስራ ፡ መመቸት ፡ ደንጊያውን ፡ በባሩድ ፡ በድጅኖም ፡ እየሰበሩ ፡ የጅጣና ፡ የበሽሎ ፡ ቁልቁለት ፡ በብዙ ፡ ቀን ፡ ደለደሉትና ፡ በሚያዝያ ፡ ወራት ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ገቡ ። እንደ ፡ ገቡ ፡ በስተ ፡ ወድያው ፡ ለጦርነት ፡ ያሰናዱ ፡ ነበር ፡ የመቅደላ ፡ አምባ ፡ መውጫውና ፡ መግብያው ፡ እያሰናዱ ፡ ሳሉ ፡ በስከወድያው ፡ እንግሊዞች ፡ ወደ ፡ ደላንታ ፡ መጥተው ፡ ሰፈሩ ። ንጉሡም ፡ በየበሩ ፡ ሁሉ ፡ መድፍና ፡ ዘበኛ ፡ አደረጉለት ፡ እንግሊዞችም ፡ በቶሎ ፡ የበሽሎን ፡ ቁልቁለት ፡ ንጉሡ ፡ በደለደሉት ፡ መንገድ ፡ መጓዝ ፡ ሲጀምር ፡ በመነጠር ፡ አሻግረው ፡ አዩትና ፡ ለመኳንንት ፡ ሁሉ ፡ መነጠር ፡ እንዳያይ ፡ ከለከሉትና ። ማክሰኞ ፡ እለት ፡ በመቅደላ ፡ የነበረውን ፡ እስር ፡ ሁሉ ፡ ከአምባው ፡ አውርደው ፡ ወደ ፡ ሰላምጌ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሰፈር ፡ አመጡት ፡ ነጭ ፡ የሆነ ፡ እስር ፡ ካምባው ፡ ሲቀር ፡ የሐበሻ ፡ ሰው ፡ እስር ፡ የሆነ ፡ ከአምባው ፡ አልቀረም ። መቸም ፡ እስሩ ፡ እኩሉ ፡ ሊደበድቡነን ፡ ይሆን ፡ ይላል ፡ ደግሞም ፡ ይፈቱነን ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ አደረ ፡ ሮብም ፡ ዋለና ፡ ሮብ ፡ ማታ ፡ ላሙስ ፡ አጥብያ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እስሮች ፡ ምሕረት ፡ አገኘነ ፡ መስሎአቸው ፡ እግዚኦ ፡ እንበል ፡ ብለው ፡ መከሩና ፡ እግዚኦ ፡ አሉ ፡ እስሩ ፡ ሁሉም ፡ ተቀበለና ፡ እግዚኦ ፡ እያለ ፡ ሰፈሩን ፡ ሁሉ ፡ አደነቈረው ። ንጉሡም ፡ በቶሎ ፡ ዘበኛ ፡ ሰዱዱና ፡ ምን ፡ ሁነሀል ፡ ብለው ፡ አስጠየቁ ፡ ዘበኞቹም ፡ እስሮች ፡ ናቸው ፡ ከጃንሆይ ፡ ምሕረት ፡ ብናገኝ ፡ እግዚኦ ፡ እንላለን ፡ አሉ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ፡ በል ፡ ዝም ፡ ብላችሁ ፡ እደሩ ፡ በላቸው ፡ ብለው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ አደሩ ። አሙስ ፡ በማለዳ ፡ ቶሎ ፡ ስጮሁ ፡ ያደሩትን ፡ እስሮች ፡ አምጣ ፡ ብለው ፡ አዘዙና ፡ እስሮችም ፡ ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ በንጉሥ ፡ ፊት ፡ መጥተው ፡ ቆሙ ። ንጉሡም ፡ ምን ፡ ሁናችሁ ፡ ነው ፡ የጮኋችሁ ፡ ብለው ፡ ጠየቁዋቸው ፡ እስሮችም ፡ ጃንሆይ ፡ ይምሩን ፡ ብለን ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ንጉሡም ፡ የእንግሊዞች ፡ ጠላት ፡ መጥቶበታልና ፡ ፈርቶ ፡ ይፈታናል ፡ ብለሽ ፡ ነው ። እኔ ፡ አንድ ፡ የናቱ ፡ እኔ ፡ የመይሳ ፡ ልጅ ፡ አልተውሽ ፡ አልምርሽም ፡ ጠላቴን ፡ በፊቴ ፡ ነው ፡ የማረግሽ ፡ አሉና ። በስከ ፡ ወድያ ፡ የእስሮች ፡ ደብዳቤ ፡ አምጣ ፡ አሉና ፡ ደብዳቤው ፡ እየተነበበ ፡ በብዙ ፡ የበደላቸውን ፡ በደሉን ፡ ወቅሰው ፡ ወደ ፡ ግራ ። እጅግ ፡ በደል ፡ ያልነበረውም ። ነገሩን ፡ ተናግረው ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አቆሙትና ።

በዝያው ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ አርአያ ፡ የአጤ ፡ ዮሐንስ ፡ አጎት ፡ እስር ፡ ነበሩና ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራና ፡ ከልጃቸው ፡ ጋራ ፡ ከእስሮች ፡ ጋር ፡ ቁመው ፡ ሳሉ ፡ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገርዋቸ ፡ ደጃች ፡ አርአያ ፡ አንተ ፡

የበደልኸኝ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ መልካም ፡ ጎበዝ ፡ ተዋጊ ፡ ነህና ፡ እንዳትሸፍት ፡
ብጠረጥርህ ፡ ነው ፡ ያሰርሁህ ፡ አሉና ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ አሳልፋቸው ፡ ብለው ፡
ወደ ፡ ቀኝ ፡ አቆሙዋቸውና ፡ እንዲህም ፡ አልዋቸው ፡ ዛሬ ፡ እንዳልፈታህ ፡
ፈርቶ ፡ ፈታኝ ፡ ልትለኝ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ታሰርህ ፡ ቆይ ፡ አልዋቸው ፡ ደጃች ፡
አርአያም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ጃንሆየ ፡ የዛሬን ፡ ጦርነት ፡ አብሬዎ ፡ ልዋልና ፡
ተመልሸ ፡ ልታሰር ፡ ልጀና ፡ ወንድሞቹ ፡ መያዥ ፡ ይሁኑና ፡ ወንድነቴን ፡ ላ
ሰየዎ ፡ አሉ ፡ ንጉሡም ፡ መልካም ፡ ጅግና ፡ መሆንህ ፡ አውቃለሁና ፡ ዝም ፡
ብለህ ፡ ተቀመጥ ፡ አልዋቸው ፡

በግራ ፡ የቆመውን ፡ ሁሉ ፡ በጠበንጃ ፡ እየገደሉ ፡ ወደ ፡ ገደል ፡ ሰደዱ
ት ፡ ገደሉ ፡ ረጅም ፡ ነበረና ፡ ሰው ፡ ሞላ ።

የሕማማት ፡ ጸሎተ ፡ ሐሙስ ፡ ነበረ ። በቀኝ ፡ ያቆሙት ፡ ግን ፡ አልተ
ደበደም ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ ቆየና ፡ እንግሊዞች ፡ ፈቱት ።

አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ሰውን ፡ ደብድበው ፡ ታበቁ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጡ ፡
መነጠር ፡ ለማየት ፡ ከራስ ፡ እንግዱና ፡ ከፊተውራሪ ፡ ገብርየ ፡ ጋራ ፡ የእንግ
ሊዝ ፡ ወታደርም ፡ የበሽሎ ፡ ቁልቁት ፡ ሲወርድ ፡ አዩትና ፡ ተመልሰው ፡ ወ
ረዱ ፡ ደግሞ ፡ ሰላይ ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሰላ
ዮች ፡ ፳ፈረሰኞች ፡ መጥተው ፡ ወርቄ ፡ ውሃ ፡ ላይ ፡ ከጥላ ፡ እግር ፡ ተቀምጠ
ው ፡ ከዝያው ፡ ሁነው ፡ ምሳ ፡ በልተው ፡ አረቂ ፡ ሲጠጡ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ነገ
ራቸው ፡ ንጉሡም ፡ ለዘበኞች ፡ ተቆጡ ፡ ምነው ፡ ያልጠበቃችሁ ፡ ብለው ፡
መጥተው ፡ የነበሩ ፡ የእንግሊዝ ፡ ፈረሰኞች ፡ ግን ፡ ፩ታላቅ ፡ ሰው ፡ ነበራቸ
ው ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ መሪ ፡ ወደር ፡ የተባለ ፡ ፊተውራሪ ፡ ነበረ ።

በነገታው ፡ ዓርብ ፡ የስቅለት ፡ እለት ፡ በእኩል ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በ፯ሰዓት ፡
የበሽሎን ፡ አቀበት ፡ ጨርሶ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ ወደ ፡ ወርቄ ፡ ውሃ ፡ ሜ
ዳ ፡ በርበሬ ፡ መስሎ ፡ ልብሱ ፡ ቀይ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ የለበሰ ፡ በሜዳ
ው ፡ ብቅ ፡ አለ ፡ ቀጥሎም ፡ ጓዙና ፡ ጭነቱ ፡ ዝሆኖችም ፡ እንደ ፡ ተጫኑ ፡ ዘ
ለቁና ፡ ሊሰፍር ፡ ማራገፍ ፡ ሲጀምር ፡ ንጉሡ ፡ በመነጠር ፡ አይተው ፡ አያሳድ
ረኝ ፡ እንዳላሳድረው ፡ ብለው ፡ ፈከሩና ፡ የጦር ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ በየ
ሰልፍህ ፡ ተሰልፈህ ፡ ተቀመጥ ፡ ብለው ፡ አሰለፉትና ። በስከ ፡ ወድያው ፡ ገብ
ርየን ፡ ጥራ ፡ አሉ ፡ ፊተውራሪ ፡ ገብርየም ፡ የአምበሳ ፡ ለምድ ፡ በወርቅ ፡ የ
ተቃጠለ ፡ ለብሰው ፡ ባለጫሚ ፡ ሾተል ፡ ታጥቀው ፡ የተንቆጠቆጠ ፡ ወርቅ ፡
ጋሻ ፡ እና ፡ ፪አፍጨ ፡ ጦር ፡ አንዱን ፡ ነጥለው ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ እየሰበቁ ፡
አንዱ ፡ ጦርም ፡ በግራ ፡ እዳቸው ፡ ከእዛብ ፡ ጋር ፡ ከፈረሱ ፡ ጋማ ፡ ላይ ፡ ይዘ



ው ፡ በጠገበ ፡ ሰንጋ ፡ ሁነው ፡ ገብሬ ፡ የፈሪ ፡ ጅራት ፡ እያሉ ፡ እየተንደቀደ
ቁ ፡ የዋሉበትም ፡ የገደሉትም ፡ ፈክረው ፡ ታበቁ ፡ ወድያ ። ንጉሡ ፡ ጦሩን ፡
ይዘህ ፡ ወርደህ ፡ ግጠም ፡ አልዋቸው ፡ እርሳቸውም ፡ እሽ ፡ ብለው ፡ በተጠ
ረገው ፡ ጐዳና ፡ ወርደው ፡ ገጠሙ ፡ ንጉሥም ፡ ሠራዊቱን ፡ ከገብርየ ፡ ጋር ፡
ሔድ ፡ ብለው ፡ አዘው ። ዘበኞዎና ፡ ጋሻ ፡ ዢግሮች ፡ መድፍ ፡ ተኳሾች ፡ ይ
ዘው ፡ ከፍ ፡ ታለ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ መነጠር ፡ እያዩ ፡ መድፍ ፡ ተኳሾች
ን ፡ ቶሎ ፡ ቶሎ ፡ ተኰሱ ፡ እያሉ ፡ ይተኰሱ ፡ ጀመሩ ፡ መድፍ ፡ የሚተኩሱ ፡
ፈረንጆች ፡ ነበሩና ፡ ተውት ፡ የአገሬ ፡ ሰው ፡ ይተኰሰው ፡ ብለው ፡ ፈረንጆች
ን ፡ አስትተው ፡ የሐበሻ ፡ ወታደሮች ፡ ይተኩሱ ፡ ገቡ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ፈረ
ንጆቹ ፡ ሽቅብ ፡ ነው ፡ የሚሰዱት ፡ ያለ ፡ ብሎ ፡ ነግሮአቸው ፡ ነበርና ፡ እነዝያ ፡
የንጉሥ ፡ ወታደሮች ፡ ሲተኩሱ ፡ አንዱን ፡ መድፍ ፡ ተሳስተው ፡ ሁለተ ፡ ጊ
ዜ ፡ ለጐሙትና ፡ ተሰነጠቀ ፤ ፊተውራሪ ፡ ገብርየም ፡ ማኸል ፡ ለማኸል ፡ ፊ
ታቸውን ፡ ሳያዞሩ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ገጥመው ፡ በስከወድያው ፡ ሞቱ ፡ ከርሳቸ
ው ፡ ጋር ፡ የሔደ ፡ ወታደርም ፡ የሚሞትም ፡ ከዝያው ፡ ሞተ ፡ የሚሸሽም ፡
ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ተመለሰ ። ንጉሡም ፡ ሠራዊተዎ ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ሆ
ነ ፡ በመነጠር ፡ አሻግረው ፡ ያዩ ፡ ነበር ፡ እየዘቀዘቁ ፡ መድፍ ፡ ይተኰሱ ፡ ነበ
ር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የእንግሊዝ ፡ መድፍ ፡ ተኳሾች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አስተ
ያይተው ፡ ራኬት ፡ የሚባል ፡ እንደ ፡ አሞራ ፡ የእሳት ፡ ጅራት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡
ሁሉ ፡ እያየው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አነጣጥሮ ፡ ለቀቀውና ፡ ከንጉሡ ፡ አጠገብ ፡
ድንኳን ፡ ነበረና ፡ ድንኳኑን ፡ ቀዶ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ገደለና ፡ ከመሬት ፡ ገባ ፡
መልሶም ፡ ሁለተኛ ፡ ተኰሰና ፡ ታላቅ ፡ የቁልቋል ፡ ዛፍ ፡ ነበረ ፡ ያን ፡ ዛፍ ፡
ቆራረጠና ፡ ተምድር ፡ ገባ ። በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እየፈራ ፡ ይጠጋ ፡ ጀመረ ፡
አጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ግን ፡ ከተቀመጡት ፡ አልተንቀሳቀሱም ፡ ጋሻዎን ፡ ይዘ
ው ፡ ተተቀመጡበት ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ ሁነው ፡ ንሳ ፡ ያን ፡ አረር ፡ አምጣው ፡
አሉና ፡ የራኬቱ ፡ አረር ፡ እንደ ፡ ጋለ ፡ በእንጨት ፡ ቀርቅሮ ፡ ለንጉሡ ፡ አሳያ
ቸው ፡ ቁመቱ ፡ ተክንድ ፡ ጥቂት ፡ ያንሳል ፡ ባራት ፡ ወገን ፡ ጐድጓዳ ፡ ነበረበ
ት ፡ ንጉሡ ፡ ያነን ፡ አዩና ፡ እኔ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ የተጣላሁ ፡ መስሎኝ ፡ ነው ፡
ለካ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ተጣልቸ ፡ ያለሁ ፡ አሉና ፡ አፈፍ ፡ ብለ
ው ፡ ከተቀመጡበት ፡ ተነስተው ፡ መድፉን ፡ ጐትቱና ፡ እንሒድ ፡ አሉ ፡ መ
ድፉ ፡ መጐተት ፡ ሲጀመር ፡ በስከወድያው ፡ ዝናብ ፡ ዘነበ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡
መቅደላ ፡ ከአምባው ፡ እግር ፡ ሰላምጌ ፡ ከሰፈራቸው ፡ ገቡ ፡ ወድያው ፡ እን
ደ ፡ ገቡ ፡ የፊተውራሪ ፡ ገብርየን ፡ ሞት ፡ ሰሙና ፡ ሙሉውን ፡ ሌት ፡ ሲያለ

ቅሱ ፡ አደሩ ፡ እንባቸው ፡ በአንገታቸው ፡ እስኪወርድ ፡ የናቴ ፡ ልጅ ፡ ጓዴ ፡ ጓዴ ፡ እያሉ ።

በየሰፈሩም ፡ ዋይታና ፡ ልቅሶ ፡ ሁኖ ፡ አደረ ። ከንጉሥ ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ ፈረንጆችም ፡ ከአምባ ፡ የታሰሩትም ፡ የፈረንጅ ፡ ዘር ፡ የሆነም ፡ ሎሌም ፡ ገረድ ፡ ሳይቀር ፡ እየተጨነቀ ፡ እየተጠበበ ፡ አደረ ፡ ነገ ፡ ልንደበደብ ፡ ነን ፡ እያለ ።

በነገታው ፡ ቅዳሜ ፡ ሹር ፡ ነበርና ፡ ንጉሡ ፡ ተሰልፈው ፡ ወደ ፡ እንግሊዞች ፡ ሰፈር ፡ መተያያ ፡ መነጠር ፡ ይዘው ፡ ተቀምጠው ፡ ያዩ ፡ ጀመር ፡ እንግሊዞችም ፡ ወድቆ ፡ ያደረውን ፡ ቁስለኛ ፡ የንጉሡ ፡ እያነሱ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ይወስዱ ፡ ነበር ። የሞተውንም ፡ ሲቀብሩ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ንጉሥ ፡ በመነጠር ፡ እያዩ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ የእንግሊዞች ፡ መልክተኛ ፡ ደብዳቤ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መጣ ፡ ደብዳቤውም ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ እኛስ ፡ ሰዎቻችን ፡ ልናስፈታ ፡ ነው ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ወደ ፡ ርሰዎ ፡ ቢሰድዋቸው ፡ አሰሩዋቸው ፡ መልሰው ፡ በልመና ፡ ይፍቱልኝ ፡ ብለው ፡ ቢለምኑ ፡ አልፈታም ፡ አሉ ።

አሁንም ፡ ተልከን ፡ መጥተን ፡ ምን ፡ አመጣችሁ ፡ ብለው ፡ ሳይጠይቁን ፡ በጠብ ፡ ተቀበሉን ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ያለፈው ፡ አለፈ ፡ ፩ጊዜ ፡ ሆነና ፡ ሁለተኛ ፡ የክርስቲያን ፡ ደም ፡ አይፍሰስ ፡ ሰዎቻችን ፡ ይስጡን ፡ እስሮችም ፡ ያልታሰሩትም ፡ በሐበሻ ፡ የተወለዱቱ ፡ ሳይቀር ፡ የነጭ ፡ ዘር ፡ የሆነ ፡ ይስጡን ። ከርሰዎ ፡ ጋርም ፡ እንገናኝና ፡ ከንግሥታችን ፡ ያመጣውን ፡ ቃል ፡ እንናገራለን ፡ ከዚህ ፡ ቀደምም ፡ በደል ፡ ከርሰዎ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ከኛ ፡ በደል ፡ የለም ። ብለው ፡ እንግሊዞች ፡ ላኩ ። በዚህው ፡ ንዴት ፡ በዝያው ፡ ቀን ፡ በሽጉጥ ፡ ለመሞት ፡ ከጅለው ፡ ነበር ፡ ንጉሡ ፡ ሽጉጡ ፡ ከእጃቸው ፡ ሊያስለቅቁ ፡ ወደ ፡ ሽቅብ ፡ ተተኰሰ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ከተራራው ፡ ተነስተው ፡ ወደ ፡ ሰፈረዎ ፡ ገቡና ። ከመኳንንቶች ፡ ጋራ ፡ ምክር ፡ አደረጉ ። እኩሎቹ ፡ መኳንንቶች ፡ ነጭ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ዘር ፡ ሳናስቀር ፡ እንረደው ፡ እና ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ አርገን ፡ እንሸሽ ፡ እንግሊዝም ፡ አይከተለነም ፡ አሉ ። እኩሌቶቹ ፡ ግን ፡ አይሆንልንም ፡ ባላ ፡ ገር ፡ ጠልቶናልና ፡ ባላ ፡ ገር ፡ ሊጫወትብን ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ አናመልጥም ፡ እንግሊዝም ፡ ይከተለናል ። ሰዎቹ ፡ ብናርዳቸው ፡ የኛም ፡ ሊታረድ ፡ ነው ፡ ጀንሆይ ፡ አይግቡ ፡ እንጅ ፡ ሰዎቹን ፡ እንስጠው ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሔዳል ፡ ብለው ፡ መከሩ ፡ ንጉሡም ፡ እኔን ፡ ግባ ፡ አይበለኝ ፡ እንጅ ፡



እሽ ፡ ሰዎቹን ፡ ይዞ ፡ ይሒድ ፡ እስሮች ፡ የሆኑ ፡ ሰራተኞች ፡ ተዚህ ፡ የተወለዱት ፡ ይተውልኝ ፡ አሉ ።

የዚህን ፡ ምላሽ ፡ ይዘው ፡ ደጃች ፡ ዓለሜ ፡ ጓሉና ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ዓለቃ ፡ እንግዳ ፡ ከነጮችም ፡ ማርቲን ፡ ፍላድ ፡ እነዚህ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ሰፈር ፡ ሔዱና ፡ ቃሉን ፡ ተናገሩ ፡ እንግሊዞችም ፡ ሰራተኞቹም ፡ በሐበሻ ፡ የተወለዱትም ፡ ሁሉ ፡ የኛ ፡ ዘር ፡ ነውና ፡ ነገ ፡ ይስደዱልን ፡ ብለው ፡ መልሰው ፡ ላኩ ። ንጉሡም ፡ እሽ ፡ ብለው ፡ አደሩና ፡ ቅዳሜ ፡ ሹር ፡ ማታ ፡ ንጉሥ ፡ ብዙ ፡ ፍሪዳና ፡ ብዙ ፡ በግ ፡ ወደ ፡ እንግሊዞች ፡ ሰደዱ ፡ ደጃች ፡ አለሜና ፡ አለቃ ፡ እንግዳ ፡ ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ ፡ ይዘው ፡ ሄዱ ፡ እንግሊዞችም ፡ አልተቀበልዋቸውም ፡ እንዲህም ፡ አልዋቸው ፡ እኛ ፡ በገንዘባችን ፡ ልንገዛ ፡ ነው ፡ የምንፈልግ ፡ እና ፡ በዋጋ ፡ ቢሆንልን ፡ በወደድን ፡ ነበር ፡ አልዋቸው ፡ ደጃች ፡ አለሜ ፡ ጓሉና ፡ አለቃ ፡ እንግዳም ፡ እንዲቀበልዋቸው ፡ የግድ ፡ ይለምኑ ፡ ነበር ፡ እንግሊዞችም ፡ በሉ ፡ እደሩና ፡ ነገ ፡ መክረን ፡ አንቀበላችሁ ፡ አለን ፡ ሰዎቻችን ፡ ጃንሆይ ፡ በማለዳ ፡ ቢሰዱልን ፡ የዝያን ፡ ጊዜ ፡ እንቀበላለን ፡ አሉና ፡ እነ ፡ ደጃች ፡ ዓለሜም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ልከው ፡ ከዝያው ፡ አደሩ ፡ እሁድ ፡ የፋሲካ ፡ እለት ፡ በማለዳ ፡ ሰው ፡ ሳያየቸው ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደሮች ፡ ባሻ ፡ ፈለቀ ፡ አለቃ ፡ ሁነው ፡ ፪ወይም ፡ ፫ኩባንያ ፡ የሚሆኑ ፡ ከንጉሡ ፡ ሰፈር ፡ አጠገብ ፡ ከዱር ፡ ገብተው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፡ ምን ፡ አልባት ፡ ንጉሥ ፡ ተጠጥተው ፡ እስሮችና ፡ ፈረንጆችን ፡ በመንገድ ፡ ቆይታችሁ ፡ ግደልዋቸው ፡ እንዳይሉ ፡ ብለው ።

አጤ ፡ ግን ፡ የፋሲካ ፡ እለት ፡ በማለዳ ፡ የእንግሊዝ ፡ እስሮች ፡ አስጠሩና ፡ ሂዱ ፡ አልዋቸው ፡ ሰራተኞችም ፡ የሚስዮንም ፡ በሐበሻ ፡ የተወለደውንም ፡ ሁሉን ፡ አስጠርተው ፡ ሒዱ ፡ ብለው ፡ አሰናበቱት ። ስለ ፡ ፋሲካ ፡ በዓልም ፡ ለሁሉ ፡ ፍሪዳ ፡ ፍሪዳ ፡ ሰጥተውት ፡ ነበር ፡ የነጭ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ግን ፡ ሂድ ፡ ያሉት ፡ ጊዜ ፡ እውነት ፡ አልመሰለውም ፡ ነበር ፡ ሊታዘቡን ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ሊደበድቡን ፡ ነው ፡ እያለ ፡ እኩሉ ፡ አንሔድም ፡ ይል ፡ ገባ ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ ግድ ፡ የላችሁም ፡ ሂዱ ፡ ይሉ ፡ ነበር ፡ እስሮቹ ፡ እንግሊዞች ፡ ግን ፡ አልፈሩም ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ወጡ ፡ ከነዝያ ፡ በኋላ ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡ እየነሳ ፡ ወጣ ። ከደጅና ፡ ከአደባባይ ፡ ተቀምጦ ፡ የነበር ፡ ወታድር ፡ ግን ፡ ነጭ ፡ የሆነ ፡ እንዳይደበድቡት ፡ የምን ፡ ሰደዱት ፡ ይላል ፡ አንድ ፡ አንዱ ፡ ግን ፡ እንኳ ፡ እግዚአብሔር ፡ አወጣቸው ፡ ንጉሡ ፡ ባለ ፡ ቤታቸው ፡ ያመጡት ፡ መከራ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ እነዚህ ፡ ምን ፡ አርገው ፡ ይል ፡ ነበር ። ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ኰንሱል ፡ ኬ

ምሮንና ፡ ራሰም ፡ በፊት ፡ ሁነው ፡ የቀረው ፡ ነጭ ፡ ሁሉ ፡ ሴቱም ፡ ወንዱም ፡ የነጭ ፡ ዘር ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ እየፈራ ፡ እየተብረጀረጀ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እየዞረ ፡ እያየ ፡ ይጋልብ ፡ ጀመረ ። ገና ፡ ከሰፈሩ ፡ አጠገብ ፡ ሳይለቅ ፡ የእን ግሊዝ ፡ ወታደር ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ከዱሩ ፡ ተስጦ ፡ ኑሮ ፡ እስሮቹና ፡ የነጭ ፡ ዘር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ማኸሉ ፡ አገባና ፡ አራ ፡ ብሎ ፡ ወታደሩ ፡ አተቴ ፡ የቆመ ፡ ጊዜ ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ ሙዜቃ ፡ ቢነፉ ፡ አባቁልቶችም ፡ እየደነበሩ ፡ ገደል ፡ ሊገቡ ፡ ቀረቡ ፡ አሽከሮችም ፡ ያለቅሱ ፡ ጀመሩ ፡ ነጮች ፡ የሆኑ ፡ ግን ፡ ፊታ ቸው ፡ ጠቍሮ ፡ የነበረ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ተለውጦ ፡ ብርሃን ፡ ሆነ ። እንኳን ፡ ነ ጮቹ ፡ የነዝያ ፡ ሎሌና ፡ ገረድ ፡ ፍሥሐ ፡ አደረገ ። ባሻ ፡ ፈለቀም ፡ የፊተው ራሪ ፡ ገብርየ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጠው ፡ የርሳቸው ፡ ወርቅ ፡ አምበሳ ፡ ለምድ ፡ ለ ብሰው ፡ ወርቅ ፡ ጋሻ ፡ ባለ ፡ ጫሜ ፡ ሾተል ፡ ታጥቀው ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደ ርና ፡ ሙዚቃ ፡ እየተነፋ ፡ ፈረሱ ፡ እየዘለለ ፡ እስሮችን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እን ግሊዞች ፡ ሰፈር ፡ ሲቀርቡ ፡ በሰፈሩ ፡ የነበረ ፡ ወታደር ፡ አተቴ ፡ ብሎ ፡ ሰል ድር ፡ አም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ የተማገረ ፡ ግድግዳ ፡ መስሎ ፡ ወታደ ሩ ፡ ቆመ ፡ ሎርድ ፡ ናፔር ፡ ከመኳንታቸው ፡ ጋራ ፡ ከድንኳን ፡ ወጥተው ፡ መ ቸም ፡ ልብሳቸውና ፡ ትጥቃቸው ፡ ላይን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ ቁመታቸው ፡ ሰገድ ፡ ሰገድ ፡ የሚያህሉ ፡ ከደጅ ፡ ወጥተው ፡ ቁመው ፡ ቆዩ ፡ እስሮችም ፡ ከበቅሎ ፡ ወረዱና ፡ ተሳሳሙና ፡ ሐዋርዮ ፡ ሐዋርዮ ፡ ሆነ ፡ ደስታና ፡ ውካታ ፡ ሆነ ፡ ሙ ዚቃም ፡ ምድር ፡ ሊፈነቅል ፡ ቀረበ ፡ ፈረሰኞች ፡ የተቀመጥዋቸው ፡ ፈሮሶች ፡ እንደ ፡ ሙዚቃው ፡ ስልት ፡ ይረግጣሉ ፡ የተቀመጥዋቸው ፡ ጎበዞችም ፡ ደረ ታቸው ፡ ሊሰነጠቅ ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ፡ በወኔ ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ወታደሩ ፡ በየሰፈሩ ፡ ሔደ ፡ ሎርድ ፡ ናፔርና ፡ መኳንንቱ ፡ ከእስሮችም ፡ ኰንሱል ፡ ኬ ምሮንና ፡ ምስተር ፡ ራሰም ፡ ወደ ፡ ሎርድ ፡ ናፔር ፡ ድንኳን ፡ ገቡ ፡ ለቀሩቱ ፡ እስሮችና ፡ የነጭ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ታላላቅ ፡ ድንኳን ፡ ተተክሎ ፡ ምግቡ ፡ ተሰ ናድቶ ፡ መጠጡ ፡ ሁሉ ፡ ቀርቦለት ፡ ቆየና ፡ በየጓደኛው ፡ በየወገኑ ፤ በድንኳ ን ፡ ገባ ። ምግብና ፡ መጠጥም ፡ ሞላ ። ቀኑም ፡ ፋሲክ ፡ ነበር ።

በዝያው ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ የማርቲን ፡ ፍላድ ፡ ምሽት ፡ ዜማ ፡ አደረጉ ፡ መዝ ሙር ፡ ፴፯ ፡

በዝያን ፡ ቀን ፡ የወጡ ፡ እስሮችና ፡ ሰራተኞች ፡ አስተማሮችም ፡ አዳኞ ችም ። ከሐበሻ ፡ የተወለዱ ፡ የነጭ ፡ ልጆችም ፡ ስማቸው ፡ እንጽፋለን ።



### እስሮች ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኰንሱል ፡ ኬምሮን ። | ፩ | ማክረር ፡ | ፮ |
| ምስተር ፡ ራሰም ። | ፪ | እስተርን ፡ | ፯ |
| ሃኪም ፡ ብላንክ ፡ | ፫ | መኬልቢ ። | ፰ |
| ጸሐፊው ፡ ጥሪዶ ፡ | ፬ | ሩዝንታል | ፱ |
| ኬረንስ ። | ፭ | የሩዝንታል ፡ ምሽት ። | ፲ |

### ሰራተኞች ፡

| | |
|---|---|
| አቶ ፡ ዋልድ ፡ ማየር ፡ እንጨት | ፩ |
| ሣል ፡ ሚላር ፡ ብረት | ፪ |
| ዮሐንስ ፡ ማየር ፡ ዓረብያ ፡ ነጅ ። | ፫ |
| አቶ ፡ ጸንደር ፡ እንጨትና ፡ | ፬ |
| ቤንደር ፡ አጎዶ ፡ ፎርኖ ፡ | ፭ |
| ሞሪጽ ፡ ምስል ፡ አፍሳሽ ። | ፮ |
| ቢርጎ ፡ እንጨትም ፡ ብረትም ፡ የጠበንጃ ፡ | ፯ |
| አቶ ፡ ሽምፐር ፡ የኖራ | ፰ |

### አስተማሪ ፡

| | |
|---|---|
| ማርቲን ፡ ፍላድና ፡ እስታይገር ፡ | ፱ |
| ወይዘሮ ፡ ፍላድ ፡ ፓውሊና ፡ | ፲፩ |

### ዎፍ ፡ አዳኞች ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኤስለር ፡ | ፲፪ | ቢርጎ ፡ አጋት ፡ | ፲፮ ። |
| ሽለር ፡ | ፲፫ | ቢርጎ ፡ ዌላቲን ፡ | ፲፯ ። |
| የቢርጎ ፡ ምሽት ፡ | ፲፬ | ፍላድ ፡ ሐና ፡ | ፲፰ ። |
| የቢርጎ ፡ የሚል ፡ ልጆች | ፲፭ ። | ፍላድ ፡ ፍሪድሪሀ ፡ | ፲፱ ። |

እኒህ ፡ ከሐበሻ ፡ ያልተደበለቁ ፡

እናታቸው ፡ ሐበሻ ፡ አባታቸው ፡ አይሮፓ ፡ የሆኑ ፡ በሐበሻ ፡ የተወለዱ ፡ እኒህ ፡ ናቸው ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሽምብር ፡ እንግዳ ፡ ሽት ፡ | ፩ | ሞሪዕ ፡ ያዕቆብ ፡ | ፭ |
| ፓርክስ ፡ ጆን ፡ | ፪ | ማየር ፡ ዮሐንስ ፡ | ፮ |
| ካሳ ፡ ጻንደር ፡ | ፫ | ቤንደር ፡ ጎት ፡ ሂልፍ ፡ | ፯ |
| ቤል ፡ አሊጋዝ ፡ | ፬ | | |

ሴቶች ፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጻንደር ፡ ጥሩነሽ ፡ | ፩ | ሽምፐር ፡ ትብለጥ ፡ | ፰ |
| ጻንደር ፡ አቦዘነች ። | ፪ | ሮዚሴ ፡ ዋልድ ፡ ማየር ፡ | ፱ |
| ቤል ፡ የውብ ፡ ዳር ፡ | ፫ | ሳልሚለር ፡ ኤልሳቤት ፡ | ፲ |
| ቤል ፡ በለጠች ፡ | ፬ | ቤንደር ፡ ማሪለ ፡ | ፲፩ |
| ቤል ፡ ሉዊዛ ፡ | ፭ | ቤንደር ፡ ማርታ ፡ | ፲፪ |
| ደስታ ፡ ሽምፐር ፡ | ፮ | ቢንዜሌ ፡ ሶፊ ፡ | ፲፫ |
| ሽምፐር ፡ ጣይቱ ፡ | ፯ | ሞሪጽ ፡ ወለተ ፡ የሱስ ፡ ምሽት ፡ | ፲፬ |

እነዚህ ፡ በእንግሊዝ ፡ ምርኮ ፡ የወጡ ፡ የነጭ ፡ ዘር ፡ የሆኑ ።

ራስ ፡ መሸሻ ፡ የአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልጅም ፡ እጉድ ፡ ገቡ ፡ ባለቤታቸው ፡ አባታቸውን ፡ ትተው ፡ እንግሊዞችም ፡ እጉድ ፡ እስሮች ፡ ተቀብለው ፡ አደሩና ፡ በነገታው ፡ ሰኞ ፡ በ፰ሰዓ ፡ ሌሊት ፡ በማለዳ ፡ ፈረሶች ፡ ጥሬ ፡ አብሉ ፡ ተብሎ ፡ ጥሩምባ ፡ ተነፋና ፡ ፈረሱስ ፡ በቅሎውስ ፡ አንድነት ፡ ጮኸና ፡ ጥሬ ፡ ይበላ ፡ ጀመረ ። ጥሬ ፡ ከተጨረሰም ፡ መልሶ ፡ በ፱ሰዓ ፡ ፈረሶች ፡ የእግራቸው ፡ ችንካር ፡ ይቸነከሩ ፡ ነበር ፡ የሚወለውልም ፡ የሚጭንስ ፡ ሁኖ ፡ በቶሎ ፡ ሁሉ ፡ ተጫኑና ። አንድ ፡ ቄስ ፡ ጸሎት ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፡ መኳንንቱ ፡ ሁሉም ፡ የጦር ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ ጎራዴያቸውን ፡ እንደ ፡ ታጠቁ ፡ ተምበርክከው ፡ ጸሎት ፡ አደረጉና ። በስከ ፡ ወድያው ፡ ጥሩምባ ፡ ተነፋ ፡ ፈረሰኞቹ ፡ አንድነት ፡ ከፈረስ ፡ ወጡ ፡ እግረኛም ፡ በየሰልፉ ፡ ሪጋ ፡ ሁኖ ፡ ግጥም ፡ ብሎ ፡ ቆመና ፡ በየሰልፍህ ፡ ተጓዝ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ፈረሰኛው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እግረኛውም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ጡርምባው ፡ ምድር ፡ እየፈነቀለ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ አምባ ፡ ባቀበቱ ፡ ይጓዝ ፡ ጀመረ ። ንጉሡም ፡ መምጣቱን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የአምባው ፡ በር ፡ ጠባቆች ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ከሜዳው ፡ ወርደው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎቻቸው ፡ ጋር ፡ ተሰል



ፈው ፡ ቆዩ ፡ መድፎቻቸውም ፡ ካምባው ፡ ውጭ ፡ አዝግበው ፡ ነበር ፡ እንግሊዞች ፡ ቀረብ ፡ ሲሉ ፡ መድፍ ፡ ተኰሱባቸው ፡ ንጉሥም ፡ ባለ ፡ ቤታቸው ፡ በሐመር ፡ ፈረሳቸው ፡ ወጡና ፡ ፩ጠበንጃ ፡ አነገቱ ፡ ፩ጠበንጃም ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ማኽል ፡ ለማኽል ፡ ሒደው ፡ ወደ ፡ እንግሊዞች ፡ ተኰሱ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ አትተኩሱባቸው ፡ ብለው ፡ አዘው ፡ ነበር ፡ ይላሉ ፡ አጤ ፡ ግን ፡ ከፈረሴ ፡ ደንደስ ፡ እሞታለሁ ፡ እያሉ ፡ እያመላለሱ ፡ ይተኩሱ ፡ ነበር ፡ ፈረሳቸው ፡ እስኪደክም ፡ ድረስ ። እንግሊዞች ፡ ግን ፡ እርሳቸውን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ እየተኰሱ ፡ ወደ ፡ አምባው ፡ ተጠጉ ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ ራስ ፡ እንግዱና ፡ ወንድማቸው ፡ አዛዥ ፡ ፈንታ ፡ ሞቱ ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ አምባው ፡ ገቡ ።

እንግሊዞችም ፡ ተከታትለው ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ገቡ ፡ መድፉም ፡ እጅታ ፡ አደረጉት ፡ በሩም ፡ የንጉሥ ፡ ጠባቆች ፡ ለቀቁትና ፡ ገባ ፡ ብለው ፡ ለንጉሥ ፡ ተናገሩ ፡ ንጉሡም ፡ ሽጉጠዎን ፡ መዘዙና ፡ ባፍዎ ፡ ጎርሰው ፡ ተኰሱትና ፡ ሞቱ ።

እንግሊዞችም ፡ ገብተው ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፡ እያሉ ፡ ጠየቁ ፡ ከወደቁት ፡ ለይ ፡ አሳዩዋቸውና ፡ ደነገጡ ፡ አዘኑም ፡ ከዝያ ፡ ወድያ ፡ ዕቃቤቶች ፡ የነበሩ ፡ ዕቃውን ፡ ቤቱን ፡ ያሳዩዋቸው ፡ ጀመሩ ፡ ነፍጡም ፡ ምንጣፉም ፡ መድፎችም ፡ ታላላቆች ፡ ከዝያው ፡ ነበረ ፡ የነሃስ ፡ ነው ፡ እና ፡ በተኰስ ፡ ሰነጠቁት ፡ ባለ ፡ ቋዱ ፡ ነፍጥ ፡ ሁሉ ፡ በእሳት ፡ ተቃጠለ ። ከዝያው ፡ የቆዩ ፡ እስሮች ፡ ተፈቱ ፡ መኳንንትም ፡ እየወጡ ፡ ወደ ፡ እንግሊዞች ፡ ሰፈር ፡ ይጓዝ ፡ ጀመረ ፡ ከአምባ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ መጥተው ፡ ሰፈሩ ። እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ከልጃቸው ፡ ከደጃች ፡ አለማየሁ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ሰፈር ፡ ወረዱ ፡ እንግሊዞችም ፡ በክብረት ፡ ምግባቸውን ፡ ይሰጡዋቸው ፡ ነበር ፡ ለደንገጥሮቻቸውም ፡ ለሰዋቸውም ፡ ሁሉ ። ጀንሆይም ፡ አድረው ፡ ማክሰኞ ፡ ተቀበሩ ። እንግሊዞችም ፡ ወደ ፡ ሰፈራቸው ፡ ተመለሱ ፡ በዝያም ፡ ሰፈር ፡ ፪ቀን ፡ ውሎ ፡ ሆነ ፡ ጉዘው ፡ ግን ፡ የፈተውራሪው ፡ ይጓዝ ፡ ነበር ፡ ዝሆኖችም ፡ በፊት ፡ ተጉዘው ፡ ነበር ፡ የበሽሎ ፡ አቀበት ፡ ጠባብ ፡ ነውና ፡ ወጥቶ ፡ ባባ ፡ ሰፍሮ ፡ ቆየ ። አንድ ፡ አዝማሪ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዓርባ ፡ ጡም ፡ ጡሞ ፡ ፋሲካ ፡ ሲደርስ ። በአፈር ፡ ገደፈ ፡ አሉ ፡ ያበሻ ፡ ንጉሥ ። አለ ።

ወይዘሮ ፡ መስተዋትና ፡ ወይዘሮ ፡ ወርቂት ፡ የሚባሉ ፡ የወሎ ፡ ገጋሮች ፡ ወደ ፡ ሎርድ ፡ ናፔር ፡ መጥተው ፡ ነበር ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተው ፡ ሰደድዋቸው ፡ እነዝያ ፡ ግን ፡ ሊገዙ ፡ የመጡ ፡ መስሎአቸው ፡ አገራቸው ፡ ለሌላ ፡ እንዳይሆን ፡ ደጅ ፡ ሊጠኑ ፡ ናቸው ።

ይህነን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ እንግሊዞች ፡ በመጡበት ፡ መንገድ ፡ ተመለሱ ።

ባባ ፡ በሚባል ፡ ሜዳ ፡ እሁድ ፡ ቀን ፡ ውሎ ፡ አድርገው ፡ ጦራቸውን ፡ አሰልፈው ፡ ግባት ፡ ታዩ ።

ፈረሰኛም ፡ እግረኛም ፡ ባለ ፡ መድፍም ፡ እንደ ፡ ሥራቱ ፡ አስልፈው ፡ መኳንንትም ፡ እንደ ፡ ክብረቱ ፡ መጠን ፡ በየ ፡ ማአርግ ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፡ መዚቃው ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ ወግ ፡ እየተነፋ ፡

የጦር ፡ አለቆቹ ፡ ሁሉ ፡ ጎራዴ ፡ ጎራዲያችውን ፡ መዘው ፡ ተሰለፉ ።

ሎርድ ፡ ናፔርም ፡ በማካከል ፡ ነበሩ ፡ የርሳቸው ፡ ፈረስ ፡ ከፈረሶች ፡ ሁሉ ፡ ይረዝማል ፡ ባጠገባቸውም ፡ ሎርድ ፡ ሐምልቶን ፡ የሚባሉ ፡ ልብሳቸው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የተለበጠ ፡ የሚመስል ፡ ወጣት ፡ ጎበዝ ፡ ነበሩ ፡ የእንግሊዝ ፡ ወታደር ፡ ሁሉ ፡ ልብሱ ፡ በየዓይነቱ ፡ የተለየ ፡ ነበር ፡ ቀይ ፡ የለበሰ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ጥቁር ፡ የለበሰ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ቡላ ፡ የሚመስል ፡ የለበሰ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የሌት ፡ ዳውርዮችም ፡ የበግ ፡ አጎዛ ፡ ቀሚስ ፡ የለበሱ ፡ ነበሩ ። ባርኔጣቸው ፡ የተሰነገለ ፡ ብር ፡ የሚመስል ፡ ፈረሰኞችም ፡ ነበሩ ፡ በጠኃይ ፡ ወገን ፡ ቢያዩቸው ፡ ለዓይን ፡ ያንጸበርቃል ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ወገን ፡ ተሰልፈው ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ በባባ ፡ ሜዳ ፡ ተሰልፎ ፡ እግረኛ ፡ ሶልዳቶ ፡ እንግሊዞች ፡ የሒንድ ፡ እግረኛ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የእንግሊዝ ፡ ፈረሰኛ ፡ የሒንድ ፡ ፈረሰኞችም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ተሰለፉ ፡ የሂንድያ ፡ ወታደሮች ፡ መልካካም ፡ ጎበዞች ፡ ላይን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ናቸው ፡ ቁመታቸው ፡ ረጅሞች ፡ ናቸው ። ጠርቡሻቸው ፡ በእኩል ፡ ራሳቸው ፡ ያረጉታልና ፡ ያምርባቸዋል ፡ ጠጉራቸው ፡ ረጅም ፡ ነውና ፡ በመንቀሻ ፡ ነቅሰው ፡ ይጐነጉኑታል ። እኒህ ፡ ሁሉ ፡ በባባ ፡ ላይ ፡ መጥተው ፡ ተሰለፉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጡሩባ ፡ ነፋና ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ጠበንጃውን ፡ በትክሻው ፡ ሰቀለው ፡

መልሶ ፡ ቢነፋም ፡ ወደታች ፡ አወረደው ።

፫ስተኛ ፡ ቢነፋ ፡ ወታደር ፡ እግረኛ ፡ በ፪ክቢ ፡ እንደ ፡ አጥር ፡ ሁኖ ፡ ጀኔራሉና ፡ መኳንንቱን ፡ ከማኸል ፡ አገባቸው ፡

በ፬ተኛ ፡ የካቫሌርያ ፡ ጡርምባ ፡ ተነፋ ። በስከዝያው ፡ ፈረሰኛው ፡ መጥቶ ፡ ከእግረኛ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ አጥር ፡ ከበበው ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ፩የእንግሊዝ ፡ መኰንን ፡ ከፈረሱ ፡ ኮርቻ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ በእግሩ ፡ ቆመ ፡ ከዝያ ፡ ላይ ፡ ቁሞ ፡ ወረቀቱን ፡ ዘረጋና ፡ በእ



ንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ አነበበ ፡ መልሶም ፡ በአማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ አነበበ ፡ ደብዳቤውም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

የእንግሊዝ ፡ ንግሥተ ፡ ንግሥት ፡ በግፍ ፡ የታሰሩ ፡ ሰዎቻቸው ፡ ስለ ፡ መስፈታት ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቴዎድሮስ ፡ በፍቅር ፡ ላኩ ፡ አጤ ፡ ቴዎድስ ፡ ግን ፡ አልፈታም ፡ አሉ ። ስለ ፡ ዚህ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ጦር ፡ ሰደዱ ፡ ሰዎቻቸውን ፡ ስለ ፡ መስፈታት ። እግዜር ፡ ደግሞ ፡ ለንግሥታችና ፡ ለሠራዊትዋ ፡ ድል ፡ ሰጠታት ፡ ጠላትዋ ፡ የምታሸንፍበት ፡ ደግሞ ፡ የኛ ፡ መንግሥት ፡ አገር ፡ አይዘርፍ ፡ ሰው ፡ አይገድል ፡ የሰው ፡ ገንዘብ ፡ አይፈልግምና ፡ ስለ ፡ ዚህ ፡ የኛ ፡ ንግሥት ፡ ባለ ፡ ዕድል ፡ ናቸው ፡ ሠራዊታቸውም ፡ ያስቸንፋል ፡ እንጅ ፡ አይቸነፍም ። ለንግሥታችንና ፡ ለእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ዕድሜና ፡ ጤና ፡ ይስጥልን ። ያለ ፡ ጊዜ ። ወታደሩ ፡ ሁሉ ፡ ጩሆ ፡ አራ ፡ ሲል ፡ ጊዜ ። በሰከ ፡ ወድያው ፡ ሙዚቃው ፡ ይነፋ ፡ ጀምር ።

መድፉንም ፡ ይተኰስ ፡ ጀምር ፡ ምድር ፡ እስኪነቀቅ ፡ በስከ ፡ ወድያው ፡ ፈረሰኛ ፡ ባንደ ፡ ጊዜ ፡ ሜዳው ፡ የሚፈርስ ፡ መስሎ ፡ ሰንደቅ ፡ አላማውን ፡ እያንበለበለ ፡ እግረኛው ፡ ፫ጊዜ ፡ ዘረና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አለፈ ።

ከዝያ ፡ ወድያ ፡ እግረኛ ፡ ሶልደቶ ፡ ነጭ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ የሂንድ ፡ ወታደር ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሁኖ ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ ተከፍሎ ፡ የጦር ፡ አለቃውና ፡ መኳንንቱ ፡ ጎራዲያቸውን ፡ መዘው ፡ በማኸል ። ፈረሰኛ ፡ በግራ ፡ በቀኝ ፡ ሆነና ፡ ፈረሰኛውም ፡ እግረኛውም ፡ እንደ ፡ ጡርባው ፡ ስልት ፡ ይረግጥ ፡ ነበር ፡ በዝያው ፡ ጊዜ ፡ የእንግሊዞች ፡ መኳንንት ፡ በኩራት ፡ ጫንቃቸው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ደረታቸውም ፡ የሚገለበጥ ፡ ይመስላል ፡ ፈረሶቻቸውም ፡ እየዘለሉ ፡ እንደ ፡ ሙዚቀው ፡ ይረግጡ ፡ ነበር ።

በዝያው ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የሐበሻ ፡ ወታደር ፡ እንዲህ ፡ ሁኖ ፡ ሙዚቃ ፡ እየተነፋ ፡ ጦር ፡ ቢገጠም ፡ ግዝት ፡ ያርግብኝ ፡ እንዳልሸሽ ፡ አለ ። ግባቱ ፡ ከተጨረሰ ፡ የጦር ፡ አለቃም ፡ መኳንንቱም ፡ መታደሩም ፡ በየድንኳኑ ፡ ገባ ። በነገታውም ፡ በባባ ፡ ውሎ ፡ አድርገው ፡ የአጤ ፡ ቴድሮስ ፡ ወታደር ፡ የነበረ ፡ እስሮች ፡ የነበሩም ፡ የዋድላ ፡ የደላንታ ፡ የመጬት ፡ የጋይንት ፡ የጨጭሆ ፡ ምላሽ ፡ የቤጌምድር ፡ የደምብያ ፡ የዳራ ፡ የፎገራ ፡ የጐጃም ፡ ሰው ፡ በየአገርህ ፡ ግባ ፡ ብለው ፡ አሰናበቱት ፡ ስንቅም ፡ ሰጡት ፡ ለምርኮኛው ፡ ሁሉ ፡ ደግሞ ፡ በመንገድ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ እንዳይጣላ ፡ ብለው ፡ የጦሩ ፡ ዛብያ ፡ እየቆረጡ ፡ የጠበንጃውንም ፡ ሰደፉ ፡ እየሰበሩ ፡ ሰጡት ። በመንገድ ፡

አትጣሉ ፡ እያሉም ፡ መክረው ፡ ያማራ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አሰናበቱት ፡ እየመረቀ ፡ በየአገሩ ፡ ተበተነና ፡ ወታደሩ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አጤ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ገባ ፡ ይሉታል ፡

የትግሬ ፡ ዘማችና ፡ እስሮች ፡ የነበሩ ፡ እነ ፡ ራስ ፡ አርአያ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ምግብ ፡ እየተቀበሉ ፡ አብረው ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ ደጃች ፡ ካሳ ፡ ተገናኙ ።

በአዲ ፡ ግራት ፡ ኩፍኝ ፡ ገብቶ ፡ ነበር ፡ በእንግሊዞች ፡ ሰፈር ፡ ከዝያው ፡ ፩ታላቅ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሙቶ ፡ ከራስ ፡ ስብሐት ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ተቀበረ ።

የእንግሊዝ ፡ ጦርም ፡ በፊት ፡ በመጡበት ፡ መንገድ ፡ አርገው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ተመለሱ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ሲጓዙ ፡ በየሰፈሩበት ፡ ጦርና ፡ ምግብ ፡ እየተዉ ፡ ሂደው ፡ ነበርና ፡ ባደሩበት ፡ ሁሉ ፡ ሲሳይ ፡ ሞልቶ ፡ ነው ፡ ሙብል ፡ ሆነ ፡ መጠጥ ፡ ሆነ ፡ ፊትና ፡ ደጀን ፡ እየሆነ ፡ ነው ፡ የሚጓዝ ፡ የነበረ ፡ የፊተኛው ፡ ካደረበት ፡ የኋለኛው ፡ በነጌታው ፡ መጥቶ ፡ ይሰፍርበታል ፡ በየስፈሩ ፡ ሁሉ ፡ ጨርሶ ፡ ሲጓዝ ፡ ጥሬውም ፡ ዶቄትም ፡ ለባላገር ፡ ያሻሙታል ፡ ባላ ፡ ገሩ ፡ ሁሉ ፡ በእንጨትስ ፡ በሳርስ ፡ በበግ ፡ በፍየል ፡ በዶሮ ፡ በእንቁላል ፡ በወተት ፡ ብዙ ፡ ብር ፡ አገኘ ፡ በረከት ፡ ላመጣም ፡ ሳይሰጡ ፡ አይሰዱትም ። ነበሩ ። የአጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ምሽት ፡ እቴጌ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የደጃች ፡ ውቤ ፡ ስሜን ፡ ልጅ ፡ የደጃች ፡ አለማየሁ ፡ እናት ፡ በመንገድ ፡ ሲጓዙ ፡ ታመሙ ፡ ጨለቆት ፡ ሲደርሱ ፡ ሞቱ ፡ በዝያው ፡ ተቀበሩ ፡ የእንግሊዝ ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ጦር ፡ አሰልፈው ፡ ጡርንባ ፡ እየተነፋ ፡ ቀበርዋቸው ፡ ልጃቸው ፡ ደጃች ፡ አለም ፡ አየሁ ፡ ግን ፡ እናታቸው ፡ ቀብረው ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ወደ ፡ ሀንጣሎ ፡ ተጓዙ ፡ እስከ ፡ ሀንጣሎ ፡ ድረስ ፡ ስልክ ፡ ተተክሎ ፡ ነበር ፡ በኋላ ፡ ሲጓዙ ፡ እየነቀሉት ፡ ሔዱ ፡ ስልኩ ፡ ቀይ ፡ ነሐስ ፡ ነበርና ፡ ላንጠሮች ፡ ይጠቅማቸው ፡ ነበር ፡ አጤ ፡ ዮሐንስም ፡ በምላሽ ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋር ፡ በሰናፌ ፡ ተገናኙ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጦርም ፡ ከሰናፌ ፡ ወደ ፡ ዙላ ፡ ጠቅልሎ ፡ ወረደ ፡ ከዙላ ፡ ከባሕር ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ኮሞሎ ፡ የሚባል ፡ የምድር ፡ ባቡር ፡ ነበረ ፡ በዙላም ፡ ብዙ ፡ ካንቲና ፡ ብዙ ፡ የወታደር ፡ ድንኳን ፡ ብዙ ፡ ሰራተኛ ፡ የብረትም ፡ የእንጨትም ፡ ነበረበት ።

ያጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ታሪክ ፡ ተጨረሰ ። ከዚህው ፡ ቀጥለን ፡ ያጤ ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ያጤ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊጻፍ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ዚህ ፡ ካ፩ታላቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ቢሆን ፡ በተሻለ ፡ ይመስለኛል ።